# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናትና የጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ስነ ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


# ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሃላባ ብሄረሰብ


በ

ኤልያስ ወላንሳ ሀብተየስ

አማካሪ

ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር)



ሰኔ፣ 2006 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሃላባ ብሄረሰብ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለአማርኛ ስነ ፅሁፍ እና ፎክሎር
ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ኤልያስ ወላንሳ ሀብተየስ

ሰኔ 2006 ዓ.ም

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር**

# ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሃላባ ብሄረሰብ

በ

ኤልያስ ወላንሳ ሀብተየስ

2006 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም ፊርማ

______________________ ________________

______________________ ________________

የፈታኝ ስም ፊርማ

______________________ ________________

______________________ ________________

# ምስጋና

ጥናቴን በምተገብርበት ወቅት እንዴት ማካሄድ እንዳለብኝ አቅጣጫ በማመልከት፣ በማረምና በማስተካከል ታላቅ ድጋፍ ላደረጉልኝ  አማካሪዬ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ላቅ ያለ ምስጋናዬን እነሆ፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይህንን ጥናት አሰራበት ዘንድ ለፈቀደልኝ ትንሽ ገንዘብ አንሶኛልና  አላመሰግንም አልልም፡፡ መኮንን አስማማው (ሞኬ) ምናልባት ለዋልክልኝ ውለታ መጣኝ ባይሆንም  እባክህን ምስጋናዬን አልቀበልም አትበለኝ፡፡ ጸዳለ ታደሰ (ፀዲ) ጥሩ ባልነበርኩበት ሰዓት ጥሩ እሆን ዘንድ ጥረት አድርገሽ ጥሩ እህትነትሽን አሳይተሽኛልና ባለቀለም ምስጋና ቸርኩሽ፡፡ ሳሙኤል በቀለ ለጥናቴ መሳካት ትልቅ ድርሻ አለህና ልቤ ውለታህን ፈጽሞ አይረሳውም፡፡ ትምህርቴን ስማር የገንዘብ ፣ የሃሳብና የሙያ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ካሳሁን ኤርሚያስ ፣የምስራች ኤርሚያስ ፣ሚሚ በቴቦ፣ አምባዬ ምንዳና ሌሎችም ጥልቅ ምስጋናዬ በያላችሁበት ይድረሳችሁ፡፡

የምስራቅ ባዳዋቾ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤትና የወረዳው አስተዳደር አካላት የትምህርት እድል አግኝቼ እንድማር መልካም ፈቃዳችሁ በመሆኑ ከልቤ የሆነ ምስጋና ይገባችኋል፡፡ወ/ሮ ሙሉእመቤት ሶደኖ፣ አቶ እንዳለ በቀለና  አቶ አክሊሉ ወንድሙ መረጃ አቀባዮቼ ስለ ሃላባ ኦገቴ መረጃ እንዲሰጡኝ ስላመቻቻችሁልኝና እንደራሳችሁ ስራ በመቁጠር ሳትሰለቹ  ከኔ ጋር ደፋ ቀና በማለታችሁ እጅግ  በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በአጠቃላይ ለሃላባ ልዩ ወረዳ የባህላዊ ግጭት መፍቻ ሥርዓት ሽማግሌዎች ላደረጋችሁልኝ ልባዊ ትብብር ከልብ ላመሰግናችሁ ወደድኩ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................ I

ማውጫ ........................................ II

አበርክቶ ........................................ IV

አጠቃሎ ........................................ V

1. መግቢያ ........................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................ 2

1.1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2

1.1.2. የጥናቱ ዓላማ ........................................ 2

1.1.3. የጥናቱ ዘዴ ........................................ 2

1.1.3.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........................................ 3

1.1.3.1.1 ምልከታ ........................................ 3

1.1.3.1.2. ቃለ መጠይቅ ........................................ 4

1.1.3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........................................ 4

1.1.4. ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ ........................................ 4

1.1.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 5

1.1.6.ለችግሮቹ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........................................ 5

1.2 የሀላባ ብሄረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ........................................ 5

1.2.1. የሃላባ ብሔረሰብ ታሪክ ........................................ 5

1.2.2. የብሔረሰቡ መጠሪያ ስያሜ ........................................ 7

1.2.3. የብሔረሰቡ መገለጫ ባሕሎች ........................................ 7

1.2.3.1 ኦጋቴ /ባሕላዊ ሸንጐ/ ........................................ 8

1.2.3.2. ጋብቻ በሃላባ ብሄረሰብ ........................................ 10

1.2.3.3 ግርዛት /ጡርከሙ/ ........................................ 12

1.2.3.4 የለቅሶ ባሕል /አልፊቴ ሴራ / ........................................ 13

1.3.የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ........................................ 14

1.3.1. የግጭት ብያኔ ........................................ 14

1.3.2. የግጭት ዓይነቶች ........................................ 16

1.3.3. በሀገር ውስጥ የተሰሩ ባህላዊ የግጭት ጥናቶች ........................................ 17

2. ግጭት፣ የግጭት አፈታት ስርዓትና ተቋማት በሀላባ ብሄረሰብ ........................................ 21

2.1. የግጭት ዕሳቤ በሀላባ ብሄረሰብ ........................................ 21

2.2. የሀላባ ብሔረሰብ ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶች ........ 22
2.2.1. የቤተሰብ አለመግባባቶች ........ 22
2.2.2. የጐረቤት ግጭቶች ........ 24
2.2.3. የጐሣዎች እና የአጐራባች ሕዝቦች የርስ በርስ ግጭት ........ 25
2.2.4. በስርቆት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች ........ 25
3. የሀላባ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅርና ሥርዓቶች ምንነት ........ 30
3.1. መዋቅር ........ 30
3.2. ሥርዓቶች ........ 32
3.2.1. ምርጃሞ እና ሩበቴ ........ 32
3.2.2. የጉዳ እና የጉማ የዕርቅ ሥርዓቶች ........ 33
3.2.3. የጥቁር እንስሳ ዕርድ ሥነ-ሥርዓት ........ 34
3.2.4. የማርና የኮሶ መርጨት ሥነ ሥርዓት ........ 35
3.2.5. ራጋ ........ 36
3.2.6. ወደፋ ........ 38
3.2.7. ማጋ ........ 38
3.3 የስርዓቶቹ አከዋወን ሒደት ........ 41
4. የግጭት መፍቻ ተቋማት በሀላባ ብሄረሰብ ........ 48
4.1. ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ........ 48
4.2. ዘመናዊ የፍትህ መስጫ ተቋማት ........ 49
5. በመደበኛ ፍርድ ቤትና በአላባ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት /አገቴ/ መካከል ያለ ግንኙነት ........ 50
5.1. የአገቴው ሚና በሀላባ በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ ........ 50
5.2. በሀላባ ማህበረሰብ ዘንድ የአገቴው ስርዓት ተመራጭነት ........ 51
6. ትንተናና ቁዘማ ........ 54
6.1. የባህላዊ የፍትህ ስርዓት እሴቶች ........ 54
6.2 የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ጠንካራና ደካማ ገጽታዎች ........ 56
6.2.1. ባህላዊው የግጭት አፈታት ያሉት ጠንካራ ጎኖች ........ 56
6.2.2. የባህላዊው የፍትህ ስርዓት ደካማ ጎኖች ........ 57
6.3 ግጭት የፈጠሩት አካላት ባህላዊውን የፍትህ መፍቻ ስርዓት የሚመርጡበት ምክንያት ........ 57
6.4. የባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ የብሔረሰቡን ሰላም የማምጣትና የማስጠበቅ ሚና ........ 58
6.5. ማጠቃለያ ........ 61
6.6. ይሁንታ ........ 62
የተጠቀሱ ምንጮች ........ 64
አባሪዎች

# አበርክቶ

**ይህ ጥናት በረከትነቱ ፡-**

ለእናቴ:   ወ/ሮ እህታገኘሁ  አሰፋ

ለባለቤቴ:   ወ/ሮ ጸደቀች ኤርሚያስ

ለልጆቼ:   ሃሴታ ኤልያስና

አዕላፍ ኤልያስ  ይሁንልኝ፡፡

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት "ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በሃላባ ብሄረሰብ " በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥም ለጥናቱ የሚሆን መረጃ የተሰበሰበው የሀላባን ብሄረሰብ ባህል ጠንቅቀው ከሚያውቁ ሶስት ቁልፍና አስር ንዑሳን መረጃ ሰጪዎች እንደሆነ ተገልጿል፡፡ መረጃዎቹም የተሰበሰቡት ቃለ መጠይቅ በማድረግና የሀላባ ኦገቴ በሚሰበሰብበት ዐውድ ላይ በመገኘት በምልከታ መሆኑ ሰፍሯል ፡፡

የተሰበሰቡትን መረጃዎችም ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ መረጃዎቹም የሀላባ ኦገቴ ግጭቶችን ለመፍታት ከመጀመሪያ እስከማለቂያው ድረስ ምን አይነት ሂደት እንደሚከተሉ፣ ምን አይነት ስርዓት እንደሚከወን በማሳየት ቀርቧል፡፡ በመቀጠልም በሃላባ ብሄረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች ምን ምን እንደሆኑና እያንዳንዳቸውንም ለመፍታት የሚከወኑትን ሰርዓቶች በሚገልጽ መልኩ ቀርቦበታል፡፡

በሃላባ ብሄረሰብ ውስጥ ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት በሃቀኝነትና በታማኝነት ህብረተሰቡን እያገለገለ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩትን ግጭቶች ስራዬ ብሎ በመስራቱ ምክንያት ባህላዊ ተቋሙ ከመደበኛው የፍርድ ተቋም ይልቅ በህዝቡ የተሻለ ተመራጭ ሆኖ እየሰራ ይገኛል፡፡ በስርዓቱም ከግጭት በኋላ ዕርቅ ሲፈጸም እንደ ጥፋቱ መጠን ካሳ ይከፈላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም በዳይ ካሳውን እስኪከፍል ድረስ ዋስ(ሩበቴ) በመጥራት እንደሚቆይ ተገልጾበታል፡፡ በብሄረሰቡ የባህላዊ ተቋሙ ውሳኔ በጣም የሚከበርና የሚፈጸም ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን በባህላዊ ህጉም ሆነ በሽማግሌዎቹ እርግማን የከፋ ነገር እንደሚደርስ ተቀምጧል፡፡

የሃላባ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩትን ግጭቶች በመፍታት፣ በብሄረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግረኞችን በመርዳት፣ ከመደበኛው የፍትህ ተቋም ጋር በመተባበር ህዝቡ በሰላምና በመተሳሰብ እንዲኖር ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መንግስትና የሚመለከተው ክፍል ባህላዊ ተቋሙ የላቀ ስራ እንዲሰራና ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ና ማህበረ-ባህላዊ እሴትነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ የሚያመላክቱ አስተያየቶችም ተሰጥተውበታል፡፡

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የሚያጠነጥነው በሀላባ ብሄረሰብ ማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ በመግባት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በሚያበረክተው  በባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓት ምንነት ፣ መዋቅር፣ የአከዋወን ስርአትና የአፈጻጸም ሂደት ላይ ነው፡፡

ጥናቱ በውስጡ ስድስት ክፍሎችን ይዟል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል  ሶስት ንዑስ ክፍሎችን ማለትም የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት ፣ዓላማ፣ ጥናቱ የቀረበበትና መረጃ የተሰበሰበበትን ዘዴ አካቷል፡፡ በተጨማሪም  የሀላባን ብሄረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራን ከሀላባ ህዝብ ታሪክ፣ ከብሄረሰቡ ስያሜና መገለጫ ባህሎቹ አንጻር ዘርዝሯል፡፡

በክፍል ሁለት ደግሞ በሀላባ ብሄረሰብ ያለውን  የግጭት ዕሳቤ  ምን እንደሚመስልና በማህበርሰቡ ዘንድ ያለው ደረጃም ተገልጿል፡፡ በማከልም በሃላባ ውስጥ የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች ቀርበዋል፡፡

በክፍል ሶስትም እንዲሁ በብሄረሰቡ ግጭት የሚፈታባቸውን ተቋማት  አስተዳደራዊ መዋቅርና የግጭት አፈታት ስርዓት እንዴት እንደሚከወንና ምን እንደሚመስል በሚያሳይ መልኩ ተዘርዝሯል፡፡ በተጨማሪም የእርቅ ስርዓቱን ሂደትም  አስቀምጧል፡፡

በሀላባ ልዩ ወረዳ በአሁኑ ጊዜ በስራ ላይ ያሉ የፍትህ ተቋማት ምን ምን እንደሚመስሉና ምን ምን እንደሚሰሩ የተገለጸው  በክፍል አራት ነው፡፡ በዚህም ክፍል ሁለቱም የፍትህ ተቋማት ለማህበረሰቡ ያላቸውን ጠቀሜታ  እንዲሁም የአሰራር መዋቅራቸው ተካቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱ ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሃላፊነትና ሚና እንዲሁም እንዴት በጥምረት እንደሚሰሩም  ተዘርዝሯል፡፡

በሰድስተኛው  ክፍል ባህላዊው የፍትህ ስርዓት  በብሄረሰቡ ውስጥ ያሉትን እሴቶች በመግለጽ ፤ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን በመለየት ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት እንዳለውና ለህዝቡ ሰላም ማግኘት ያለውን እገዛ  በሚያሳይ መልኩ ተተንትኗል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

### 1.1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው የሀላባ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ብሎ ጥናት እንዲሰራ ያነሳሳው በሀላባ አጎራባች ወረዳ ተወልዶ ያደገና ለወረዳው ቅርብ በመሆኑነው፡፡ እንዲሁም መረጃውን በቅርበት ሊያገኝ ስለሚችልና በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ የሚከወነው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ከዚህ በፊት በዚህ ደረጃ በጥናት አለመዳሰሱ ይህንን ጥናት እንዲሰራ መነሻ ሆኖታል፡፡

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማ

ይህ የሀላባ ልዩ ወረዳ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገው ጥናት ዋና ዓላማው እንደሚከተለው ነው፡፡ በሀላባ ብሔረሰብ የውስጥም ሆነ የውጭ ግጭቶች ሲፈጠሩ የግጭት አፈታቱን ሂደት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ በመተንተን ማሳየት ነው፡፡

ከላይ የተገለፀው የጥናቱ ዋና ዓላማ ሲሆን የሚከተሉት ደግሞ ዝርዝር ዓላማዎቹ ናቸው፡፡

- በግጭት አፈታቱ ወቅት ምን ምን ደረጃዎች እንደሚታለፉ መግለጽ፡
- በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ የሚያጋጥሙ ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶች የትኞቹ እንደሆኑ ማሳየት፡፤
- በብሔረሰቡ ውስጥ በግጭት አፈታት ላይ ሴቶች ያላቸውን ሚና ማመልከት፡፡
- የሀላባ ብሔረሰብ ለግጭት ያለው አመለካከት ምን እንደሆነ መግለጽ፡፡
- በብሔረሰቡ ውስጥ ግጭቱን የሚፈቱት አካላት ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑና ያላቸውንም ሚና ማስረዳት ነው፡፡

### 1.1.3. የጥናቱ ዘዴ

የፎክሎር ጥናት በሚካሄድበት ወቅት ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት መስክ መውጣት ግድ ይሆናል፡፡ መስክ በመውጣትም መረጃዎችን በተለያየ መልኩ መሰብሰብ ይቻላል፡፡ ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር ፈቃደ አዘዘ በአማርኛ እንደሚከተለው

አስፍሮታል። የመስክ ምርምር በሶስት ልዩ ልዩ መልኮች ሊካሄድ እንደሚችልና እነዚህም ምልከታ(Observation)፣ ኢንተርቪው (Interview) ና መጠይቅ (questionnaire) እንደሆኑ ገልጿል(1995፤ 90)።በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጡት ዘዴዎች በዋናነት ሁለት ናቸው። እነሱም ምልከታና ቃለመጠይቅ ሲሆኑ በተጨማሪ ከጽሁፍ የሚገኙ መረጃዎችም ላይ ትኩረት በማድረግ መረጃውን አጠናክሯል።

አጥኚው መስክ በመውጣት የሚሰበስበውን መረጃ የገላጭ ምርምር ዘዴን (descriptive research method) በመጠቀም ተንትኗል። በዚህም የአተናተን ሂደት በባህላዊ የግጭት አፈታት አውዱ ላይ የተከወኑ ክዋኔዎች ሁሉ ትራንስክራይብ ተደርገው ተተንትነዋል። ክዋኔዎችን ለመከወን ተፈጥሯዊ መቼትን በዋናነት በመጠቀም ምልከታ ያደረገ ሲሆን፣በተለይም በየአስራ አምስት ቀኑ በየቀበሌያቱ እየተዘዋወረ የሚከወነውን የሀላባ ኦገቴ(ጎጎታ) በመመልከት፤ (በእርግጥ በእለቱ ሊታይ ታቅዶ የነበረው በግድያ ምክንያት የቀረበው ጉዳይ በተከሳሾቹ አለመገኘት ምክንያት ባይከወንም) በኦገቴው ክፍትህ አሰጣጥ ውጪ የሚከወኑ ተግባራትንና የኦገቴው የአከዋወን ስርኣትን እንዴትነት ለማየት ችሏል። በእለቱም ሲከወኑ የነበሩትን አጠቃላይ ክዋኔዎች በመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች ማለትም በቴፕ ሪከርደር፣በፎቶና በቪዲዮ ካሜራ ሰበስቧል።

### 1.1.3.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

### 1.1.3.1.1 ምልከታ

አጥኚው እነዚህ ባህላዊ ክዋኔዎች በሚከወኑባቸው አውዶች ላይ በመገኘት ባህላዊው የግጭት አፈታት ስርዓትና የፍትህ አሰጣጥ ሒደትን ሊመለከት ችሏል። በተለይም በየአስራአምስት ቀኑ የሚካሄደውን የሃላባ ኦገቴ ስርአት በሚከወንበት ቦታ በመገኘት ምልከታ አድርጓል።በዚህ አጋጣሚም የሃላቢ ኦገቴ ባህላዊ አውድ(context) ምን እንደሚመስልና እንዴት እንደሚጀመርና እንደሚከወን በመመልከት መረጃ ሰብስቧል። በክዋኔውም ላይ የወማውን አቀማመጥ ፣ የቆርቶዎችን ቃል አቀባበልና መረጃ አሰባሰብ ለመመልከት ችሏል። በተጨማሪም የየጎሳዎቹ መሪዎች በአካባቢያቸው ያለ አዲስም ሆነ ነባር ጉዳይ በዱዱቦ (ዜና) መልክ እንዴት እንደሚያቀርቡ ተመልክቷል።

### 1.1.3.1.2. ቃለ መጠይቅ

በብሄረሰቡ ውስጥ በትክክል መረጃ ሊያቀብሉ የሚችሉ መረጃ ሰጪዎችን በመጠየቅ የሚከወኑትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርኣቶችንና ሂደታቸውን በሚመለክት እንዲሁም የውሳኔ አሰጣጡን አጠቃላይ ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ ሰብስቧል፡፡ መረጃ ሰጪዎችም የተመረጡት የአካባቢውን ባህልና ወግ ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ በተመሳሳይ አውድ ላይ ብዙ ልምድ ያላቸውንና ትክክለኛ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ሽማግሌዎችን ከወረዳው ባህል ፣ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ስራ ሂደት አስተባባሪ ጋር በመሆን ነው፡፡

### 1.1.3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ከመስክ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች የሚቀብሉ መረጃ ሰጪዎች ባህሉንና የብሄረሰቡን ታሪክ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆን ስለሚገባቸው እነዚህን መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት አላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴን (purposive sampling method) ነው፡፡

### 1.1.4. ጥናቱ የሚያስገኘው ጠቀሜታ

ከላይ በተገለፀው ርዕስ ዙሪያ የሚያጠነጥነው ይህ ጥናት የተቀረጹትን ዓቢይና ንዑስ ዓላማዎች በመተግበር ከተከወነ በኋላ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ እንደየብሔሩና እንደየባህሉ ቢኖርም በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ ከሌላው የተለየ ዘዴ ካለ ልምድን ለማዳበር ይረዳል፡፡
- የሀላባን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ማወቅና የተሻለ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ እንደመነሻነት ያገለግላል፡፡
- በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ የሚገኙት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ለዘመናዊ የፍትህ ስርዓት አጋዥ ሀይል ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማመልከት ይጠቅማል፡፡
- በባህላዊ መልኩ የሚከወኑት የግጭት መፍቻ ስርዓቶች ትልቅ አስተዋጽዖ እንዳላቸው በመረዳት የሚመለከታቸው መንግስታዊ የአስተዳደር መዋቅሮች ለነዚህ የግጭት መፍቻ ተቋማት እውቅና በመስጠት በጥምረት እንዲሰሩ ለማድረግ ያግዛል፡፡

➢ የብሄረሰቡን ባህል ቀርሶና ሰንዶ ለትውልድ  ለማቆየት ይረዳል፡፡

### 1.1.5. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በወጣሁበት ወቅት የሃላባ ልዩ ወረዳ የየቢሮው ሃላፊዎች ለረጅም ጊዜ ስልጠና ወደ ባህር ዳር ሄደው ስለነበር በህጋዊ መንገድ ማለትም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ይገፔ የሄድኩትን ደብዳቤ ለማን እነደምሰጥ ችግር አጋጥሞኝ ነበር፡፡ሌላው ከዩኒቨርስቲው የሚሰጠው ገንዘብ በምሰራው ጥናት ዓይነት ሳይሆን በኪሎሜትር ተለክቶ ስለሆ የተሰጠኝ  የገንዘብ ዕጥረት አጋጥሞኛል፡፡

### 1.1.6.ለችግሮቹ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

የቢሮ ተወካዮችን በማነጋገር  ደብዳቤውን ገቢ ማድረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ተችሏል፡፡ የገንዘብን ችግር በተመለከተ ባለው ግንዘብ አብቃቅቶና ከዩኒቨርስቲው ከተሰጠው ገንዘብ ሌላ ከራስ በመጨመር ጥናቱ ከታሰበው ግብ እንዲደርስ  ተደር

ጓል፡፡

## 1.2 የሀላባ ብሄረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ

### 1.2.1 የሃላባ ብሔረሰብ ታሪክ

የሃላባ ብሔረሰብ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ሥር ከሚገኙ ከ56 በላይ ብሔረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ የሃላባ ብሔረሰብ በዋነኛነት የሚኖረው በሃላባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ሲሆን ከወረዳውም ውጭ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ጋር ተቀላቅሎ በሰላምና በአንድነት የሚኖር ብሔረሰብ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በዋነኛነት የሚኖርበት የራሱ ስነምህዳራዊ አቀማመጥ፣ ቋንቋ፣ የፍልስፍናና የትግል ታሪክ እንዲሁም እምነትና ባሕላዊ መተዳደሪያ ደንብ /ሴራ/ ያለው ነው (የደቡብ ብ/ብ ፕሮፋይል፡ 2004፤ 10)፡፡

የሃላባ ብሔረሰብ በዋነኛነት የሚኖርበት የሃላባ ልዩ ወረዳ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ 8 ልዩ ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ የልዩ ወረዳው ዋና ከተማ ሀላባ ቁሊቶ፣ ከአዲስ አበባ በ315 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ ከክልሉ ዋና ከተማ አዋሳ ደግሞ በ87 ኪሎ ሜትር ሰሜን ምዕራብ የሚገኝ ነው፡፡ የሃላባ ልዩ ወረዳ

በ73 የገጠር ቀበሌያትና በ2 ክፍለ ከተሞች በድምሩ በ75 ቀበሌያት የተደራጀ ሲሆን ወደ 250.000 አካባቢ የሚገመት የሕዝብ ብዛት ይኖርበታል፡፡ ልዩ ወረዳው በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ወይናደጋና ደረቅ ወይናደጋ የአየር ንብረት አለው፡፡ የመሬቱም አቀማመጥ በአብዛኛው ሜዳማ ነው፡፡ ከባሕር ጠለል በላይ ከ1700-2200 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ የቆዳ ስፋቱም 8146 ሄ/ር ይገመታል፡፡ አመታዊ አማካይ የዝናብ መጠን ከ44.6 ሚ.ሜ እስከ 274.6 ሚ.ሜ ይደርሳል፡፡ ዝቅተኛው የሙቀት መጠን 17°c ይሆናል፡፡ በልዩ ወረዳው ከሚገኘው አጠቃላይ የመሬት ስፋት ለእርሻ የዋለው 6671 ሄ/ር፤ ለግጦሽ የዋለው 4438.5 ሄ/ር፤ በደን የተሸፈነ 1731.2 ሄ/ር፤ ሊለማ የሚችል 33000 ሄ/ር ሊለማ የማይችል 953.9 ሄ/ር ሲሆን ሌሎች 4266.06 ሄ/ር ነው፡(የደቡብ ብ/ብ ፕሮፋይል፡2004፣10)፡፡

የልዩ ወረዳው ሕዝብ በዋነኛነት አርሶ አደርና ገጠር ነዋሪ ሲሆን የአጠቃላይ ሕዝቡን 93% ይሸፍናል፡፡ በእምነቱም በሙሉ ማለት ይቻላል የሙስሊም እምነት ተከታይ ነው፡፡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን በግብርና ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከብት፣ ፍየልና በግ የመሳሰሉትን ያረባል፡፡ በእርሻው ዘርፍም በዋነኛነት በርበሬ፣በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴና ሌሎችም ያመርታል፡፡

የሃላባ ህዝብ ባህላዊ አስተዳደር 'ሴራ' እንደሚባል በ2004 ዓ.ም. በድጋሚ በመታተም ለንባብ የበቃው የደቡብ ብ/ብ/ህ ፕሮፋይል ይገልጻል፡፡በተጨማሪም 'ሴራ' የሚባለው ባህላዊ የአስተዳደር ስርአትን ህዝቡ አምኖ እንደተቀበለውና በሱም እንደሚመራ በስፋት አትቷል፡፡ በዚህ ሴራ ተብሎ በሚጠራው ባህላዊ አስተዳደር ስርም የየራሳቸው መጠሪያ ያላቸው የስልጣን አካላት እንዳሉና እነርሱም የመጀመሪው (ኦገቴ) እንደሚባል፤ ይህም አካል የመሰብሰቢያ ቦታው ጥላ ስር እንደሆነ፤ የስብሰባው መሪ (ወማ) እንደሚሰኝ ገልጿል፡፡ ይህ ስርአት ስራ ላይ የሚውለው ደግሞ በሃገር ጉዳይና በህልውና ላይ የሚከሰት ችግር ካለ ብቻ እንደሆነ ያስነብባል፡፡ ሌሎቹ በየጎሳው የጎሳ መሪዎች በብሄረሰቡ አጠራር (ቦኪ ሙሪቾ) በመባል ሲታወቁ ጎሳውን የሚመራው (ደቦ ሙሪቾ) ነው፡፡ እነዚህ በኦጋቴ/ሸንጎ/ ስር ሆነው የቤተሰቡንና የጎሳውን አስተዳደራዊ ስራዎች የሚሰሩ ናቸው፡፡ አጠቃላይ ሸንጎ/ኦጋቴ/ ሲኖር ኦጋቴን የሚመራው (ሲዴ) በመባል የሚታወቀው ጎሳ አባል ነው፡፡የዚህ ምክንያት ደግሞ በብሄረሰቡ የሲዴ ጎሳ አባላት የነቢዩ መሃመድ ዘር ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡የየጎሳዎቹ ጉባዔ የሚመራው

ግን በጎሳ መሪዎች ነው /የደቡብ ብ/ብ/ህ/ ፕሮፋይል፡2004፣ 10፤ አቶ ሀቢብ ፣የካቲት 16፣ 2006 ዓ.ም. ስክርብ ፣31/፡፡

### 1.2.2 የብሔረሰቡ መጠሪያ ስያሜ

የአላባ ብሔረሰብ መጠሪያ ስም "አላባ" ወይስ "ሀላባ" የሚለው ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ አነጋጋሪ ነው፡፡ የሀላባ ብሔረሰብ አባቶች ያለልዩነት የብሔረሰቡ መጠሪያ "ሀላባ" ነው በማለት ይስማማሉ፡፡ በአሁን ወቅት ለብሔረሰቡ መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ ያለው "አላባ" የሚለው ቃል ከጊዜ በኂላ የመጣ እንጂ ከመሠረቱ የብሔረሰቡ መጠሪያ አይደለም፡፡ ስለዚህ የብሔረሰቡ መጠሪያ ስም "ሀላባ" ነው(የሀላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998)፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አነጋጋሪ ጉዳይ ሀላባ የሚለው ስያሜ የተገኘው የቦታ ወይስ የብሔረሰቡ አባት ስም የሚለው ነው፡፡ አንዳንዶች ሐላባ የብሔረሰቡ መጠሪያ የሆነው አሁን ድረስ በባሌ ውስጥ የሚገኝ "ሀላቤ" የተባለ ተራራ ስያሜ ነው፡፡ ብሔረሰቡም በዚህ አካባቢ ለረጂም ጊዜ ሰፍሮ የቆየ በመሆኑ ስያሜውን ያገኘው "ሀላቤ" ከተባለ ተራራ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡ በሌላው ወገን ደግሞ ባሌ ውስጥ የሚገኘው ተራራ ስያሜውን ያገኘው የሀላባ ብሔረሰበ በአካባቢው በመስፈሩ የብሐረሰቡን ስያሜ ነው ለተራራውም የተሰጠው የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው፡፡ የሀላባ ብሔረሰብ አባቶችም ሀላባ የብሔረሰቡ እንጂ የቦታ ስያሜ እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡ ስለዚህ "ሀላባ" የሚለው መጠሪያ የብሔረሰቡ የጥንት አባት መነሻ ስም እንጂ የቦታ ስም እንዳልሆነ በብሔረሰቡ ውስጥ ታምኗል (የሀላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998)፡፡

### 1.2.3 የብሔረሰቡ መገለጫ ባሕሎች

ባሕል ለአንድ ኅብረተሰብ ብሔራዊ ማንነቱን የሚለይበት በጋራ አንድ ላይ ለመኖር ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙቶችን ለአጠቃላይ የእድገት ደረጃው በሚያመች መልኩ የጋራ መግባባትና እምነት ሆኖት የሚጠቀምበትና ያልተጻፈ ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የሚሄድ ሀብቱ ነው፡፡

የሃላባ ብሔረሰብም እንደማንኛውም በሀገራችን ያሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሱ የሆነ ባሕል፣ ታሪክና ቋንቋ ያለው ህዝብ ነው፡፡ አብዛኛው የብሔረሰቡ አባላት

በአንድ አካባቢ ማለትም በሀላባ ልዩ ወረዳ በጋራ የሚኖሩ እንደመሆናቸው መጠን ከጥንት አያት ቅድመ አያት ሲወርዱ ሲዋረዱ የመጡ የራሱ የሆኑና የሚኮራባቸው ባሕሎች አሉት፡፡ (የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998)፡፡ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን እንመለከታለን፡፡

### 1.2.3.1 ኦጋቴ /ባሕላዊ ሸንጎ/

ኦጋቴ የአላባ ብሔረሰብ ባሕላዊ ሸንጎ ሲሆን በባሕሉ መሠረት በአብዛኛው ወንዶች የሚሳተፉበት ሆኖ በተወሰነ ጊዜ ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመም ከመደበኛ ጊዜ ውጭ እየተሰበሰቡ ስለብሄረሰቡ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ በመወያየት ውሳኔ የሚተላልፍበት ባህላዊ ተቁዋም ነው፡፡ ስብሰባው የሚካሄድበት ቦታ ቋሚ አይደለም፡፡ በአብዛኛው የሚካሄደው በየአስራአምስት ቀኑ አካባቢን /ቦታን/ በመቀየር በተረኛው ቀበሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ኦጋቴ የሚሰበሰብበት ቀበሌ ሰዎች የጥላውን ስር የማጽዳት፣ ወማው የሚያርፍበትን ምንጣፍ የማንጠፍ፣ ለተሰብሳቢዎች የሚያስፈልገውን ወጪና መስተንግዶ የመሸፈን ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ባህላዊ የፍትህ መፍቻው ስርዓት (ኦገቴ) የሚካሄደው አካባቢን /ቦታን/ በመቀያየር ቢሆንም የመሰብሰቢያ አውዱ በትልቅ ዋርካ ጥላ ስር ነው(አቶ ሀቢብ ፣የካቲት 2006 ዓ.ም. ስክርብ ፣43)፡፡



ፎቶ .1 የሃላባ ኦገቴ ስብሰባ

የእለቱ የሸንጎ ስርአት የሚጀምረው ሶላት ተሰግዶ፣ ቡና ቀርቦ ከተጠጣና ምርቃት /ዱአ/ ከተደረገ በኋላ ሲሆን ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ለመግባት በሁለቱ ቆርቶዎች አማካይነት የእለቱ አጀንዳዎችና አዳዲስ ጉዳዮችም ካሉ ይፋ ይደረጋሉ፡፡(ቆርቶዎች በሃላባ ብሄረሰብ

የኦገቴ ስርዓት ላይ ከሳሽንም ሆነ ተከሳሽን በመወከል የሚከራከሩ ሰዎች ናቸው፡፡) በዋናዎቹ አጀንዳዎች ላይ ውይይት ከመደረጉ በፊት ዜና /ዱዱቦ/ ያለው እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ በዜናው የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ፣የአጐራባች ብሔረሰቦችና በየአካባቢው የተፈጠሩ ጉዳዮች ካሉ  ይካተታሉ፡፡ ከሸንጐው አባላት መካከልም ሳይቀርብ ቀርቷል ብለው ያሰቡትን ዜና  የማቅረብ መብታቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በኋላ ሀገር ሰላም መሆኑ ተረጋጋጦ በብሔረሰቡ አባባል “አዞሃ ወገሬት” (የወተት ሰላም እንደማለት ነው) ከተባለ በኋላ ነው ወደ አጀንዳዎቹ ውይይት የሚገባው፡፡ ውይይቱ በሁለቱ ቆርቶዎች እየተመራ ከክርክርና ስምምነት ደረጃ የሚደረሰው   ተሰብሳቢዎች በአንደኛው ቆርቶ ሀሳብ ላይ የተቃውሞ ወይም የድጋፍ አስተያየት ካቀረቡ በሁዋላ ነው፡፡ ይህም ጉምጉማ ይባላል፡፡ ቆርቶዎች የተሳሳተ አቅጣጫ ከያዙ ከተሰብሳቢው ማስተካከያ /ሎኮ/ ይቀርብላቸዋል፡፡ በመጨረሻም በውሳኔ ላይ መድረስ የሚቻለው ጉምጉማው /የተቃውሞና ድጋፍ/ ድምጽ ተቆጥሮ አብላጫ ድጋፍ ያገኘው የቆርቶ ሀሳብ የውሳኔ ሀሳብ ይሆናል፡፡ ሸንጐው የሚመራው በወማ /ባሕላዊ መሪ/ ሲሆን ውሳኔውንም በድምጹ መሰረት ማጽደቅ ይጠበቅበታል፡፡

በዕለቱ የሚካሄደው የኦጋቴ ስርአት የጠቅላላ አላባ  ካልሆነም በደቦና በቦኮ ደረጃም ከላይ የተጠቀሰውን ስርአት ተከትሎ ይፈፀማል፡፡ የሚመራውም በደቦ ዳኛና በቦኪ ሙሪቾ ሲሆን ቆርቶዎቹ ባሕሉን ጠንቀቀው የሚያውቁ ሽማግሌዎች ይሆናሉ፡፡ የቦኪ ኦጋቴ ውሳኔን በደቦ፣ የደቦ ኦጋቴ ውሳኔን በሙሉ አላባ ኦጋቴ ደረጃ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ ለውሳኔው አፈጻጸም እንዲመች ሁለቱ ባለጉዳዮች /ከሳሽና ተከሳሽ/ በቅድሚያ ዋስ እንዲጠሩ ይደረጋል፡፡ በዚህም ጥፋተኝነት የተወሰነበትን ወገን ውሳኔ የማስፈፀም ግዴታ የዋሱ ይሆናል፡፡ ለኦጋቴ ውሳኔ የማይገዛና ከስርአት ውጪ የሚሆነውን ወገን ከሌሎች አነሰተኛ ቅጣቶች ጀምሮ ከማኅበረሰቡ እሰከ ማግለል እርምጃ የመውሰድ ባሕል አለው፡፡ የስልጣን ሽግግሩም በዘር ሐረግ የሚተላለፍ ነው(ሃቢብ ፣የካቲት 16፣ 2006 ዓ.ም ፣ ስክርብ  42) ፡፡

የዚህን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ተዋረዳዊ እርከን ጠብቆ ያልከሰሰ ወይም ወደ መንግሥታዊ ተቋማት ቀድሞ ያደረሰ አካል በሃገሬው ሽማግሌዎች ክስ ይቀርብበታል፡፡ ክሱም እኛ የሃገር ሽማግሌዎች እያለን እንዴት ወደ መንግስት አካል ለክስ ሄድክ

በማለት የማር ቅጣት ይጥሉበታል። በአሁኑ ጊዜም ይሄ አካሄድ እየተሰራበት ይገኛል (አምሩላህ፡ 2003. 74)።



ፎቶ 2:

የኦገቴው ገጽታ

## 1.2.3.2. ጋብቻ በሃላባ ብሄረሰብ

### ሀ. ቅድመ ጋብቻ ስርዓቶች

- ***ሃማሞታ***

*ሐማሞታ /ሠርገኛ/፡- በሠርጉ እለት የሙሽራው ጓደኞች ሙሽራውና ሚዜው ሲቀሩ በአቻ እድሜ ላይ ያሉ ዘመድና ወዳጆቹ ተሰብስበው ወደ ሙሽሪት ቤተሰብ ቤት በመሄድ ሙሽራዋን ይዘው ይመጣሉ። ሰርገኞቹ ወደ ሙሽሪት ቤት በሚደርሱበትና ሙሽሪትን ካልወሰድን በሚሉበት ወቅት ከሙሽሪት ጉዋደኞችና የሰፈሩዋ ወጣቶች በበሰበሰ እንቁላል ፣ በኩይሳ ጓልና በኩበት የመደብደብ ፈተና ይደርስባቸዋል። በሙሽሪት ቤተሰቦች ቤትም ለሠርገኞች አተካኖ /ከቆጮና ቡዕላ የሚዘጋጅ/ እና ሻሜታ/ ከበቆሎ ወይም ከዳጉሳ የሚዘጋጅ መጠጥ/ ከማቅረብ የዘለለ ምንም መስተንግዶ አይደረግላቸውም። ምናልባት የሙሽሪት ቤተሰቦች ሀብታሞች ከሆኑ ሰርገኞቹ ወተት ይጠጣሉ።።። መደበኛውና አውዱን የሚገልጸው የሠርግ ድግስ የሚበላው ሙሽራዋን ይዘው ከመጡ በኋላ በሙሽራው ቤተሰቦች ቤት ነው። ሠርገኞቹ ወደ ሙሽራዋ ቤት የሚሄዱት በቀን ወይም ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት መሆን አለበት። ወደ እኩለ ሌሊት ገደማ ወደ ሙሽራው ቤት ሙሽሪትን ይዘው ይመለሳሉ።*

የአላባን ብሔረሰብ ከበርካታ ብሔረሰቦች የተለየ የሚያደርገው ሙሽራዋን ለማምጣት ከሐማምታ /ሠርገኛ/ ጋር ሙሽራውና ሚዜዎቹ አብረው አይሄዱም፡፡ ሰርገኞቹ ሙሽራዪቱን ይዘው እስኪመጡ ድረስ በሙሽራው ቤተሰቦች ቤት ይጠብቃሉ፡፡ ሠርገኞቹም ወደ ሙሽራይቷ ቤት ሲሄዱና ሲመለሱ አላህ ዳኢሞ/ አላህ ዘላለማዊ ነው/ እያሉ ይዘፍናሉ (የሃላባ ሴራ በአል አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998፣19)፡፡

**ለ.የጋብቻ ዓይነቶች**

በሃላባ ብሔረሰብ በርከት ያሉ የጋብቻ ዓይነቶች በተለያየ መልኩ ይፈፀማሉ፡፡

- ❖ **መኢሲሶ/ማኡታ**/፡- የሚባለው ቀጥተኛ ጋብቻ ሲሆን የማፈፀመውም በተለያየ ጥቆማና አጋጣሚ ልጅቷን አይቷት ወይም ቤተሰቦቹ መርጠውለት ወፍ ያይና ወፉ ከተስማማው ሽማግሌ ተልኮ በባሕሉ ተለምኖ በመጨረሻም የልጅቷ ቤተሰቦች ከተስማሙ  አይኗና ጥርሷ ሲቀር ሰጥተናል ክብት አግዱ ብለው የሚፈቅዱበት ነው፡፡ በመቀጠልም ገበራ /ጥሎሽ/ ይከፈላል፡፡ ኒካ /ቀለበት/ ይታሰርና ለሰርጉ ቀን ተቆርጦና ተደግሶ የሚጋቡበት ሰርአት ነው፡፡
- ❖ **ቡሬን አሱ** /ቀበቶ መስጠት/፡- የሚባለው በተለያየ ምክንያት ሰርግ ለመደገስ ካልተቻለ በአጭር ቀጠሮ ብዙ ወጣ ውረድና አጃቢ ወይም ቤተዘመድም ሳይኖር ቅቤ ቀብቶ የመስጠት /የመዳር/ ስርአት ነው፡፡ በዚህ ስርአት የልጅቷ ፍላጐት በአብዛኛው አይጠየቅም፡፡
- ❖ **ሄረና** /ማስኮብለል/፡- የሚፈፀመው ሁለቱ ተጋቢዎች ከቤተሰብ እውቅና ውጭ ተፋቅረው ወይም ልጅቱን በማባበል የሚወሰድበት ስርአት ሲሆን ልጅቷ እጮኛ ያላትም የሌላትም ልትሆን ትችላለች፡፡ ጉዳያቸው የሚፈፀምበት /የሚያልቅበት/ የራሱ የሆነ ስርአትም አለው፡፡
- ❖ **ጉሱ** /ጠለፋ/፡- የሚባለው ልጅቷም ሆነች ቤተሰቦቿ ሳያውቁ መውሰድ(መጥለፍ) ሲሆን ልጅቷ እጮኛ ያላትም የሌላትም ልትሆን ትችላለች፡፡
- ❖ **ወጋ /ቢላ** /በድንገት መጠየቅ/፡- የሚባለው በተለያየ ምክንያት ለሰርጉ ቀጠሮ ተይዞ ወይም በሰርጉ እለትም ሊሆን ይችላል እጮኛውን ያጣ ወጣት ከሷው ቤተዘመድም ሆነ ከሌላ ቤተሰብ በድንገት በመጠየቅ የማፈፀም የጋብቻ ስርአት ነው፡፡ ወጋ/ቢላ የተጠየቀ ቤተሰብ በባሕሉ መሠረት መከልከል አይችልም፡፡

- ❖ **ኣጋ** /የሴቷ ወደ መሄድ/፡-የሚባለው ሴቷ ወንዱን ከወደደችው "ጋጅን ገፍልን ኦጐም ፉሽቶኖቼአ" ወድጄ እዚህ ቤት ገብቻለሁና አታውጡኝ ብላ የወንዱን ቤት ምሰሶ በመያዝ የምትገባበት የጋብቻ ስርዓት ነው፡፡
- ❖ **ረግታ**/ውርስ/፡- የሚፈፀመው ባል ሲሞት የባለ ወንድም ወይም ከቤተዘመዱ የተፈቀደለት ሰው የሟቹን ሚስት የማግባት ስርአት ነው፡፡ ሴቷ ቤተዘመድ መርጦ ያቀረበላትን ወንድ በባልነት ከመቀበል ውጭ የመቃወም መብት የላትም(የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998 ፤ ሼህ ሻፊ ጥር 28፣ 2006 ፣ ስክርብ 31)፡፡

## 1.2.3.3. ግርዛት /ጡርከሙ/

ጡርከሙ ሴራ /የግርዛት ባሕል/ በአላባ ብሔረሰብ የተለመደና የተከበረ ባሕል ነው፡፡ ልጆች አድገው ለአቅመ አዳም በሚቃረቡበት ጊዜ ይገረዛሉ፡፡ ይኸውም ራሳቸውን በደንብ አውቀው ወደ ማሕበራዊ ሕይወት የሚቀላቀሉበት ጊዜ ማለት ነው፡፡ የአላባ ብሔረሰብ በኦገቴ ያሉትንና በአጠቃላይ አስተዳደራዊና ማሕበራዊ ተቁዋማት ውስጥ ያሉትን ሕጐች /ሤራዎች/ ተለማምደው እንዲወጡ ግርዘኞችን በኦገቴ ሴራ ላይ ያስቀምጧቸዋል፡፡ ግርዛት የሚፈፀመው በነሐሴ /መሰሮ/ ወር ነው፡፡ የሚገረዘው ልጅ በግርዛቱ ዋዜማ ላይ ሊነጋጋ ሲል ኮሶ እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ ልጁ ኮሶውን መጠጣቱ እንዳይፈራና ለማበረታታት ሲባል ጓደኞቹ አብረውት ይጠጣሉ፡፡ ለቤተሰቡም የመጀመሪያው የልጃቸው ወግ ማዕረግ ስለሆነ ዘመድ አዝማድ ይጠራል፡፡ እንደየቤተሰቡም አቅም ይደገሳል፡፡በዋዜማውም ሴቶችና ጓደኞቹ ሲጨፍሩ አምሽተው ሲጨፍሩ ያድራሉ፡፡ ግርዛቱ የሚፈፀመው ማለዳ ጐህ ሲቀድ አካባቢ ነው፡፡ ልጁ ወደ መገረዣ ቦታ ማለትም የቤቱ ደጃፍ ላይ ወደ ተዘጋጀለት ከፍ ያለ ቦታ ከመውጣቱ በፊት ከአባቱ ጀምሮ ቤተዘመዶቹ እርፎ /ሽልማት / ሊሰጡት ተራ በተራ ቃል ይገቡለታል፡፡ ይህ ካልተፈፀመ ልጁ ከቤት አይወጣም፡፡ ሽልማቱም በአብዛኛው ከብት /ጊደር/ ሲሆን ፍየል፣ በግ፣ ልብስና የመሳሰሉት ቃል ይገባለታል፡፡ በመቀጠልም ልጁ የመረጠው ወይም አባቱ የመረጠለት አይን ያዥ /የአይን አባት/ በተዘጋጀለት ቦታው በመቀመጥ የልጁን ዓይን በመያዝ ያስገርዘዋል(የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998፤እማም ዝዋር ፣ ጥር 29 2006 ፣ ስክርብ፣ 37 )፡፡

### 1.2.3.4 የለቅሶ ባሕል /አልፌቴ ሴራ/

በሃላባ ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲሞት በአካባቢው የሚገኝ ሕዝብ ሰው መሞቱን የሚያውቀው የለቅሶ ድምጽ ሰምቶ በመውጣት ሲሆን ለሩቅ ዘመድ ግን መልእክተኛ ይላካል፡፡ የተላከው መልእክተኛ መልእክቱን ለማን እንዳደረሰ ተመልሶ ያሳውቃል፡፡ ለለቅሶ የተሰበሰበ ቤተዘመድ /እድርተኛ/ የመጀመሪያ ተግባሩ አስክሬኑን አጥቦ ማንሳትና የቤትና የግቢውን ዝግጅት በማከናወን ወደ መቃብር ቁፋሮ መሄድ ነው፡፡ ቁፋሮ ከመጀመሩ በፊት የሙዋች ወንድም ወይም የቅርብ ዘመድ ቀድሞ በመቆፈሪያው ቦታውን በመውጋት ይጀምራል፡፡ ከቀብር ቁፋሮው በተጨማሪም የከፈን ጨርቅ፣ ቡና፣ ንፍሮና ቂጣ ይዘጋጃል የመቃብር ጉድጉዋዱ እንደደረሰም አስክሬኑ ተከፍኖ የአስክሬን ሶላት ተሰግዶ ይቀበራል፡፡ በባሕሉ አስክሬን ሳይቀበር የሚያያድረው የመቃብር ቁፋሮው አልቆ ለቀብር ዝግጁ ካልሆነ ወይም የማይደርስ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ከቀብር መልስ ለለቀስትኛው ቡና፣ ንፍሮና ቂጣ የሚቀርብ ሲሆን ሟቹ አዋቂና ሐብታም ከሆነ በሬ ታርዶ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ በሰባተኛው ቀን እንጀራ፣ ቂጣና አይብ ተዘጋጅቶ ለቅሶ ያበቃል:::: በለቅሶው ማብቂያ እለት ወይም በማግስቱ ለሟቹ ፀሎት /ሐጃ/ ይደረጋል፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ትምህርት የተማሩ /ኪታበኛኑት/ በሐጃው እለት ቁርአን ይቀራሉ፡፡ ምግብም ተዘጋጅቶ ይበላሉ፡፡ ሟቹ አዋቂ ከሆነ በሰባቱ የለቅሶ ቀናት ምግብ እየተዘጋጀ በየዕለቱ ይበላል፡፡ የሕጻናት ለቅሶ ሲሆን ግን አስፈላጊ አይሆንም፡፡

ለቅሶ ለመድረስ የሚመጣ ሰው ፊቱን ከታጠበ በኋላ ፋቲሐ እንዲባል ይጠይቅና ፈቲሐ ይቀራል፡፡ ለሙዋቹ ቤተሰቦች መጽናናትን/ሰብር/ ይለምንላቸዋል፡፡ ሟች ልጅ ከሆነም የተሻለና የሚያድግላቸውን አላህ እንዲሰጣቸው አዋቂ ከሆነም አላህ የጀነት እንዲያደርገው የቀረ ዘሩን ልጆቹን የተባረኩ እንዲሆኑለት፣ የቡና ቁርሱ ዝግጅት እንዳይከብዳቸውና አልቅሶ የሚያለቅስ፣ የረሳን የሚያስታውስ አላህ እንዳያመጣባቸው ፀሎት /ዱአ/ ያደርጋል፡፡ የሟች ቤተሰብ ተወካይም" ክፉ አይድረስብህ በማለት መልስ ይሰጣል፡፡ በመቀጠልም የቀረበለትን ቡናና ቁርስ ይቀምሳል፡፡ ከዚህ በፊት ግን ቡናና ቁርስ መቅመስ ክልክል ነው፡፡ በመጨረሻም ሲወጣ አንድ ብር እንደቅርበቱ ከዚያም በላይ የእዝን ይሰጥና ይወጣል፡፡ ሟቹ አማቹ ከሆነ የሴት ልጅ ባል ወይም ዘመዶቹ እንደ አቅማቸው የእርድ ከብት፣ እህልና የመሳሰሉትን ለቅሶውን ሊደርሱ ሲመጡ ይዘው ይመጣሉ፡፡

ባሏ የሞተባት ሴት በለቅሶው እለት ቅቤ ተቀብታ ከሴቶች መካከል ትቀመጣለች። ለቅሶው ካለቀ በኋላ ፀጉሯን ትላጭለች። ራሷን ትላጭና ስስ ሻሽ ታስራለለች። እስከ አንድ አመት ድረስም ሌላ ባል አታገባም።

የአለቃቀስ ስርአቱ ወንዶቹ በአርጬሜ ወይም በአለንጋ ትከሻቸውን እየገረፉ በእግርም ሆነ በፈረስ ያሉ ሁሉ ይህንን ድርጊት እየፈጸሙ የሙዋች ቤተሰብ ያሉበት ድረስ ሦስት ጊዜ ተመላልሰው፣ ያለቅሳሉ፣፣ ሴቶች ግን ነጠላቸውን እያራገቡ አልፎ አልፎም ደረታቸውን እየደቁ ገብተው ተቀላቅለው ያለቅሳሉ እንጂ ሦስት ጊዜ መመላለስ አያስፈልጋቸውም(የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998፤ እማም ዝዋር ፣ ጥር 2006 29 ፣ ስክርብ 35)።

## 1.3.የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

### 1.3.1 የግጭት ብያኔ

ግጭት የሰው ልጅ ከሚከሰቱበት የህይወት ገጠመኞቹ አንዱ ነው። በዚህም ከሠው ልጆች መፈጠር ጀምሮ አሁን እስካለበት የስልጣኔ ደረጃ ድረስ ብዙ የጭት ውጣ ውረድ አልፎ እንደመጣ የማይካድ ሀቅ ነው። ይህንንም ሲያጠናክር (Zertman)« … Conflict is an evitable of human interaction, an avoidable concomitant of choices and decisions.» (1999:299) በማለት ይገልፀዋል። በመሆኑም የሰው ልጅ በህብረት በሚኖርበት ቦታ ሁሉ ግጭት እንዳለና በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር እንደሚችልም እንዲሁ አሰፋ አበበ የተባለ አጥኚ ሲያስረዳ "… የግጭት ታሪክ በማህበረሰቡ ውስጥ የህዝቡን ያህል ዕድሜ እንዳለውና አብሮ እንደነበረ፤ አብዛኛውን ጊዜ ግጭቶች ይነሱ የነበርው ተፈጥሯዊ ሀብቶችን (Natural resources) ለመቆጣጠርና የበላይ ለመሆን በሚደረግ ውድድር እንደሆነ ያስገነዝባል። ይህም ውድድር ማህበረሰቡን በፖለቲካ፣ በሀይማኖት፣ በኢኮኖሚና የመሳሰሉት መደቦች በማቡዋደን ጎራ ለይተው እንዲጋጬ እንደገፋፋቸውም ያሳያል። በመቀጠልም ግጭት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚጠላና እንዳይፈጠር የሚፈለግ ቢሆንም ሊጠፋ የማይችልና ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የሚቀጥል እንደሆነ ገልጿል"(አሰፋ፡ 2001)።

እንዲሁም 'Addressing pastoralist conflict in Ethiopia: the case of the Kuraz and Hamer sub- stricts of south Omo zone' ብለው ዮሐንስ ገብረሚካኤልና ሌሎች ባሳተሙት መጽሀፍ ውስጥ ግጭትን ሲገልፁ

> "Conflict is a relationship between two or more parties (individual or groups) who have, or think they have in compatible goals depending on the goals and behavior conflict was further categorized as no conflict, blent conflict open conflict and surface conflict"/Yohannes etal 2005, 40/.

እንደ አጠቃላይ ሲታይ ግጭት በተለያዩ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል ባለ ነገር ማለትም በጋራ የሚጠቀሙት ንብረት ወይም ሌላ ጉዳይ ላይ አለመስማማት በመፍጠር የሚፈጥሩት ጥል ወይም አለመግባባት እንደሆነ ምሁራኑ ይገልፃሉ።

በተጨማሪም የግጭትን ምንነት Boulding ሲያስረዳ ግጭት ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች በሚኖሩበት ማንኛውም ቦታ ሁሉ ሊፈጠር የሚችል ክስተት ነው። "conflict is an activity that found almost in anywhere" (Boulding: 1962,1). በማለት ይገልጻል። እንዲሁም Rugmamu ግጭት የሰው ልጆች በሌሉበትም በእርግጠኝነት ሊፈጠር የማይችል እንደሆነ «To be sure, a conflict does not emerge in vacuum» (Rugmamu: 2000) በማለት ይናገራል።

በእርግጥ የግጭት መኖር የሰው ልጅ ህይወትን የሚቀጥፍ አደጋ ቢሆንም ግን የአስተሳሰብና የእድገት ደረጃውን ሊያሳድግ እንደሚችልም (coser:1970.20) ይገልጻል:: ከዚህም አንጻር የግጭት መኖር ብዙ ጉዳት ቢኖረውም ሰዎችን ሰላም ለመፍጠርና ተባብረው እንዲኖሩ የሚያስችል ልምድን ያስጨብጣልና አንዳንዴ ግጭት ጥሩ ጎን አለው የሚል አንድምታ ይይዛል።

በሌላ ጎኑ ደግሞ ግጭት የሚለውን ቃል አብዛኛው ሰው ሲሰማው በዚያው ቅጽበት የሚፈጠርበት ምስል አሉታዊና አፍራሽ የሆነ ነው።በመሆኑም በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ግጭት ተቀባይነት የሌለውና የልማት ጸር እንደሆነ ነው የሚታወቀው።ለዚህም

ማስረጃው በዓለማችንየተለያዩ ሃገራት ሁለት ጎራ ከፍለው በፈጠሩት ገጭት ምክንያት ጥቁር ጠባሳ ጥለው ያለፉት የዓለም ጦርነቶች ናቸው፡፡የነዚህ ጦርነቶች መኖርም ለሚሊዮኖች ህይወት መጥፋትና ለአያሌ ንብረት መውደም መንስዔ መሆኑ ምስክር የማያስፈልገው እውነት ነው፡፡ በዚህ ዘመንም የዓለም ባንክ ባቀረበው ሪፖርት መሰረት ባለፉት አስርት አመታት በግጭት ምክንያት ከአምስት ሚሊዮን በላይ ህዝብ እንደሞተና ከሀምሳ ሚሊዮን ህዝብ በላይ ደግሞ ከመኖሪያው እንደተፈናቀለ ገልጹዋል(The world bank, 2000)፡፡

## 1.3.2 የግጭት ዓይነቶች

Fisher ግጭቶችን በሶስተ አይነት ይከፋፍላቸዋል፡፡ እነሱንም Economic conflict (የኢኮኖሚ ግጭት)፣ power conflict(የስልጣን ግጭት) እና value conflict(የእሴት ግጭት) በማለት ማህበረሰቡ በነዚህ አማካይነት ግጭት ውስጥ ሊገባ እንደሚችልም ገልጿል፡፡በተጨማሪም እንደ ፊሸር ሁሉ ግጭትን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈለው kreidier ነው፡፡እነርሱንም የሃብት ክፍፍል፣ የፍላጎት አለመስማማትና የእሴት ግጭት ናቸው ይላል፡፡እነዚህንም በትንሹ ሲያብራራ የሃብት ክፍፍል ላይ እኩል ድርሻ ባለመኖሩ የሚፈጠር፣ በፍላጎት አለመጣጣም በኩል ደግሞ የሚፈልጉትን ሊያገኙ በሚጥሩበት ወቅት በሌላ ተይዞባቸው ሲያገኙትና የራሳቸው ለማድረግ በመፈለግ የሚፈጥሩት ግጭት ነው፡፡ እንዲሁም አሴቶቻቸው መገለጫዎቻቸው እንደመሆናቸው መጠን በሌላው ወገን ክብር ሲነፈጋቸውና ዋጋ ሲያጡ ሲያዩ ግጭት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይገልጻል(kreidier.1984)፡፡

በእርግጥ ግጭት ሊፈጠር የሚችለው ውስን ሃብቶችን በባለቤትነት ለመቆጣጠር፣ ለመከፋፈልና ለመጠቀም ከሚደረግ ከፍተኛ ፍላጎት ነው፡፡ ይህም በአብዛኛው ድብልቅ ማህበረሰብ ባለበት ቦታ የበላይ የሆነው ቡድን ያለውን ሃይል ለማሳየትና የራሱን ጥቅም ማስጠበቂያ ዘዴ በመጠቀም ምንነቱንና መገለጫውን ሃይል በሌለው ቡድን ላይ ግፊት በማድረግ ፍላጎቱን ይፈጽማል፡፡ ይህንን ሁኔታም ሲያጠናክር Anstey እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡ "Relative deprivation language over others in a hetrogneous society"(Anstey, 199 29)፡፡

በአጠቃላይ ግጭት  በተለያዩ ምክንያቶች  በግለሰቦችም ሆነ በቡድኖች መካከል የሚፈጠር አለመግባባት እንደሆነ ምሁራኑ ይገልጻሉ፡፡ በዚህም እንደየግጭት ደረጃዎቹ ጉዳቶች ሲክሰቱም ይታያል፡፡

### 1.3.3 በሀገር ውሰጥ የተሰሩ ባህላዊ የግጭት ጥናቶች

በተለያዩ አጋጣሚዎች ባህላዊ የግጭት አፈታትን ስርአትን በተመለከተ ብዙ ጥናቶች ተሰርተዋል፡፡

አጥኚው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ  በግጭት አፈታት ዙሪያ በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ 19 ጥናቶች ዳሷል፡፡ እነዚህም በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚከወኑትን  ባህላዊ የፍትህ አሰጣጥ  በሚያሳይ መልኩ የተከወኑ ናቸው፡፡ ከቀረቡትም የጥናት ጽሁፎች በኦሮሚያ ሶስት፣ በአማራ ክልል ስድስት ፣ በደቡብ ክልል ስድስት ፣ በትግራይ ፣ አፋር ፣ ጋምቤላና ድሬዳዋ በያንዳንዳቸው አንዳንድ ዲማጸች ተሰርተዋል፡፡ ዲማጸቹንም ከብሄረሰቦች አንጻር ስናያቸው ደግሞ አማራ ፣ኦሮሞ ፣ አፋር ፣ ኩናማ ፣ጋሞ ፣ ጉራጌ ፣ወላይታ ፣ሲዳማ ፣ አኚዋ ፣ ኢሳና ሻካቾ  ናቸው፡፤ በየአመቱ ስንከፋፍላቸው ደግሞ በ1997 ዓ.ም. አንድ፣ በ1998 ዓ.ም. ስምንት፣ በ 1999 ዓ.ም. ሶስት፣ በ2001 ዓ፣ም. አንድ፣ በ 2002 ዓ.ም አራት፣ በ 2003 ዓ.ም. አንድ፣ በ2004 ዓ.ም. አንድ ናቸው፡፡ ከላይ የተገለፁት አስራ ዘጠኝ  ጥናቶች በየተጠኑበት ማህበረሰብ ውስጥ ግጭቶች በምን መንስዔነት እንደሚፈጠሩ፣ እነዚህ የተፈጠሩ ግጭቶች እንዴት እንደሚገለፁና እንደሚዳኙ በመጨረሻም ግጭቶቹ ተቀርፈው ሰላም /እርቅ/ የሚፈጠርባቸውን ሂደቶችን በሚያሳይ መንገድ ቀርበዋል፡፡

ከነዚህም ውስጥ  በደቡብ  ክልል ውስጥ ብቻ  የተሰሩትን  ለይቶ ማየት ካስፈለገም

**አብርሃም ታደሰ** በሲዳማ ብሔረሰብ ውስጥ የሚከሰቱትን ቤተሠብ መሀል ከሚፈጠሩ እስከ ነፍስ ግድያ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዴት አንደሚፈቱና እነዚህንም ግጭቶች የሚፈቱ አካላትን እንደ ኦይዱ ሶንጎ" የቤተሰብ ጉባኤ፣ "ጭናንች ሶንጎ" የቤተዘመድ ጉባኤ፣ "አላ ሶንጎ" የመንደር ጉባኤ እና "ሞቴ ሰንጎ" የጎሣ ሸንጎ እንደሆኑ በዝርዝር በመግለጽ በሲዳማ ብሔረሰብ ውስጥ በብዛት  የግጭት አይነቶች የሚከሰቱት በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ እንደሆኑና መንስኤያቸውንና ከላይ

ከተገለፁት ጉባዔዎች የትኛው በየትኛው ጉባዔ እንደሚዳኝ አሳይቷል። /አብርሃም፡ 1999/

**ይልማ ተፈሪ** በወላይታ ብሔረሰብ ውስጥ ባህላዊ የእርቅ ስርዓት የሚከወነው በወንዶች ብቻ ሲሆን፣ ይህም በሶስት ዓይነት ባህላዊ ተቋማት እንደሚከወን ይገልፃል። እነዚህም ጪመታ /ሽምግልና/ ጨጫ ጨቻ /የደም ካሣ የሚያስከፍል የዕርቅ ስርዓት/ እና ጫቆ /መሀላ/ እንደሚባሉ በጥናቱ ላይ አሳይቷል። የነዚህንም ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ሚና ሲገልጽም ጪመታ /ሽምግልና/ በቤተሠብ አባላት፣ በባልና ሚስት፣ በጓደኛሞች፣ በጎረቤታሞች፣ በጠለፋ ምክንያት ወዘተ… የሚከሠቱ ግጭቶችን ለመፍታት ስራ ላይ እንደሚውል ይገልፃል። ጫቆ ደግሞ በጎሣ ግጭት የሚከሰት ቅራኔን ለመፍታት የማገልገል ስራ ላይ ሲውል፤ በብሔረሰቡ አባላት መሀል በነፍስ ግድያ ምክንያት በሚከሰቱ ግጭቶች መፍትሄ የሚገኝለት ባህላዊ ተቋም ደግሞ ጨጫጨቻ እንደሆነ በመግለጽ ጥናቱን ሰርቷል። /ይልማ 1998/

**አንዱአለም አባተ** በመኤኒት ብሔረሰብ ውስጥ ያለውን ባህላዊ የግጭት አፈታት በዋናነት ትኩረት በማድረግ ለማየት ሞክሯል። ባህላዊ የግጭት ሥርዓቱ ግጭቶችን እንዴት እንደሚፈታ፣ በማን እንደሚፈታና የአፈታት ሒደቶችን አሳይቷል። በብሔረሰቡ ውስጥ የሰው መግደል እርቅ ስነስርዓት ሂደት አሻ በመክፈል፣ እንዲሁም የመድፈር እርቅ ሥነ ሥርዓት ሂደት ደግሞ በማጠብ እንደሚፈታና የድንበር እርቅ ሥርዓት ሒደትም ቀርበውበታል። /አንዱአለምፀ 2004/

**የወንድወሰን አውላቸው** "የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት" በሚል በሠራው የመመረቂያ ጽሁፉ ትኩረቱ ያደረገው የግጭት ምክንያቶች፣ የግጭት አይነቶተና የግጭት መፍትሄዎችን ማመላከት ነው። በአካባቢ ድንበር መጋፋት፤ ስርቆት፣ ቤት ማቃጠልና ንብረት መዝረፍ የግጭት መነሻ ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጿል። የግጭት ዓይነቶቹ የቤተሠብ፣ የልጆች ወይም የጎሣ ሲሆኑ ለነዚህ ግጭቶች ማስወገጃ መፍትሄ የሚያመጡ ባህላዊ ተቋማት እንዳሉና እነሱም ስምንት እንደሆኑም አሳይቷል። እነዚህም በመዋቅራዊ አስተዳደር ከታች ወደላይ ሲቀመጡ ቤተሠብ፣ ቤተዘመድ፣ ጎሣ፣ አካባቢ፣ ጀፎሮ፣ ቃያ፣ ክፍለ ጉራጌና የጆካ እንደሚባሉ በጥናቱ አብራርቷል /የወንድወሰ፡1998/

**ተመስገን ምን ዋጋው** "ሀገረሰባዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በዶኮ ጋሞ ብሔረሰብ" በሚል በሠራው ጥናቱ በብሔረሰቡ ዋና ዋና ግጭቶች የሚነሱባቸውን ጉዳዮች ሲያብራራ ለነፍስ ግድያ፣ በጎሳ፣ በድንበር፣ የሰው ሚስት በመድፈርና በዘመዳሞች መሀል በሚፈፀም የግብረ ስጋ ግንኙነት አማካይነት ነው፡፡ እነዚህን ግጭቶች የሚፈቱት ከእግዚአብሔር ፀጋ እንደተሰጣቸው በሚታመንባቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ነው፡፡ እነዚህ ሹማምንትም እርቁን የሚያካሂዱት በአደባባዮች ላይ እንደሆነ ገልጿል፡፡ ግጭቶችንም ለመፍታት ስምንት ሀገረሰባዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት እንዳሉና እነዚህም ማካ፣ ጌቃ- አቃ፣ ካሬ፣ በላና ዶና፣ ኤራርሶ መሆናቸውን አስፍሯል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ከተጻፉት ጥናቶች ውጭ በእንገሊዝኛ ቋንቋ በ2001 ዓ.ም. በቀረበውና ስዩም መንግስቱ ‹*Natural Resources Competition and Inter ethnic Relation a Case Study of Arsi Oromo and Alaba ethnic group in Alage, south central Ethiopia.* በሚል ርዕስለትለጸኛ ዲግሪ ባካሄደው ጥናት ላይ በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል በተደጋጋሚ ግጭት ይነሳ እንደነበር ገልጿል፡፡ የግጭቶቹን መንስዔዎችና እነዚህን ግጭቶች ለማስወገድ የሚከወኑ ባህላዊ ስርዓቶችንና ሂደታቸውን አሳይቷል፡፡ ስዩም በአርሲ ኦሮሞዎችና በአላባ ብሄረሰቦች መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ለመፍታት የሚሰየሙት ሽማግሌዎች ከሁለቱም ብሄረሰቦች የሚወከሉና ስርዓቱን ጠንቅቀው የሚያውቁ እንደሆኑ አብራርቷል፡፡ ክዚህ በተጨማሪ በጥናቱ ላይ በአርሲ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ሴቶች ምንም ሚና እንደሌላቸው መግለጹና የግድያ ወንጀልን ዕርቅ ሲፈጽሙ ጉዳ መደረጉ እኔ ከማጠናው የሃላባ ብሄረሰብ የግጭት አፈታት ስርዓት ጋር ይመሳሰላል፡፡ በሃላባ ብሄረሰብ በሚከወነው የግጭት አፈታት ስርአት ላይ የሴቶች ሚና የለም፡፡ በመሆኑም ባህላዊው ክዋኔያቸው ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በአርሲ ኦሮሞ ማህበረሰብ እቤት ውስጥ ግጭት ቢፈጠር በሴት ልጆች መሃል የተፈጠረን ግችት እናት እነደምትፈታው፤ በወንድ ልጆች መካከል የሚፈጠረውን ግጭት ደግሞ አባት እንደሚዳኝ፤ እንዲሁም በሁለት ጎሳዎች መሃል የሚነሳን ጠብ ሌላ ሶስተና ጎሳ እንደሚፈታ በጥናቱ አስፍሯል፡፡ በሃላባ ኦገቴ ከቤት ጀምሮ በየደረጃው ለሚነሱ የግጭት ዓይነቶች በየደረጃው ያሉ ተዋረዳዊ መዋቅሮች ይዳኙታል እንጂ ከኦገቴው ውጪ ሌላ ክፍል አይፈታውም፡፡ ይህም ማለት በሃላባ ብሄረሰብ ውስጥ ሁለት ጎሳዎች ቢጋጩ ሌላ ጎሳ ገብቶ ችግራቸውን

አይቀርፍም። በዚህ ደረጃ በብሄረሰቡ ውስጥ ግጭት ከተነሳ የሃላባ ኦቴ( ሃላቢ ኦገቴ) ነው ጉዳዩን አይቶ ችግራቸውን የሚያቃልልላቸው። በዚህ ደግሞ ልዩነት አለባቸው።

ከላይ በአማርኛ የተሰሩትም ሆነ በአርሲ ኦሮሞና በሃላባ መካከል የተሰራው ጥናቶች ከኔ ጋር የሚያለያያቸው ደግሞ በሀላባ ብሄር ተሙዋጋቾች(በዳይና ተበዳይ) ለባህላዊ የዳኝነት ስርአት በሚቀርቡበት ወቅት እነሱ ስለራሳቸው የሚከራከሩ ሳይሆን ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ መሪ /ኦገቴ/ በሚያቆምላቸው የህግና ንግግር አዋቂዎች /ቆሮቶዎች/ አማካይነት ፍትህ የሚያገኙበት መሆኑ ነው። ይህ ማለት በብሄረሰቡ ውስጥ ባህሉንና ባህላዊ ስርኣቱን ጠንቅቀው የሚያውቁና ይህንንም ጥሩ አድርገው በንግግር ሊያቀርቡ የሚችሉ ሰዎችን በመምረጥ ለተሙዋጋቾቹ እንዲከራከሩላቸው በማድረግ የሙግቱን ሂደት የሚያስፈጽሙበት ሁኔታ ነው።

በተጨማሪም የሃላባ ብሄረሰብን ባህላዊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን ብሄረሰቡ ከማን ጋር በቋንቋ በደም እንደሚቀራረብ ለማሳየት **ፍሬህይወት አድነው** በ1997 ዓ. ም. “ከምባቶመት” በሚል ርዕስ የከምባታ ብሄረሰብ የፎክሎር ለውጥ በማስመልከት በሰራው የመመረቂያ ጥናቱ ላይ በአጠቃላይ የተነሳበት ጉዳይ የከምባታ ፎክሎር ለውጥ ጉዳይ ቢሆንም ከምባታ ከአጎራባች ህዝቦች ጋር ያለውን የደም፣ የቋንቋና ሌሎች ግንኙነት አንስቶ ከሃላባ ፣ ከዶንጋና ጠንባሮ ብሄረሰቦች ጋር ያለውን ዝምድና ከቋንቋ ባለፈ በከምባታ ስም በመጠራት በአካባቢው ይኖሩ እንደነበር ይገልጻል።

እንዲሁም **ተስፋዬ ሃቢሶ** ሃላባ ሃዲያን በመጠጋት በሃዲያ ቡድን ውስጥ ይኖር እንደነበር በግልጽ አስቀምጧል። ከማሂኮ ተቀውሞ ውድቀት በኋላ ሃላባ ከሃዲያ ጥገኝነት በመውጣት መኖር እንደጀመረና ነገር ግን በክርስትያን መንግስት ስር እንደነበረ አስፈሯል። በኋላም ፈርናንዴዝ የተባለ ፖርቹጋላዊ በ1613 ሀላባን ሲረግጥና ሃሊኮ የተባለውን የእስልምና መሪ ካገኘው በኋላ ከኢትዮጵያ የቁጥጥር በተወሰነ መልኩ ነጻ ሆኖ እንደቆየ አስቀምጧል። በዚህም መሰረት የሃላባ ብሄረሰብ ከከምባታ ፣ ጠምባሮና ዶንጋ ጋር የበለጠ ትስስር ያለውና በአንድ ዞን ውስጥ የቆየ ቢሆንም ከ1994 ዓ. ም. ጀምሮ ራሱን በማስተዳደር ልዩ ወረዳ ሊሆን ችሏል።

# 2. ግጭት፣ የግጭት አፈታት ስርዓትና ተቋማት በሀላባ ብሄረሰብ

## 2.1 የግጭት ፅሳቤ በሀላባ ብሄረሰብ

የሀላባ ብሄረሰብ ኣባላት እንደየመረዳት አቅማቸው ለግጭት ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ በብሄረሰቡ ቋንቋ ግጭት (ጎጨንሻ) ሲባል ጠብ ደግሞ (ቢታት) እንዲሁም ጦርነትን (በገዙ/ኦለንሻ) በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም በተለያየ መልኩ ይጠሩ እንጂ ጽንሰ ሃሳባቸው አንድ ነው፡፡ ሁሉም ባለመግባባት ምክንያት የሚፈጠሩና ለሰው ልጅ ህይወትና ለንብረት መጥፋት ምክንያት የሆኑ ጎጂ ክስተቶች ናቸው፡፡ (አቶ አምባዬ፡ የካቲት 2፣ 2006 ዓ.ም.፣ ስክርብ፣41)

"ግጭት አለመግባባት ነው፡፡ በድንበር የሚነሳ፣ በልጃገረድ ጠለፋ፣ በእሳትና በሌላ ምክንያት ለፈጠር የሚችል ክፉ ነገር ነው" (አህመድ መሶሮ  መጋቢት 4፣ 2006 ዓ.ም ስክርብ፣ 25.)፡፡

ግጭት እንደ ሀላባ ብሄረሰብ በማህበራዊ ህይወቱ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ማለትም እንደ የግጦሽ መሬት፣በድንበር ማለፍና አልፎም ማረስ ፣በንብረት ስርቆትና በመሳሰሉት ምክንያቶች አለመግባባት ሲፈጠር የሚከሰት ችግር ነው፡፡ ለምሳሌ የሀላባ ህዝብ ጥምር ግብርና የሚጠቀም ማለትም ሰብል በማምረትና ከብት በማርባት የሚተዳደሩ በመሆናቸው በተለየ መልኩ በነዚህ እሴቶቻቸው የሚመጡባቸው አለመግባባቶች ግጭት ይፈጥሩባቸዋል(አክሊሉ፡ ጥር 2006)፡፡  በተጨማሪም በሴት ልጅ ጠለፋ፣ በቂም በቀል በመነሳት የመኖሪያ ቤትን በእሳት ማቃጠል ትልቅ ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ (እማም ሁልጫፎ፡ ጥር 29፣ 2006 ዓ.ም.)

በአጠቃላይ በሀላባ ብሄረሰብ በግጭት ዙሪያ ያለው እሳቤ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም አለመግባባት የሚፈጥረውና በአጭሩ ካልተቀጨ  እስከ ህይወት መጥፋትና አካል ማጉደል እንዲሁም ንብረት ማውደምን የሚያስከትል ጎጂ ክስተት እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የሚፈጠረው ግጭት ብዙ ጉዳት ያለው መሆኑን በመረዳት  እንደ ሌሎቹ የሀገሪቱ ብሔሮች ሁሉ የሀላባ ብሄረሰብም ግጭት ከተፈጠረ በኋላ ጊዜ ሳይሰጥ በባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቁዋማቱ እንደየደረጃው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ዕርቅ

የመፍጠር ስራውን ይፈጽማል፡፡ በዋናነት በሀላባ ብሔር ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ችግር የሚፈታው ተቋም 'ኦገቴ' ሲሆን በየደረጃቸው ግን 'ቦኪ አገቴ' የቤተሠብ ሽንጎ፣ 'ዶቦ አገቴ' /የጎሳ ሽንጎ/ና 'ሀላቢ ኦገቴ' (የሀላባ ሽንጎ) በመባል ይታወቃሉ፡፡/አምሩላህ 2003፡ 73/

በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ በዋናነት የግጭት መንስኤ ሆነው የሚከሰቱት የግጦሽ መሬት ጥያቄ፣ በዝርፊያና በጋብቻ ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ናቸው፡፡በመሆኑም ከዚህ ቀደምም ሆነ አሁን ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚፈጠረው ግጭት ከሁለቱም ወገን በተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት በሰላም ይፈታል፡፡ /የደቡብ ብ/ብ/ህ/ፕሮፋይል 2004፡ 10/

የሀላባን ብሔሰብ የግጭት አፈታት ከሌሎች ብሔሮች የግጭት አፈታት የሚለየው በብሔሩ ውስጥ ባሉ አባላት ከላይ በተገለፀው መልኩ ግጭት ሲፈጠርና በባህላዊ የሽምግልናው /የዳኝነቱ/ ወቅት ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ በዚያ ሽንጎ ላይ ሲገኙ ምንም አይነት ንግግር ሊያደርጉ አለመቻላቸው ነው፡፡ ይልቅስ በአካባቢው የታወቁ ንግግርና ህግ አዋቂዎችን ኦገቴው ያዘጋጅላቸውና እነርሱ ይከራከሩላቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች በብሔረሰቡ 'ቆሮቶ' በመባል ይታወቃሉ፡፡ ቆሮቶዎች የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ጠበቆች አይደሉም፡፡ ከጠበቃ የሚለያቸው ባለጉዳዮቹ ገንዘብ ከፍለው ወይም መርጠው የሚያመጧቸው ሳይሆኑ ኦገቴው ራሱ ስለሚያዘጋጃቸው ነው፡፡ /አምሩለህ 2003፡ 78/

## 2.2 የሀላባ ብሔረሰብ ውስጣዊና ውጫዊ ግጭቶች

### 2.2.1 የቤተሰብ አለመግባባቶች

በዚህ ደረጃ የሚፈጠሩት ግጭቶች ብዙውን ጊዜ ከቤት አይወጡም፡፡ በሀላባ ብሄረሰብ በብዛት የቤተሰብ ግጭት የሚፈጠረው ልጆች ለአቅመ አዳም ወይም ለአቅመ ሄዋን ደረሰው ራሳቸውን የሚችሉበት መሬትና ንብረት በሚጠይቁበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዕድሜ ጋር ተያይዞ ታናሽ ለታላቅ አልታዘዝ የሚልበት አጋጣሚ ሲፈጠር ነው፡፡ ውርስም አንዱ የግጭት መንስዔ ነው፡፡

ወንድ ልጆች ለአካለ መጠን የደረሱ ከሆነ ከወላጅ አባታቸው መሬት ተቆርሶና የቁም ከብቶችም ተሰጥቷቸው ለወደፊት የሕይወት ጉዞአቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለማመቻቸት

እንደሚሰጣቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ሁኔታ ካልተሟላላቸው ከወላጅ አባታቸው ጋር ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ እንዲሁም ወንድ ልጆችንና ሴት ልጆችን ርስበርሳቸው ግጭት ውስጥ የሚከታቸው ሌላ ቁልፍ ጉዳይ ደግሞ እናትና አባታቸው በሞት የተለዩ ከሆነና የሀብት ንብረት ክፍፍል ፍትሃዊ ካልሆነና አድሎ ያለበት እንደሆነ ከባድ ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በተጨማሪ ወንድ ልጆችን ለብቻቸው የሚያጋጫቸው ሌላ ጉዳይ ደግሞ አንዱ በሞት ቢለይ የሟቹን ሚስት ማን ይውረስ? የሚል ጥያቄ ይሆናል፡፡ እንደ ባህሉ ከሆነ ከወንድማማቾች መካከል የሟች ወንድምን ሚስት መውረስ ያለበት ታላቅ ወንድም ሲሆን ይህንን ባህላዊ ስርዓትን ተላልፎ ታናሽ ወንድም የወረሰ ከሆነ ግጭቱ ከበድ ያለ ይሆናል፡፡ ታናሽ ማግባት ያለበት ታላቅ ወንድም ከአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን መርቆ ከሰጠው ብቻ ነው (አቶ እንዳለ፤ መጋቢት 4፣ 2006 ዓ.ም ፣ስክርብ)፡፡

ሴት ልጆችም በተመሳሳይ መልኩ ለማግባት ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት የተለያዩ ስጦታዎች ተሰጥቷቸው ይዳራሉ፡፡ የሚሰጡዋቸው ስጦታዎች ሙሉ ካልሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ለምሳሌ፡ አንዲት ልጃገረድ ስታገባ ከወላጆቿና ከቅርብ ቤተ ዘመዶቿ በራሷ ምርጫ የቁም ከብት ስጦታ ይበረከትላታል፡፡ በወላጅ እናቷ ደግሞ ሙሉ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ይሟላሉ፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን እኔ ከማን አንሼ ነው ባዶ እጄን የምዳረው በማለት ከወላጆቿ ጋር ቅሬታ ውስጥ ትገባለች፡፡ በአግቢው ቤተሰብ ዘንድም ሙሉ ስጦታ ይዛ የማትሄድ ከሆነ ባዶ እጇን የመጣች ተብላ ተገቢ ክብር፣ ዕውቅናና ተቀባይነት ሊነፈጋት ይችላል፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በቤተሰብ ውስጥ አለመግባባት ይፈጠራል፡፡ በዚህ መልኩ በቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩትን የግጭት ዓይነቶች ቀላል ተብለው ስለሚታመኑ ቤተሰብ ራሱ በመጀመሪያ በጉዳዩ ላይ ተነጋግሮ የሚፈታበት ባህል አለ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ችግሮቹ በቤተሰብ የማያልቁባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ በዚህ ወቅት ነገሩ ርቆ ሳይሄድ የአካባቢው የሀገር ሽማግሌዎች ቤተሰቡን ግጭት ውስጥ ያስገባውን ጉዳይ መርምረው በቤተሰብና በቤተዘመድ ኦገቴ /የእርቅ ሂደቶች/ ይፈቱታል፡፡ ባህላዊ ሥርዓቱን የተላለፈ ወገንም በምክርና በተግሳጽ እንዲሁም በኮርማ እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ አለመግባባቶች በጊዜ መፍትሔ ካልተበጀላቸው ወደ አላስፈላጊ ግጭቶች ውስጥ የሚከቱ ይሆናሉ፡፡ እንዲህ አይነቶቹን አለመግባባቶች የሀገር ሽማግሌዎች ወደ ባሰ ደረጃ እንዳይደርሱ ሁልጊዜ እየተከታተሉ በዕንጭጩ ይፈቷቸዋል፡፡ ከላይ ከተገለጹት

በተጨማሪ በቤተሰብ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶች ሲፈጠሩ ይስተዋላል፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት ሼህ ሻፊ ገጠመኛቸውን እንደሚከተለው ይነግሩናል፡፡

**ተረክ 1** ሪባቶ አህመድ የተባለ ወጣት ሃሙስ ገበያ ውሎ ወደ ቤቱ ሲመለስ የአካባቢው ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ አየለች ለዕመንጎ በጀርባቸው ከተሸከሙት ሸክም በተጨማሪ በእጃቸው ያንጠለጠሉት ዘንቢል ከብዷቸው እንዲያግዛቸው ቢጠይቁት"እኔ የራሴም ሸክም ከብዶኛል፣ ከዚህ በላይ አልችልም" በማለት መለሰላቸው፡፡ በዚህ መልሱ የተበሳጩት ወ/ሮ አየለች አቅማቸው የደከመ ሰዎችን ቢያግዝ እንደሚመረቅና ወደፊት ህይወቱ የተባረከ እንደሚሆን በመናገር አሁን አደግኩ ብለህ ነው መታዘዝ እምቢ ያልከው ሲሉት "እንደውም እኔ የርሶ አሽከር አይደለሁም ላግዞትም ግዴታ የለብኝም" ብሎ ስለመለሰላቸው ተበሳጭተው በቤተዘመድ ገባዔ ላይ ከሰሱት፡፡ ጉባዔውም ላይ ቀርቦ ሪባቶ ጥፋቱን በማመኑ በወደፋ ተቀጣ፡፡ ወደፋ የማር ቅጣት ነው፡፡አንድ እንስራ ማር እንዲያመጣ ታዘዘ፡፡ በእርቁም ዕለት ሪባቶ ማሩን ይዞ ተገኘ፡፡ ግማሹን ማር በጥብጦ ብርዝ በማድረግ በኩባያ ለተሰብሳቢዎቹ አጠጣ፡፡ የቀረውንም በኮባ ቅጠል በማድረግ እንዲሁ አዳረሰ፡፡ከዚያም ሙሪቸው ከተበጠበጠው ማር በመጎንጨት ሁለቱ ተጣዮች ላይ ተፍተዉባቸው የእርቁ ስነስርኣት ተፈጽሙዋል(ሻህ ሺፋ የካቲት 3፤ 2006 ዓ. ም፣ ስክርብ፣33)፡፡

## 2.2.2. የጉረቤት ግጭቶች

የሰው ልጅ በየዕለቱ በሚያደርጋቸው የሕይወት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከመኖሪያ ቤቱ ጀምሮ እስከ አጎራባቹ በባህላዊ፣ በማህበሪዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ እርስበርስ መገናኘቱ የማይቀር የተፈጥሮ ግዴታው ነው፡፡ በዚህ የርስበርስ ግንኙነት ውስጥ መልካም ግንኙቶች እንደመኖራቸው ሁሉ አለመስማማቶችም እንዲሁ ይኖራሉ፡፡ በሀላባ ብሔረሰብም ጎረቤትን ከጎረቤቱ የሚያገናኙት ዘርፈ ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ በዋናነት የመገልገያ ቁሳቁሶች በጋራ የመጠቀምና የመዋዋስ፣ በአዋሳኝ መሬቶች አካባቢ የግጦሽ ሣር አጠቃቀም፣ የእርሻ ማሳዎችን አንድ አካባቢና በኩታ ገጠም መጠቀምና የድንበር መገፋፋት፣ የቤት እንስሳትን ቀላቅሎ ማሰማራትና በጋራ በአንድ ኩሬ ወይም ወንዝ መጠቀም፣የአንዱን ንብረት ያለፈቃድ መጠቀምና መውሰድ የመሳሰሉት ቁልፍ

ግንኙነቶች ናቸው፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ሕዝቡ በየዕለቱ በሚያደርገው የርስበርስ ግንኙነቶች በንብረት አጠቃቀም፣ በተፈጥሮ ሀብትና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች በልጆች፣ በሴቶችና በአዋቂ ወንዶች መካከል ግጭቶች ይፈጥራሉ፡፡ በተለይ በድንበር ምክንያት የተፈጠረባቸውን አጋጣሚ ገራድ ሙንዲኖ ሲናገሩ፡-

ተረክ.2 እኔ ቤተሰብ ውስጥ በድንበር በሆነ ወቅት ተጣልተው ነበር፡፡ጥሉም ጠንከር ያለ ነበር ፡፡ ይህንን ግጭት ለመቅረፍ የአካባቢው ሽማግሌዎች ድንበራቸውን ለመከለል ሳምንት ሙሉ ከተከራከሩ በሁዋላ በመስማማት ጋሻ ሙሉ መሬት በቅንጭብ ሲከልሉ ዋሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ ከልለው ከሄዱ በሁዋላ እረኝነት የዋለና ድንበሩ ሲካለል ያልነበረ ወጣት መጣና የተከለለውን ሲያይ ተናዶ ሽማግሌዎቹ ሲተክሉ የዋሉትን ቅንጭብ ነቃቅሎ ጣለው፡፡በማግስቱ ሽማግሌዎቹ ወደቦታው ሲሄዱ የተከሉት ቅንጭብ ተነቃቅሎ አገኙት፡፡ሰዎችንም ሲጠይቁ ሁኔታውን ነገሩዋቸው፡፡ ሽማግሌዎቹም በጣም አዘኑ፡፡በቀጥታ ወደ ነቀለው ልጅ እናት ቤት በመሄድ "ልጅሽ ያደረገውን አይተሻል ብለው በመጠየቅ ልጅሽ እኛ የተከልነውን እንደነቀለ እኛም እሱን ነቅለነዋል "ብለው ሄዱ፡፡ ሽማግሌዎቹ ሄደው ብዙም ሳይቆይ ልጁ እዚያው እረኝነቱ ቦታ ላይ በድንገት ሞቶ አስክሬኑን ተሸክመው አመጡት(ገራድ ሙንዲኖ ፡ ጥር 28፣2006 ዓ.ም. ፣ስክርብ፣18)፡፡

## 2.2.3. የጉሣዎች እና የአጉራባች ሕዝቦች የርስ በርስ ግጭት

የሃላባ ብሄረሰብ ከሃዲያ፣ ከከምባታ፣ ከስልጤና ከአርሲ ኦሮሞ ጋር በተለያ አቅጣጫዎች ተዋስኖ የሚኖር ህዝብ ነው፡፡ ስለሆነም ልክ እንደ ጉርብትና የግጭት ዓይነቶች ሁሉ በሀላባ ብሔረሰብ ጉሣን ከጉሣ፣ የሃላባን ጉሣ ከሌላ ጉሣ እንዲሁም አጎራባች ህዝቦችን አለመግባባት ውስጥ የሚከቱ ቁልፍ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ማለትም የውሃ፣ የግጦሽ ሣር፣ በድንበር አካባቢ የሚገኘውን መሬት የይገባኛል ጥያቄዎች፣ የመኖሪያ ቤቶች በቂም በቀል ተነስቶ መኖሪያ ቤት ማቃጠል፣ እንስሳትን አለአግባብ የእርሻ ቦታዎች ውስጥ መልቀቅ፣ የሴት ልጆች የጋብቻ ሁኔታና የቤት እንስሳት ስርቆት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የነዚህ

ዓይነቶቹ አለመግባባቶች ከባድና አደገኛ የግጭት አይነቶች ተብለው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በዚህ መልኩ የሚቀሰቀሱ ግጭቶች በጊዜና በሰዓቱ መፍትሔ ካላገኙ አብዛኞቹ የርስበርስ ግድያ ውስጥ የሚከቱ ናቸው፡፡

በሀላባ ብሔረሰብ የቤት እንስሳት የግጦሽ ሣር ፍለጋ ወደ ሌላ ግለሰብ የግጦሽ መሬት ወይም ድንበር አልፈው ወደ ሌላ ብሔረሰብ ስለሚገቡ ጉዳዩን በትዕግስትና በማስተዋል ሁለቱም ወገኖች የማይፈቱ ከሆነ ርስበርስ ከፍተኛ ፍጭት ውስጥ ይከታቸዋል፡፡ በብሔረሰቡ እያንዳንዱ ግለሰብ የራሱ የሆነና የተከለለ፣ ለቤት እንስሳቱ የግጦሽ ሳር ስፍራ ስላለው ከበቶቹን ወደ ሌላ ግለሰብ ክልል መልቀቅ የለበትም፡፡ ፡፡ ለጋራ ጥቅም የተከለለ ግጦሽን መጠቀም እንኳን ቢያስፈልግ በማስፈቀድ በቻ መጠቀም ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የውሃ አጠቀቀምን በተመለከተ ቢቻል ሁሉም የየራሱ ኩሬ ቢኖረው ይመረጣል፡፡ ካልሆነ ግን እያንዳንዱ ሰው በጋራ የሚጠቀምበትን ኩሬ በጥንቃቄ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ያለ ጠባቂ የቤት እንስሳቱን ወደ ኩሬ አለመልቀቅ፣ ሲያጠጣም በኩሬው ዙሪያ በተዘጋጀው ማጠጫ ብቻ እንዲጠቀም ባህሉ ያስገድደዋል፡፡ እነዚህን ባህላዊ የአጠቃቀም ስልቶችን አልፎ አልፎ የማይከተሉ ግለሰቦች ይኖራሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ በተለያዩ ጊዜያት ግጭቶች ይከሰታሉ፡፡ ቃለ መጠይቅ ባደረግኩለት ወቅት አቶ አህመድ መሶሮ የሚከተለውን ገጠመኙን ነግሮኛል፡፡

**ተረክ 3.** በ2000 ዓ.ም  አካባቢ ሀላቦችና ኦሮሞዎች በድንበር ምክንያት ግጭት ፈጥረው እስከ ጦርነት ደረጃ ደርሰው ነበር፡፡በዚህም ወቅት ከሁለቱም ወገኖች የብዙ ሰዎች ህይወት ጠፍቶ ነበር፡፡ በሁዋላም ይህንን ግጭት ለመፍታት ከሁለቱም ወገኖች የተውጣጡ ሽማግሌዎችን በማሰባሰብ ሰላም ተፈጥሮ ነበር፡፡ በወቅቱም ከሁለቱም ወገኖች በዳይም ተበዳይም በአውዱ ተገኝተው እርቅ ስነስርኣት ፈጽመው ነበር፡፡ በስነስርዓቱም ላይ የገዳይ ወገኖች ለሟች ወገኖች ካሳ ከፍለው ነበር፡፡እኔ በወቅቱ የተገኘሁት አንድ ዘመዳችን የሆነች ሴት ባሉዋ ተገድሎባት ለእርቅ በመጣችበት አጋጣሚ ነው፡፡ የዘመዳችንን ባል የገደለው ሰው በቦታው የተገኘው ትልቅ ቡሉኮና ጥቁር በግ ይዞ ነበር፡፡ ያመጣውን በግና ቡሉኮ በመያዝ ወደኛ ተጠጋ፡፡ከዚያም ለሟች ሚስት ቡሉኮውን አለበሳት፡፡ ጥቁሩን በግም ከኛ ጋር በመተጋገዝ ጣልነውና አረደው፡፡ ወዲያው

አንጀቱን በማውጣትና በመግመድና እንደሰንሰለት በማጠላለፍ የሚች ሚስትና ገዳይ ጫፍና ጫፉን በመያዝና መሃላ በመፈጸም እርቁን አጠናቀዋል፡፡ በእለቱም  እንደዚህ ዓይነት ብዙ የእርቅ ስነስርዓቶች ተፈጽመዋል(አህመድ መሰሮ ፡ መጋቢት 4፣ 20060.ም. ፣ስክርብ፣25)፡፡

## 2.2.4. በስርቆት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች

በሀላባ ብሔረሰብ በሰፊው ከሚካሄዱት የስርቆት አይነቶች ውስጥ ግንባር ቀደሙ የቤት እንስሳት ስርቆት ወይም ዘረፋ ነው፡፡ ስርቆቱ የሚካሄደው አብዛኛው ጊዜ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና ጨለማን ተገን አድርጎ ነው፡፡ የስርቆት ድርጊት ሲፈፀም የሀላባ ሕዝብ የተሰረቁትን የቤት እንስሳት የሚያስመልስበት ራሱን የቻለ ባህላዊ አካሄድ አለው፡፡ ይህም ቁልፍ የፍለጋ ስልታቸው የከብቶቹን የእግር ዱካ ተከትሎ መሄድ ነው፡፡ ዱካቸውም የሆነ ቦታ ደርሶ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ባለቤቶቹም የከብቶቹ ዱካ የጠፋበት ቦታ ወይም ስፍራ ሆነው ጩኸታቸውን ያሰማሉ፡፡ ጩኸቱን  የሰማ የአካባቢው ነዋሪ በሙሉ ምን ተፈጠረ? ምን ደረሰ? በማለት ግር ብሎ ይወጣል፡፡ የጠፉትን ከብቶች ፈላጊዎችም የተሠረቁት ከብቶች ዱካ ይኸው እዚህ ደርሷልና ወይ ዱካውን አሳልፉን ወይም የሰረቀ ግለሰብ እናንተ ውስጥ አለና አውጡ ይላሉ፡፡ የመንደሩ ነዋሪዎችም እንደተባለው የከብቶቹን ዱካ በዕርግጥ መንደራቸው መግባቱን ካረጋገጡ የከብቶቹ ዱካ ከመንደራቸው ማለፍ አለማለፉን በጥንቃቄ ያረጋግጣሉ፡፡

ነገር ግን የከብቶቹ ዱካ መንደራቸው ገብቶ በስውር አቅጣጫ ከመንደሩ ከወጡም በባህላዊ የፍለጋ ሰልታቸው ከመንደራቸው ከብቶቹ መሻገራቸውን አረጋግጠው ከራሳቸው ዱካውን ያሳልፋሉ፡፡ ዱካው ካላለፈና በመንደራቸው  ከቀረ የሰረቀው ግለሰበ የግድ መውጣት አለበት በማለት ርስበርሳቸው ማን ይህን ድርጊት ሊፈጽም ይችላል በማለት ምርመራቸውን ይቀጥላሉ፡፡ የስርቆት ድርጊት የፈፀመ ግለሰብ በምንም መልኩ ሊያመልጥ ስለማይችል በተለያዩ መንገዶች ይመረምራሉ፡፡ ያጋልጣሉም፡፡ የተጠረጠረው ግለሰብም እውነቱን እንዲያወጣ ጦር ከጦር አገናኝተው በማቆም በመሃል በማሳለፍና በማዘለል ምርምራ ይካሄዳሉ፡፡ የሠረቀውም ግለሰብ በጦር መሃከል ከማለፍ ብሎ ያምናል፡፡ ምክንያቱም ካላመነና በዚህ መልኩ መሃላ ከፈፀመ እርግማኑ ለልጅ ልጅ ከመተላለፍ አልፎ ሠራቂውንም ለልዩ አደጋ ሊያጋልጠው ይችላል ተብሎ ስለሚታመን

ጥፋትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ በብሔረሰቡ የተለመደ ነው፡፡ ዘራፊው የፈፀመው ድርጊት በራሱ ላይ በደረሰው በደል የተነሳ ሆን ብሎ በቂም በቀል መፈፀሙን ካመነና የተወሰዱትን ከብቶች ለመመለስ ቃል ከገባ ሌላ ምንም ሳይቀጣ በምክርና በተግሳፅ ምህረት ይደረግለታል፡፡ እሱንም የበደሉት ማለትም የተዘረፉት ቤተሰብ ላደረሱበት በደል ይቅርታ እንዲጠይቁ ይደረጋሉ፡፡

የሰረቀው ግለሰብ ሆን ብሎ ከሆነና ያለ በቂ ምክንያት በቂም በቀል ተነሳስቶ ድርጊቱን ፈፅሞ ከሆነ የሀገር ሽማግሌዎች ልዩ ምርመራ አድርገው ለፈፀመው ድርጊት ኮርማ አርዶ እንዲያበላ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የተሰረቀው ግለሰብ ለፍለጋ ያወጣውንም ወጪ ይመልሳል፡፡የሚከፍለው ገንዘብ ከሌለው የቁም ከብቶ ወይም መሬቱንም ይሁን ሌላ ንብረቱን ሽጦ እንዲከፍል ይወሰንበታል፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን የከብቶቹ ዱካ መንደራቸው ገብቶ የማይተባበሩ ወይም የሰረቀውን ግለሰብ አሳልፈው ወይም አጋልጠው የማይሰጡ ከሆነ እስከ ሞት የሚያደርስ የርስበርስ ግጭት ይቀሰቀሳል፡፡ ይህ እንዳይፈጠር በሀላባ ብሔረሰብ ማንም ወንጀል የሰራ ግለሰብ የትም ስፍራ ተሸሽጎ ወይም ተሰውሮ መኖር ስለማይችል እውነታዎች ውለው ሳያድሩ ይወጣሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሌላ ከፍተኛ ግጭት የሚቀሰቅሰው የስርቆት ድርጊት በድንበር አካባቢ ከሚገኙ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር የቤት እንስሳት በግጦሽ ሣርና በውሃ አጠቃቀም በሚንቀሳቀሱበት ወቅትነው፡፡ በዚህም ሆን ተብሎም ይሁን ድንገት የአንዱ ግለሰብ ከብት ወደ ሌላው ግለሰብ ከብቶች ተቀላቅሎ ሊጠፋ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ የእኔን ከብት መልስ በሚል እሰጣ ገባ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ በሰላማዊ መንገድ ወዲያው ካልተፈታ ውሎ አድሮ በሁለቱ ሕዝቦች መካከል የማያባራ ግጭትን ይቀሰቅሳል፡፡ ሰዎች እርስ በርስ በመደባደብ የአካል ማጉደልና የመገዳደል ወንጀሎች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡ የዚህ አይነቱን የግጭት አይነት በሁለቱም ሕዝቦች በኩል ያሉት የሀገር ሽማግሌዎች ርስበርስ ተነጋግረው በባህላቸው መሠረት ዕርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ፡፡ ሆን ብለውም ይሁን በድንገት ይህን ድርጊት በፈፀሙ ግለሰቦች ላይ በግጭቱ ሰው ሞቶ ከሆነ በጉማ፣ የአካል ማጉደል ድርጊት ከተፈፀመ በግማሽ ጉማ፣ ሌላ መለስተኛ ድርጊት ከፈፀመ ደግሞ በኮርማ ክፍያ ዕርቅ እንዲወርድ ያደርጋሉ፡፡ በብሄረሰቡ ውስጥ በጎረቤቶች መካከል ተፈጥሮ የነበረ ግጭትን በማንሳት የሚከተለውን ታሪክ አቶ እንዳለ አጫውተውኛል፡፡


**ተረክ** 4 የላይኛው በደኔ ተብሎ በሚታወቀው ቀበሌ ሶስት ወንድማማቾች ይማከሩና ጎረቤታቸው የሆነ አርሶ አደርን የቀፎ ማር ይሰርቁበታል፡፡ አርሶ አደሩም እነዚን ሰዎች ይጠረጥርና ለአካባቢው ጉባዔ ይከሳቸዋል፡፡ በሸንጎው ላይ ቀርበው ተጠርጣሪዎቹ ሲጠየቁ አልወሰድንም በማለት ካዱ፡፡ በዚህ ምክንያት ጉዳዩ ወደ ጎሳ ሸንጎ ተዛወረ፡፡በዚያ ጉባዔም ላይ የተሰበሰቡት ሽማግሌዎች "የአካባቢዉን ኦገቴዎች አልፋችሁ ነው የመጣችሁት" ብለው ጠየቁዋቸው፡፡ ከሳሽም በዚያ ደረጃ ፍትህ ሊያገኝ እንዳልቻለ ገለጸላቸው፡፡ በመቀጠልም ሽማግሌዎቹ ተክሳሾቹን እናንተ ሰዎች ማሩን ወስዳችሁ ከሆነ እመኑ፡፡ ብታምኑ ክሱ ቀለል ይልላችሁዋል፡፡በማለት ሊያሳምኑዋቸው ሞከሩ፡፡ተጠርጣሪዎቹ ግን ፈጽሞ ሊያምኑ አለቻሉም፡፡ሌላ አማራጭ ስላላገኙ እውነታውን ለማግኘት ወደ መሃላ ደረጃ ደረሱ፡፡ ለዚህም እንዲያመች በጉባዔው የተገኘውን ህዝብ ለሁለት በመክፈል መሃሉን ክፍት በማድረግ መንገድ ከፈቱ፡፡ ከዚያም ተከሳሾቹን የዚህን ሰዉዬ ማር አልወሰድንም ስትሉ ዓይናችሁን በእጃችሁ በመሸፈን በዚህ መንገድ ተራምዳችሁ ጉባኤውን አቋርጡ አሉዋቸው፡፡ በጉባኤው ላይ የተጠርጣሪዎቹ አባት ነበር፡፡ ከመሃላው በፊት እባካችሁ ልጆቼ ወስዳችሁ ከሆነ እመኑ ቅጣቱን እኔ እከፍላለሁ አላቸው፡፡ አልወሰድንም! በማለት በሃይለ ቃል በመመለስ ታላቁ ወንድማቸው አይኑን በእጁ በመሸፈን ጉባኤውን አቋረጠ፡፡ አቋርጦ እንደጨረሰም እጁን ከአይኑ ላይ ሲያነሳ ዓይኑ ተታውሩዋል፡፡ወዲያውም በጣም ደንግጦ "ወይኔ ዓይኔ! "በማለት ጮኸ፡፡ ይህንን ያዩት ታናናሽ ወንድሞቹ ወዲያው ጥፋታቸውን አመኑ፡፡በስፍራው የነበረው ሰው ሁሉ በጣም ተገረመ፡፡ ወዲያውም ጥፋተኞቹ የኮርማና የማር ቅጣት ተበይኖባቸው ወደ ሌላ ጉዳይ ተገባ (አቶ እንዳለ፡ ጥር 28፣ 2006 ዓ.ም. ስክርብ፣11)፡፡

# 3. የሀላባ ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታባቸው መዋቅርና ሥርዓቶች ምንነት

## 3.1. መዋቅር

ማንኛውም ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት በሀላባ ብሔረሰብ ዘንድ 'አገቲ ሴሪ' በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ የ 'አገቴ' ሥርዓት አራት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነርሱም በአንድ ቤት ውስጥ የሚፈጠርን ግጭት የሚፈታ 'ሚኒ አገቴ' በመባል የሚታወቀው ባህላዊ ተቋም ሲሆን እቤት ውስጥ አባት ወይም እናት ካልሆነም ደግሞ ታላቅ ወንድሞ የሚሸመግልበት ሂደት ነው፡፡ በመቀጠል 'ቦኪ ሙሪች' የሚባል ደረጃ አለ፡፡ ይህ ደረጃ ደግሞ በአንድ ቤተሠብ ውስጥ የተፈጠረን ችግር /ግጭት/ የሚፈታ ተቋም ነው፡፡ የሚከወነውም በወንድማማቾች ቤት ግጭት ቢፈጠር ይህንን ግጭት ለማስወገድ የቤተሠቡ ታላቅ የሆነው ሰው ሰብስቦ ችግርን የሚፈታበት ሂደት ነው፡፡ ግጭቱ ግን ጠንከር ብሎ ከዚህ ደረጃ ከፍ ካለ ቀጥሎ ወዳለው ደረጃ እንዲሄድ የቤተሠቡ መሪ ያስተላልፈዋል፡፡ ቀጥሎ ያለው ደረጃ 'ደቦ መሪቾ' በመባል ይታወቃል፡፡ የቤተሠቡ መሪ ይህንን ጉዳይ ለጎሣ ሸንጎ /ደቦ አገቴ/ አሳልፎ ሰጠ ማለት ጉዳዩ ወደ ጥላ ስር ደረስ ማለት ነው፡፡ ይህ ደረጃ በሀላባ ሴራ ኦገቴ በሁለተኛ ደረጃ  ይገኛል፡፡ የመጨረሻው የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ደረጃ 'ሀላቢ አገቴ' ወይም 'ጎጎታ' ተብሎ ይጠራል፡፡ በዚህ ሸንጎ ላይ ግን በብዛት የሚታዩት ጉዳዮች ዋና ዋና ጉዳዮች ለምሳሌ፡- ከአገራባች ከሌሎችና ዞኖች ጋር የተፈጠሩ ችግሮችን መፍታት፣ ድርቅና ረሀብ ካለ በነዚያ ጉዳዮች ዙሪያ መነጋገር፣ የተቸገሩ ሰዎችን መርዳትና የመሣሠሉት ናቸው፡፡ ሌሎች በተለያዩ ወንጀሎች ተከሰው የቀረቡ ጉዳዮች ቢመጡ በየደረጃቸው ለጎሣና ለቤተሠብ ሸንጎዎች ተመልሰው እዚያው በተፈጠሩበት ቦታ እንዲታዩ ይደረጋል፡፡

ከለይ እንደተገለፀው በሀላባ ብሔረሰብ የሚፈጠሩ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ግጭቶች ለመፍታት የሚያስችሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸው ባህላዊ ተቋማት አሉ፡፡




**የሀላባ ባህላዊ አስተዳደር መዋቅር (መዋቅራዊ ምስሉ በአጥኚው)**

1. **የቤተሠብ ሸንጎ /ቦኪ ሙሪቾ/**

ይህ እርከን አጠቃላይ የቤተሠብ አባላትን እስከ አራት ወይም አምስት አያት ትውልድ ድረስ ያሉትን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይህንን ደረጃ የሚመራው 'ሙሪቾ' ይባላል፡፡

2. **የቤተ ዘመድ ሸንጎ /ሚኒ አገቴ/** በዚህ ደረጃ ደግሞ እስከ ሰባት በዛ በከተባለም እስከ ስምንት አያት ትውልዶች ድረስ የሉትን ያካትታል፡፡ በደረጃውም ከ 'ቦኪ ሙሪቾ' ሰፋ ያለ ነው፡፡ በነዚህ ደረጃዎች የተፈጠሩ አለመግባባቶችን የሚፈታ ነው፡፡

3. **የጎሣ ሸንጎ /ደቦ መአገቴ/**

ይህ እርከን በሀላባ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ውስጥ መካከለኛ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡ ይህ ተቋምም በአንድ ጎሣ ውስጥ የሚገኝ ንዑሳን ክፍሎች አጠቃሎ የያዘና ሁሉንም የጎሣው አባላት አባል አድርጎ የሚይዝ አገቴ ነው፡፡ የዚህ ሸንጎ ተግባርና ሀላፊነትም በቤተሠብና በቤተዘመድ ደረጃ ቀርበው ከአቅማቸው በላይ ሆነው ወይም ደግሞ በይግባኝ የሚቀርቡ ግጭቶችንና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ማየትና መፍታት ነው፡፡ ይህ ተቋም በጎሣው ታላቅ ቤት ሰው መሪነት እና የተለያየ ቁጥር ባላቸው ሙሪቾ ተብለው በሚታወቁ አስፈፃሚዎች የሚመራ ነው፡፡ መሪውም የደቦ ዳኛ ይባላል፡፡ የጎሣ ዳኛ እንደማለት ነው፡፡

4.**የሀላባ አገቴ /ሀላቢ አገቴ/ጎጎታ/**

ይህ እርከን የመጨረሻው የስልጣን ደረጃ ሲሆን በሀላባ ውስጥ ያሉ ሁሉንም ጎሣዎች አባል የደረገ ነው፡፡ ስልጣንና ሀላፊነቱም ከላይ ካየናቸው አንፃር ሰፊና ተልቅ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ብሔረሰቡን በተመለከተ የሚወጡ ህጎችን፣ ፓሊሲዎችን፣ ከአጐራባች ህዝቦች ጋር ሊኖር የሚችል/ የሚገባ ግንኙነትን የመወሰን ስልጣን አለው፡፡ በተጨማሪም በጎሣ የረጃ ተይዘው ሊፈቱ ያልቻሉና በይግባኝ የመጡ ጉዳዮችን የሚፈታ ተቋም ነው፡፡ መሪውም 'ወማ' ይባላል(እማም መሀመድ ጥር 29 ፡ 2006 ዓ.ም፣ ስክርብ፣ 27 )፡፡



ፎቶ 3፡ የሃላባ ኦገቴ መሪ ‹ወማ›

## 3.2. ሥርዓቶች

### 3.2.1 ዎርጃሞ እና ሩበቴ

ዎርጃሞ ኮርማ ማለት ሲሆን፤ በሀላባ ብሔረሰብ ማንም ግለሰብ ትንሽ ወይም ትልቅ ጥፋት ካጠፋ በኮርማ ይቀጣል፡፡ ኮርማ መቅጣት የብሔረሰቡ ወግና ልማድ ነው፡፡ የኮርማ መቀጮ በብሔረሰቡ ባህል ቋሚ እንስሳት ማለትም የቀንድ ከብት ኮርማ፣የበግ ወይም የፍየል ሙክት ካልሆነም እነዚያን የሚተካ ጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ በብሔረሰቡ በኮርማ መቀጣት ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ የተለመደና አሁንም እየተሰራበት ያለ ጠንካራ ባህል ነው፡፡ማንም በጥፋተኝነት የተፈረጀ ሁሉ ኮርማ ይቀጣል፡፡ በዳይ ወይም ጥፋተኛ ግለሰብ አገቴ ፊት ቀርቦ ስለጥፋቱ ያምናል፡፡ ለዕርቅ የተሰበሰበው ዕድምተኛ ይህ ግለሰብ ጥፋት አጥፍቶ ይኸው በከበረው ኦገቴ ፊት ቀርቦዋልና ምን ይደረግ? ተብሎ ሲጠየቅ ተሰብሳቢው በአንድ ድምፅ ይቀጣ ! ይላል፡፡ የአገቴው መሪ ምን ይቀጣ? ይላል፡፡ በመቀጠል ተሰብሳቢው ጥፋተኛው በመጀመሪያ ዋስ ይጥራ ይላል (ሩበቴ በሀላብኛ ቋንቋ ዋስ ማለት ነው)፡፡ ጥፋተኛው ግለሰብ ለዕርቅ ከተሰበሰቡት ውስጥ ለዋስትና ይሆነኛል ብሎ ያመነበትን አንዱን ግለሰብ ይጠቁማል፡፡ ለዋስትና የተጠራ ግለሰብም ዋስትናውን መቀበል አለመቀበሉን ይጠየቃል፡፡ መቀበሉን ሲያረጋግጡ ጥፋተኛው ግለሰብ ኮርማ እንዲቀጣና ቅጣቱን ካልከፈለ ግን ዋስ የሆነለት ግለሰብ እንደሚከፍል ካሳሰቡ በኋላ ወደ ዋናው ጉዳይ በማለፍ ስለ ተከሰተው ግጭትና ስለ

ደረሰው ጥፋት መመልከት ይጀምራሉ፡፡ የጥፋት አይነቶቹ ቀላል ይሁኑ ከባድ ሁሉም የዕርቅ ሂደቶች የሚጀመሩት በዚህ መልኩ ይሆናል፡፡

በሀላባ ብሔረሰብ የወንጀል ድርጊት በፈፀመ ግለሰብ ላይ ባህላዊ የጥፋተኛነት ውሳኔዎች ከመተላለፋቸው በፊት ጥፋተኛው ግለሰብ ዋስ እንደሚጠራ የታወቀ ሲሆን ይህ የዕርቅ ሂደት በብሔረሰቡ ዘንድ ሩበቴ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለግለሰቡ ለማናቸውም ጉዳዮች ጥፋተኛውን በሚመለከት ኃላፊነት የሚወስድ ሰው የግድ ስለሚያስፈልግ ነው፡፡ ወንጀል ፈጻሚው ካመለጠ ወይም የተላለፈውን የቅጣት ውሳኔ በጊዜና በሰአቱ የማይከፍልና ማይፈጽም ከሆነ በቀላሉ ዋሱ ስለሚጠየቅ ነው፡፡ ጥፋተኛውም ግለሰብ ዋስ /ሩበቴ/ የሆነለትን ግለሰብና ቤተሰቡን ችግር ውስጥ ላለመከተት ብሎ ለባህላዊ የዕርቅ ውሳኔዎች ሁሉ ተገዢና ታዛዥ ይሆናል(የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ መጽሄት 1998 ፤ እማም መሃመድ ፣ ጥር 29፣ 2006፣ ዓ.ም ፣ ስክርብ ፣ 30)፡፡

## 3.2.2 የጉዳ እና የጉማ የዕርቅ ሥርዓቶች

በቤተሰብ፣ በቤተዘመድ፣ በጎረቤት፣ ጉሣ ከጉሣ፣ አንድ ጎሳ ከሌላ ጎሣ እንዲሁም ከአጐራባች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ድንገት ሳይታሰብና በስህተት የተፈጠረ የግድያ ድርጊትን የሀላባ በባሕላዊ የዳኝነት ሥርዓቱ /ኦገቴ/ የማፈታበት የዕርቅ ሂደት ጉዳ ይባላል፡፡ በዚህ በጉዳ ሥርዓት ከገዳይ የጥቁር ዕርድ ብቻ ይጠበቅበታል (እማም መሃመድ ፣ ጥር 29፣ 2006፣ ዓ.ም ፣ ስክርብ ፣30)፡፡

ጉማ አንድ ግለሰብ ሆን ብሎ አስቦበትና አቅዶ በቂም በቀል ግድያ ከፈፀመ በኦገቴ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓተ 100 የቁም ከብቶች የሚቀጣበት ባህላዊ የፍርድ ሂደት ነው፡፡ ምንም እንኳን 100 የቁም ከብቶች ለአንድ ሰው ከአቅም በላይ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም የገዳዩ የቅርብ ቤተ ዘመድና ጉሣ የቁም ከብቶችን በማዋጣት ይተባበሩታል፡፡ ምክንያቱም ገዳዩ ችግር ውስጥ ሳይገባ በፊት ለሌሎች ችግር እንዲሁ የደረሰ በመሆኑ ዛሬ አንዲህ ያለ ችግር ውስጥ ገብቶ እንዴት ዝም እንላለን የሚል የመተባበርና የመተጋገዝ ባህሉ በብሌረሰቡ ዘንድ የነበረና ያለ ስለሆነ የተላለፈበት የቅጣት ውሳኔ በዚህ መልኩ ይከፍላል፡፡ ከብቶቹ በዋናነት ጊደሮችና ላሞች ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም የደረሰው በደል አስከፊ በመሆኑ ላሞችና ጊደሮች ወላድና የሚራቡ በመሆናቸው የሟች ቤተሰብን

ሞራል ይጠብቃል፤ ሊካሱ ይችላሉ፤ ተብሎ ስለማታመን ቅጣቱ በዚህ ይወሰናል። በሌላ መልኩ በባህሉ እንደ ጥፋቱ ቅለትና ክብደት አንድ ጥፋተኛ ግማሽ ጉማ ወይም ሩብ ጉማ የሚከፍልበት ሁኔታ ይኖራል። ከጉማ አከፋፈል ጎን ለጎን በባህሉ የማይቀረው የጥቁር እንስሳ ዕርድ ሥነ ሥርአትም ይከናወናል(ኤፍሬም፡ 2006፣72)።

## 3.2.3. የጥቁር እንስሳ ዕርድ ሥነ-ሥርዓት

በሀላባ ብሔረሰብ በማወቅ ሆን ተብሎ በቂም በቀል፣ በድንገትና በስህተት /ጉማና ጉዳ/ ለሚፈፀሙ የግድያ ድርጊቶች ሁሉ ለዕርቅ ሂደቱ የጥቁር እንስሳ ዕርድ ሥርዓት ይፈፀማል። ጥቁር መልክ ያለው እንስሳ የሚመረጥበት ዋናው ምክንያት በሟች ቤተሰብም ይሁን በገዳይ ቤተሰብ በኩል የተፈጠረው ነገር እጅግ መራራ፣ የከፋ፣ ጨለማና መሪር ሀዘን መሆኑን ያመለክታል። ይህ የዕርድ ሥነ ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መኖሩን የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ። ከሚታረዱት እንስሳት መካከል በጎችና የቀንድ ከብቶች ይጠቀሳሉ። ፍየል ጭራዋ አጭርና ወደላይ የተቀለበሰና ሃፍረቷን የማትሸፍን በመሆኗ በማናቸውም የዕርቅ ሥርዓቶች ላይ የፍየል እርድ አይከናወንም። በደረሰው የግድያ ሁኔታ ምክንያት ሁለቱም ቤተሰቦች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ችግር፣ መከራና ስቃይ ተገፍፎ ወደ ብርሃን የሚቀየረው ጥቁር መልክ ያለው እንስሳ የታረደ ሲሆን ብቻ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው። ግድያው ከተፈፀመበት እለት ጀምሮ ሁለቱም ቤተሰቦች ከማህበሪዊና ኢኮኖሚያዊ የጋራ መስተጋብሮች በእጅጉ ተለያይተው የቆዩ በመሆናቸው በመጨረሻዋ የዕርቅ ዕለት ከጥቁር እርድ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ፊት ለፊት ይተያያሉ ። በዕርቁ ዕለት የገዳይ ቤተሰቦች ያመጡትን ጥቁር መልክ ያለው በግ፣ ወይፈን፣ ጊደር ሊሆን ይችላል፤ ታርዶ ደም እስኪፈስ ድረስ ሁለቱም ወገኖች አይተያዩም። በስፍራውም ሁለቱም ቤተሰቦች ፊታቸውን አዙረው ጀርባቸውን ተሰጣጥተው ይቆማሉ። የታረደው እንስሳ ደም ከፈሰሰ በኋላ ፊታቸውን ያዞራሉ። ወዲያው ከታረደው እንስሳ ሆድ ዕቃ ውስጥ አንጀቱን በማውጣት እንደሰንሰለት ተጠላልፎ ይገመድና ገዳይና የሟች አባት ወይም ሌላ በጣም የሚቀርበው ሰው ጫፍና ጫፉን በመያዝ ጎትተው ይበጥሱታል፡። ይህም ማለት አንጀት በብሄረሰቡ ዘንድ የመቀራረብና ነገርን ከልብ የመተው ምልክት ተደርጎ ስለሚቆጠር አሁን የሚፈጥሩት ዕርቅ ከአንጀታቸው እንደሆነና ከዚህ በኋላ ሁለቱም ወገኖች በቂም በቀል እንደማይፈላለጉና እንደ አንድ ቤተሰብ በፍቅር

እንደሚኖሩ የሚያሳይ አንድምታ  አለው፡፡ የታረደውም  እንስሳ ሥጋ በክትፎ መልክ ይዘጋጅና ወይም ደግሞ   ከገብስ የሚሰራ እንደ ጭኮ ያለ ባህላዊ  ምግብ ይቀርብና በገዳይ መዳፍ ላይ በማኖር ቀድሞ ለሟች ቤተሰብ ተወካይ ከመዳፉ እንደያቀምስ ይደርጋል፡፡ ይህም ሥርዓት ከዚህ በኃላ ሁለቱም ቤተሰብ ከቂም በቀል ነፃ መሆናቸውንና ዕርቅና ሰላም መውረዱን  ያሳያል(እማም ሂርጶ ፣ጥር ፣30፣2006 ዓ.ም. ፣ስክርብ ፣40)፡፡



ፎቶ :4 የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች እርቅ ሰነ ስርዓት ላይ ገዳይ ከሟች አባት እጅ ሲበላ የሚያመለክት

## 3.2.4. የማርና የኮሶ መርጨት ሥነ ሥርዓት

በመጨረሻ የዕርቅ ዕለት ከጥቁር ዕርድ ሥነ-ሥርዓት ጋር ጐን ለጐን ከሚካሄዱት ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓቶች መካከል ሌላው ቁልፍ  ተግባር የማርና የኮሶ መርጨት ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ ይህን ሥነ ሥርዓት የሚከናወኑት የገዳይ ቤተሰብ ለዕርቅ ቀን ከጥቁር ዕርድ ጋር ኮሶ ያዘጋጃሉ፡፡ የመርጨቱን ተግባር የማያከናውኑት የገዳይ እህት ወይም አክስት ስትሆን ሁለቱም ከሌሉና የማይገኙ ከሆነ ግን ከገዳይ ቤተሰብ በኩል ሌላ ሴት ልትሆን ትችላለች፡፡ ኮሶ የመርጨቱ ጉዳይ የተፈጠረው የግድያ ሁኔታ ልክ እንደ ኮሶ የመረረ መሆኑንና ከዕርቁ በኂላ ይህ መራራ ነገር መውጣቱን አመላካች ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ኮሶ ምንም መራር ቢሆንም በውስጣችን ያለ በሽታን ሚያሽረን  ነው፡፡ እንዲሁም ውስጥን የሚያነጻ ስለሆነ ኮሶን መጠቀመቀቸው ተምሳሌትነቱ የመረረውን ግጭት ከውስጣችን አውጥተነዋል  ከቂምና በቀልም ነጻ ሆነናል የሚል አንድምታ ይይዛል፡፤፤ የማር መርጨቱ ሥነ ሥርዓት ደግሞ በገዳይ ቤተሰብ በኩል ይፈፀማል፡፡ የምትረጨው ደግሞ ማንም ሴት ሳትሆን የገዳይ እህት ወይም አክስት መሆን

ይኖርባታል፡፡ ማሩንም በእርጥብ ግራዋ ቅጠል በመንከር ትረጨዋለች፡፡ ይህም በሚች ቤተሰብ በኩል ተከስቶ የነበረው መራራ ሀዘን ወጥቶ ጣፋጭ ፍቅርና ሰላም ይግባ የሚል መልዕክት ያለው ባህላዊ አንድምታ አለው፡፡ ለሀገር ሽማግሌዎችም በዋንጫ ማርና ወተት ተሞልቶ ይሰጥና እየተጐነጩ በሁለቱም ቤተሰቦች ላይ እንትፍ እያሉ ይመርቋቸዋል፡፡ በመቀጠል በገዳይ ቤተሰብ በኩል የመጣውን ጋቢ /ቡሉኮ/ እንደ ድንኳን ተዘርግቶ ሁለቱም ቤተሰብ በስሩ እንዲሰበሰቡና ምርቃት እንዲቀበሉ ይደረጋል፡፡ ይህም ከዚህ በኋላ አንድ ቤተሰብ ሆነናል፣ የተፈጠረው ችግር ተፈቷል፤ ዕርቅ ወርዷል ፣ ከዚህ በኋላ አንድ ቤተሰብ ሆነናል፤ የተፈጠረው ችግር ተፈቷል፤ ዕርቅ ወርዷል፤ ወደ ቀድሞ የርስ በርስ ፍቅርና ሰላማችን ተመልሰናል ለማለት ነው፡፡ በመጨረሻም የተዘጋጁትን ባህላዊ ምግቦች ከአንድ ገበታ ይበላሉ፡፡ ባህላዊ መጠጦችም ከአንድ ዋንጫ ይጠጣሉ፤ ተመራርቀው ይሸኛኛሉ፡፡ አልፎ አልፎ አሁንም በብሔረሰቡ ቀለል ያሉና ድንገት በስህተት የተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች በማር መርጨት ብቻ እንደሚያልቁ የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ በዚህ መልኩ ዕርቅ ከወረደ በኋላ ገዳይም ይሁን ቤተሰቦቹ ያለ ምንም ስጋት ከሚች ቤተሰብ ጋር በሰላምና በፍቅር እንደ ቀድሞአቸው በባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አብረው መኖር ይጀምራሉ፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ በሁለቱም ቤተሰቦች መካከል የበለጠ ወዳጅነትና ዝምድና እንዲኖርና እንዲጠናከር በስጋ ዝምድና የማይገናኙ ከሆኑ ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ልጆች ካሏቸው በጋብቻ ይተሳሰራሉ(ኤፍሬም፡ 2006፣73፤ እማም መሃመድ ፣ ጥር 29፣ 2006፣ ዓ.ም ፣ ስክርብ ፣28)፡፡

### 3.2.5. ራጋ

በሀላባ ብሔረሰብ የግድያ ወንጀሎች አብዛኞቹ የእምነት አባቶች፣ የጐሣ መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በሚያደርጉት የጉዳና የጉማ የዕርቅ ሂደቶች የሚያልቁ ይሆናሉ፡፡ የዕርቅ ሂደቱ ሲካሄድ አልፎ አልፎ ለዕርቅ በተሰበሰቡ ተሳታፊዎች፣ አስታራቂዎችና በተጎጂ ቤተሰቦች መካከል የሀሳብ ልዩነት የሚፈጠርበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ይህም ማለት የግድያ ድርጊቱን ግማሹ በጉዳ ይለቅ ሲል ሌላው ወገን ደግሞ በጉማ መሆን አለበት ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ የተፈጠረውን ልዩነት ወደ አንድነት የሚያመጣ በብሔረሰቡ በዕርቅ ጉዳዮች ዘመናትን ያስቆጠሩና በዕድሜ አንጋፋ የሆኑ በአካባቢው የተወሰኑ ግለሰቦች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ራጋ (አዋቂ) ተብለው ይጠራሉ፡፡ የተነሳው የሀሳብ ልዩነት

ወደነዚህ ግለሰቦች ይወሰዳል፡፡ ራጋ የተባሉ ግለሰቦችም የሟችና የገዳይ ቤተሰብን ስለ ግድያ ሁኔታው በጥልቀት ይመረምራሉ፡፡ ከዚህ በፊት በነዚህ ቤተሰቦች ውስጥ የተፈጠረ ነገር ምን አለ? ሁለቱም ወገኖች ከዚህ በፊት በሆነ ነገር ቅሬታ ኖሯቸው በመካከላቸው ፍፁም ይቅርታ ካልወረደ፣ በቤተዘመድና በጉማ ያልተከፈለ የደም ዕዳ መኖር አለመኖሩን፣ በሴራ በሁለቱም ያልተከፈለ ነገር ካለ ይመረምራሉ፡፡ የተደበቀ እርም ነገር ካለ እንደያወጡም ያደርጋሉ፡፡ ካላወጡና ደብቀው ከታረቁ ወደፊትም ቢሆን ሌላ አደጋ ስለሚያጋጥማቸውና ለልጅ ልጅም ሊተላለፍ ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ራጋ በተባሉ ግለሰቦች ፊት ሁለቱም ቤተሰቦቹ እውነቱን እንዲናገሩ ይመከራሉ፡፡ በዚህ መልኩ ራጋ የተባሉ ግለሰቦች ነገሮችን ከመረመሩ በኋላ የግድያ ድርጊቱ በጉማ ወይመ በጉዳ መጨረስ እንዳለባቸው ይነገራቸዋል፡፡ የሟችና የገዳይ ቤተሰቦችም በተነገራቸው መሠረት የደረሰውን የግድያ አደጋ በባህሉ መሠረት ይፈታሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሐሳብ ልዩነት ካልተፈጠረ በስተቀር ወደነዚህ አዋቂ ግለሰቦች /ራጋ/ ሳይኬድ የዕርቅ ጉዳዮች ያልቃሉ፡፡ የዕርቅ ሂደቶች ራጋ የተባሉ ግለሰቦች ጋ ሳይኬድ በጉዳም ይሁን በጉማ ከተፈታ በኋላ የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች ተያይዘው ራጋ ወደ ተባሉ ግለሰቦች እንዲሄዱ ይመከራሉ ወይም ራሳቸው ተመካክረው የሚሄዱበት ጊዜም ይኖራል፡፡ ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት የተፈፀመው የግድያ ድርጊት በራጋ ካልታየ ለልጅ ልጅ ይተላለፋል የሚል እምነት በመኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ቤተሰቦች ይህ የግድያ ሁኔታ ለምን ተፈፀመ? ወይም ለምን በኛ ቤተሰብ ተደጋገመ? የቆየና ያልተገለጠ ምን እርም አለ? በማን እጅ ላይ ደም አለ? የሚሉትና የመሳሰሉትን ጉዳዮችን በመያዝ፣ እንዲሁም የገዳይ ቤተሰብ ለሟች ቤተሰብ የተከፈለው የእርቅ ክፍያ ከልክ በላይ ወይም በታች መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥና ሌሎች የጥርጣሬ ጥያቄዎቻቸውን ለመፍታት ምንም እንኳን ጉዳያቸው በሀገር ሽማግሌዎች ቢያልቅም ተማክረውም ሳይመማከሩም ራጋ ወደ ተባሉ ግለሰቦች የመሄዱ ነገር በብሔረሰቡ ዛሬም መኖሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ አዋቂ /ራጋ/ የተባሉ ግለሰቦችም የሁለቱንም ወገኖች ጉዳይ በዝርዝር ከተመለከቱ በኋላ መፈፀም ስላለባቸው ነገሮች ይነገራቸዋል፣ ሁሉም ነገር እነርሱ እንደፈሩት ሳይሆንና በራጋ ምርመራ መሠረት ሰላም ከሆነ ተመርቀው እንዲሸኙ ይደረጋል፡፡ ከሀገር ሽማግሌዎች ሲናገሩ አንዳንድ ጊዜ እነዚህ ራጋ የተባሉ ግለሰቦች በቅርብ በብሔረሰቡ የማይገኙበት ወቅት ይኖራሉ፡፡ እነርሱም ማማከር በባህሉ የግድ በሚሆንበት ወቅት ወደ

አጐራባች ብሔረሰቦች ዘንድ ተኪዶ ጉዳዩ ያልቃል (እማም መሃመድ ፣ ጥር 29፣ 2006፣ ዓ.ም ፣ ስክርብ ፣29)፡፡

### 3.2.6. ወደፋ

ወደፋ በኮርማ ላይ የሚጨመር ተጨማሪ መቀጮ ሲሆን፣ ይህም የማር ቅጣት ነው፡፡ በሀላባ ብሔረሰብ አንዳንድ ቀለል ያሉ የጥፋት አይነቶች በማር ክፍያ የሚያልቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በቤተሰብና በጐረቤት አካባቢ የሚነሱ ተራ አለመግባባቶች፣ የሴቶችና ህፃናት ግጭቶችና ታላላቅ አባቶችን አለማክበርና የመሳሰሉት ግጭቶችን የአካባቢው ሽማግሌዎች ጉዳዩን አቅልለው በመፍታት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ግለሰብ ማር እንዲቀጣ ይደረጋል፡፡ የማር ቅጣቱም አንድ ሙሉ እንስራ ሆኖ ግማሹን በብርዝ መልክ ጥፋተኛው ግለሰብ ለዕርቅ ሥርዓቱ የወጡትን ሽማግሌዎችና የተበዳይ ቤተሰብን በማጠጣት የሚቀጣበት ሂደት ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ሽማግሌዎቹ በሁለቱ ወገኖች በበዳይና በተበዳይ ላይ ከዋንጫ ብርዝ እየተጎነጩ እንትፍ እያሉ ይመርቋቸዋል (እማም ሂርጶ ወጩሶ፣ ጥር 29፣ 2006 ዓ.ም .ስክሰርብ ፣39)፡፡

### 3.2.7. ማጋ

በየትኛውም አለመግባባትና ግጭት መሀል የሀገር ሽማግሌዎች፣ የእምነት አባቶችና የጐሣ መሪዎች የሚያከናውኗቸው የቅድመ ሽምግልና ተግባራትና ኃላፊነቶች ማጋ ተብለው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ ተግባራትና ኃላፊነቶች ሁለት ወገኖች በምንም ጉዳይ ሲጋጩ ጣልቃ ገብቶ የማረጋጋትና ተጋጪ ወገኖችን ያለ አድሎ ወደ ባህላዊ የዕርቅ ሂደት ጉዳያቸውን እንዲያመጡ የማድረግ ተግባር ሲሆን፤ በተለይ ከግድያ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ የሚፈፀሙት ተግባራት ሰፊ ናቸው፡፡ ገዳይ በማወቅም ይሁን በድንገት ነፍስ ካጠፋ ከግድያ ድርጊቱ በኋላ ወዲያው ወደ ታዋቂ የሀገር ሽማግሌ፣ የእምነት አባት ወይም የጐሣ መሪ ቤት ሄዶ ስለተፈፀመው ጉዳይ አሳውቆ ተደብቆ ይቀመጣል፡፡ ምክንያቱም የሟች ቤተሰብ በድንጋጤና በንዴት ሌላ አደጋ በቤተሰቡና በራሱ ላይ እንዳይፈጽሙ ለማድረግ ይህንን አስቀድሞ ይፈፅማል፡፡ ግለሰቡ ያረፈበት ታዋቂ የሀገር ሽማግሌ፣ የዕምነት አባት ወይም የጐሣ መሪ ወዲያው ስለተፈፀመው ጉዳይ በአካባቢው ላሉት ለሌሎች አባቶች በማሳወቅ ተሰብስበው ስለሚወስዱትና መውሰድ ባለባቸው ሁኔታዎች ዙሪያ ውይይት በማድረግ ወደ ሟች ቤተሰብ ዘንድ ይሄዳሉ፡፡ የሟች

ቤተሰብን የግድያ ድርጊት የፈፀመ ግለሰብ በአንዳችን ቤት አለ፡፡ ስለዚህ ስለሆነው ነገር ሁሉ በጣም አዝነናል፡፡ ጉዳዩን በሀላባ ብሔረሰብ ኦገቴ ሴራ እንጨርሰዋለን፤ ተረጋጉ፤ እኛ ጉዳዮዩን በባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱ ኦገቴ ሴራ ለመጨረስ ቃል እንገባለን፡፡ በገዳይ ቤተሰብና ሀብት ንብረት ላይ ተጨማሪ አደጋ እንዳትወስዱ፡፡ ከሁን በኋላ ጉዳዩን በኛ እጅ ላይ ጣሉት፤ ስለ ሆነው ሁሉ እኛ ኃላፊነቱን እንወስዳለን፤ በማለት ለተጎጂ ቤተሰብ ቃል ይገባሉ፡፡ በመቀጠልም ከዚህ በኋላ የሟችን የቀብር ሥነ-ሥርዓት አብረን በባህላችን እንፈጽማለን፤ በማለት የሟች ቤተሰብን ያረጋጋሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የገዳይ ቤተሰብም የዕርቅ ሥርዓቱ በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የዳኘነት ሥርዓቱ አገቴ ሴራ እስኪያልቅ ድረስ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አንድ ገበያ፣ ወንዝና መንገድ እንዳይጠቀሙ፣ በሚደረጉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ዕርቅ እስከሚወርድ ድረስ እንዳይተያዩና ቢቻል ከሟች መኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ ለጊዜው እንዲኖሩ ይመከራሉ፡፡ ይህንን ካደረጉ በኋላ ተመልሶ የገዳይን ፀጉር፣ ቅንድብ፣ ጥፍር እንዲላጭና እንዲቆረጥ ያደርጋሉ፡፡ ይህም የሚሆንበት ዋና ምክንያት ገዳይ የፈፀመው ድርጊት አስከፊ በመሆኑ፣ ማዘኑንና መፀፀቱን እንዲሁም እርም ማውጣቱን ለባህላዊ የዕርቅ ሥርዓቱ ታዛዥና ተገዥ መሆኑን ለማሳወቅ ሲባል ነው፡፡ ይህ ካልተደረገ ግን አላዘነም፣ አልተፀፀተም ተብሎ በሟች ቤተሰብ በኩል ሌላ ቅራኔ ወይመ አደጋ ስለሚያስከተል ሀላፊነት የወሰዱ አባቶች ይህንን ሁሉ ያስፈጽማሉ፡፡ በተጨማሪም ከዕርቅ ሂደቱ በፊት ሟች ከመሞቱ በፊት ለህክምናም ይሁን ከሞተ በኋላ ለቀብር ሥርዓት የሟች ቤተሰብ ወጪ ያደረጉትን ሁሉ በጥሬ ገንዘብ ተሰልቶ እንዲመለስላቸው ያደርጋሉ፡፡ እንግዲህ እነዚህ ባህላዊ የቅድመ ሽምግልና ሂደቶች በሀላባ ብሔረሰብ ማጋ ተብለው ይታወቃሉ (እማም ሂርጶ ፣ ጥር 29፣ 2006 ዓ.ም .ስከሰርብ ፣40)፡፡

- **የሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን**

በዚህ መዋቀር መሠረት በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ ጠብ/ግጭት/ ቢፈጠር በመጀመሪያ በሽምግልናው ስርዓት ላይ ነገር ለማየት የሚቀመጡ ሽማግሌዎች አሰያየም ቋሚ አይደለም፡፡ማለትም እንደ ተበዳይ ወይም በዳይ ምርጫ ነው፡፡ ማለትም አንድ ግጭት ተፈጥሮ በደረጃው ለአገቴ ቀርቦም ሆነ በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ፍርድ በሚጠብቅበት ወቅት ለባህላዊ የዳኝነት /ሽምግልና/ አካል ጉዳዩ ከተመለሰ በጎሣው መሪ ወይም በቤተሠቡ መሪ አማካይነት ሁለቱ ወገኖች /በዳይና ተበዳይ/ የየራሳቸውን ሽማግሌዎች

እንዲመርጡ ይደረጋል፡፡ ይህን በሚያስደርግበት  ወቅት የተመረጠው ሽማግሌ ለበዳይ ወይም ለተበዳይ የማይመቻቸውና በምርጫው ያልተስማሙ ከሆነ፤ ላለመስማማታቸውም በቂ ማስረጃ ካቀረቡ የተመረጠው ሽማግሌ ሊቀየር ይችላል፡፡ የቆይታ /የአገልግሎት/ ዘመናቸውም ጉዳዩን እስከሚፈቱበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሽማግሌው በማህበረሰቡ ዘንድ በጣም ተፈላጊ ከሆኑ ሌላ ጊዙም የመመረጥ  እድል ያገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል በየአገቴዎቹ ላይ መሪ ሆነው የሚቀመጡት የባህላዊው እርቅ ስርዓት መሪዎች ስልጣን ግን እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ ነው፡፡ ምክንያቱም በሀላባ ብሔረሰብ እንደዚህ ዓይነት ስልጣን የሚወረሰው  በ'ታላቅነት' በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ሲባል የሀላባ አገቴ መሪ የሚሆነው "ታላቅ ልጅ /ሰው/ እየተላለፈ የመጣ በመሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የአንድ ጎሣ መሪ /ዳኛ/ ምንም ንግግር አዋቂ ባይሆንና ፍርዱ አሰጣጡ ላይ ብዙም ባይሆን እሱ የዳኝነት ወንበሩ ላይ ዝም ብሎ ይቀመጥና ሽማግሌዎች ጉዳዩን የጨርሱታል እንጂ ከስልጣኑ አያነሱትም(እማም ዝዋር ፣ጥር 30 ፡ 2006 ዓ.ም. ስክርብ፣ 35) ፡፡

- **ባህላዊ ተቋዋሙ በአሁኑ ወቅት ያለበት ደረጃ**

በአሁኑ ወቅት የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት /ኦገቴ/ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ከመንግስታዊው  የፍርድ ቤት የፍርድ አሰጣጥ ይልቅ ተቀባይነትን በማግኘት በጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ይህም የሆነው በዚህ በባህላዊው የፍትህ ስርዓት(ኦገቴ) ምንም አይነት ውሸት፣የሀሰት ምስክር ፣ የገንዘብ ድለላ ስለሌለና ይህንን ችግር ለመፍታት የሚቀመጡት ሽማግሌዎች ያለምንም ክፍያና ማነቃቂያ ባህሉ እንዳይንሻፈፍ ፣  ፍርድ እንዳይዛባ ፣እውነትን እንዳይጓደል ከልባቸው  ስለሚሰሩ ህዝቡ እነሱን በማክበርና ባህላዊ እሴቱን  በመፍራት  በፍቅርና በሰላም ተሳስቦ እንዲኖር  ለማድረግ ስለሚያስችል በጥሩ ደረጃ እየተሰራበት ይገኛል(እማም ዝዋር ፤ ጥር 30፣  2006 ዓ.ም፣ ስክርብ )፡፡

## 3.3 የስርዓቶቹ አከዋወን ሒደት

በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሒደት በብሔረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ የሀላባ ሴራ /ባህል/ ትልቁን ድርሻ የሚወሰደው የአገቴ ስርዓት በየደረጃው ራሱና የቻለና የማይለወጥ ሂደት አለው፡፡ በመጀመሪያ እንደ ሀላባ ባህል አንድ ግጭት ሲፈጠር ቅድሚያ የሚሠጠው የተጎዳውን ሰው መርዳቱ ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በቂም በቀል ተነሳስቶ የአንድ ሰውን ቤት በእሳት ቢያያዝና ቢያቃጥል ማህበረሰቡ በጩኸት ይወጣና ከቻለ እሳቱን ያጠፋዋል፡፡ እሳቱ ግን አሸንፎ ቤቱን ቢያቃጥለው ያ እሳቱን ሊያጠፋ ሆ! ብሎ የወጣ ሠው የተቃጠለውን ቤት ለመተካት ተረባርቦ ቤት ይሰራል፡፡በወቅቱ ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረ የአካባቢው ሰው እንጨት፣ ገመድና ሳር መግዣ ገንዘብ እንዲያዋጣ በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቤቱን ሠርተው ባለቤቶቹን ወደ ቤት ያስገባሉ፡፡ ከዚያ በሁዋላ ነው ጥፋቱን ማን እንዳጠፋና ምን መቀጣት እንዳለበት ማጣራት የሚጀመረው፡፡

እንዲሁም አንድ ሰው የሰው ህይወት ካጠፋ ራሱን ለማትረፍ ለመንግስት /ለፖሊስ/ እጁን ይሰጣል፡፡ በተጓዳኝም ሽማግሌዎችን በማነሣሣት ይህንን ጥፋት ስርቻለሁ እባካችሁ ፍቱልኝ ብሎ ይነግራል፡፡ ይህ ጉዳይ ለማንኛውም ሽማግሌ ሳይሆን ለተወሰኑ በጎሣውም ሆነ በብሄሩ ተሰሚነት ላላቸው ሽማግሌዎች ነው የሚነገረው፡፡ ይህንን የሰሙትም ሽማግሌ ለአቻዎቻቸው መልዕክት በመላክ "ኑ የእገሌ ልጅ ነፍስ አጥፍቷል እሱም ጥፋቱን አምኗልና ተሰባስበን እንነጋገርና መፍትሄ እንፈልግለት "በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ (እነዚህን ሽማግሌዎች ተጠቅሞ በአፋጣኝ መፍትሄ ካልወሰደ የሟች ቤተሰብ በእልህና በንዴት በመውጣት ንብረቱን ሊያቃጥሉበት ፣ህይወት ሊያጠፉበትና ከብቶቹን ሊዘርፉበት ይችላሉ፡፡

ከዚያም ሽማገሌዎቹ ይነጋገሩና ወደ ሟች ቤተሰብ ዘንድ በመሄድ ሟች ያልተቀበረ ከሆነ ሽማግሌዎቹ ሄደው ያስቀብራሉ፡፡ የሟች ቤተሰብንም በመመረቅ 'አላህ ሀዘናችሁን ያቅልል፡፡ያቀዝቀዝ፡፡' ብለው ከመረቁ በኂላ የበዳይ ቤተሠብ ጥፋታቸውን አምነው ጉዳዩን እንዲጨረሱላቸው እንደላኳቸው ይገልፃሉ፡፡ ሽማግሌዎቸ ሄደው ይህንን በሚናገሩበት ወቅት የሟች ቤተሠቦች ምንም ምላሽ አይሰጡም፡፡ ነገር ገን "ያላችሁንን መልዕክት ሰምተናል አሁን ግነ የልጃችን ሀዘን ላይ ነን፡፡" ብለው ይመልሱላቸዋል፡፡ ሽማግሌዎችም

እንደገና አላህ ያጽናችሁ ብለው መርቀው ተመልሰው ይሄዳሉ፡፡ በሁለተኛው ቀንም መጥተው የትናንቱን ጉዳይ እንዴት እንዳዩት ይጠይቋቸዋል፡፡ በዚህ ቀን የሚች ወገኖች ስሜታቸው ከመጀመሪያው ቀን መለስ ያለ ይሆንና መልስ ይሰጣሉ፡፡ መልሳቸውም በቤተሠብ ደረጃ ተነጋግረውና ተመካክረው ሊመልሱላቸው ቀነ ቀጠሮ ይይዙና ሽማግሌዎችን ይሸኟቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁለት ሶስቴ ካመላለሷቸው በኋላ እርቅ እንዲፈፀም ይፈቅዳሉ፡፡

ከዚህ ደረጃ በኋላ ሽማግሌዎቹ ግጭቱ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተፈጠረ በጎሣ መሪው ምርመራ ያካሂዳሉ፡፡ በምርመራውም ተጠርጣሪ ወይም ገዳይ ጉዳዩን ፈጽሞ ከሆነ በመጀመሪያ ጥፋቱን እንዲያምን ማድረግ ዋናው ጉዳይ ነው፡፡ በሀላባ ሴራ አንድ ጥፋት ያጠፋ ሰው ኦገቴው ላይ ከቀረበ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጥፋቱን እንዲያምን ይደረጋል፡፡ ማለትም አድርጎት ከሆነ ማድረጉን አላደረገም ከሆነ ደግሞ አለማድረጉን ይናገራል፡፡ በሽንጎው ላይ ወንጀሉን መፈፀሙን ካመነ ወደመሀላ ደረጃ አይሄድም፡፡ ጥፋቱን ካላመነ ግን ወደ መሀላ ደረጃ ይደርሳል፡፡ ነገር ግን በሀላባ ኦገቴ ስርዓት ላይ ማንም ወንጀል ሰርቶ ስራውን አይክድም፡፡ ምክንያቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ ጠንካራ እሴት ስለሆነ/ ህዝቡ ከልጅነት ጀምሮ ይህንን ባህል ወደ ውስጡ እያሰረፀው የመጣ በመሆኑ/ ያለ ምስክርና ተጨማሪ ነገር ወዲያው ጥፋቱን ያምናል፡፡ ገዳይ ጥፋቱን ቀድሞ ቢያምንም ባያምንም በአገቴው ስርዓት እንደየጥፋቱ ደረጃ የተመደበውን ‘ጉማ’ ወይ ‘ጉዳ’ መክፈሉ አይቀርም፡፡

በእለቱ የውሳኔው ሀሳብ የሚሰጥበት ክርክር የሚደረገው በከሳሽና ተከሳሽ /በዳይና ተበዳይ/ አማካይነት ሳይሆን በኦገቴው ስርዓት በቆርቶዎች አማካይነት ነው፡፡በኦገቴው ሴራ ቆርቶዎች የሚከራከሩት ሁለት የተለያዩ ጽንፎችን በመያዝ ነው፡፡ ይህ ሲባል አንደኛው ቆርቶ የቀረበው ክሱ የሚገባውን ትክክለኛ ፍትህ እንዲያገኝ የሚከራከር ሲሆን ሌላኛው ቆርቶ ግን ፈጣሪ ይቅር እንዲለው በውስጡ በመለማመን ፍርዱን በማዛባት የገዳይን ድርጊት በመደገፍ ይከራከራል፡፡ ይህ የሚሆነው ለአገቴው ተሰብሳቢ ጉዳዩ በደንብ ግልጽ እንዲሆንና ትክክለኛ ብይን እንዲሰጥ ለማድረግ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ የሚያመጡት ከሁለቱ ቆርቆዎች አንዱ ጉዳዩን በደንብ ገልፆ መናገር ካቃተው ነው፡፡ አንደኛው ተበልጦ አንዱ ቆርቶ ብቻ ጉዳዩን እየረታ ካለ የተረታውን በመተካት ‘ጉምጉማ’ ወይም አስተያየት አለኝ በማለት የወማውን ወይም የዳኛውን ፈቃድ

ሳይጠይቁ መናገር ይጀምራሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀጠሉ በኋላ ክርክራቸውን ይጨርሳሉ፡፡ ከዚያም ዳኛው ሚዛን የደፋውን ሀሳብ እንዲመረጡ በድምጽ ብልጫ ያስወስናል፡፡ ከዚያም ወማው  የረታውን ቆርቶ 'እውነቱን ላንተ ሰጥቻለሁ' ይለዋል፡፡ የተረታው ቆርቶሞ 'እኔም ሀሳቤን አንስቻለሁ' በማለት ያበቃል፡፡ ከዚያም በድምጽ ብልጫ የተወሰነው ሀሳብ ላይ ቅጣቱ ይፈፀማል (ሼሀ ከድር ጥር 30፣ 2006 ዓ.ም፣ ስክርብ ፣20) ፡፡

በሀላባ ባህላዊ የእርቅ ስርዓት የየጥፋቱን ቅጣት በየደረጃው አገቴው ያውቀዋል፡፡ በመሆኑም ገዳይ ሟችን የገደለው ሆን ብሎ በቂምና በበቀል ተነሣስቶ ከሆነ ሙሉ 'ጉማ' ይከፍላል፡፡ ሙሉ 'ጉማ' የሚባለው 100 ከብት መክፈል ነው፡፡ እነዚህን 100 ከብቶች የሚከፍሉት በአላባ ባህል አራት መዓዘን በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡ ይህም 1.የገዳይ አባት ወገኖች፣ 2.የአባቱ እናት ወንድሞች /ኢሽማዎች/ 3.የእናት ወገኖች 4. የእናት ወንድሞች /ኢሽማዎች/ አንድ ላይ በመሆን የጉማውን ከብቶች ያመጣሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች ውስጥ የአባት ወገኖች የበለጠውን ድርሻ ይሸፍናሉ፡፡ ነገር ግን ገዳይ ሟችን የገደለው ሆን ብሎ ሳይሆን ሌላ ነገር ለመግደል በወረወረው ወይም በተኮሠው መሣሪያ ከሆነ፤ ወይም በጨዋታ መሃል ከሆነ ሙሉ ጉማ ሳይሆን እንደ ጥፋቱ ደረጃ ግማሽ እንዲሁም ከዚያ ያነሰ ሊከፍል ይችላል፡፡ በተጨማሪም  ግድያው የተፈፀመው ከላይ በተገለፁት አራት መዓዘን ተብለው በሚታወቁት ክፍሎች ውስጥ ከሆነ ጉማ የማይበላበት ሂደት አለ፡፡ ግድያው የተፈፀመው በአራት ማዕዘን ውስጥ ከሆነ ጉዳ ይቀመጣሉ፡፡ ጉዳ ማለት አንድ ቦታ ላይ ቁጭ ብለው የሟችንና የገዳይን ቤተሠብ አንድ ላይ በማድረግ ከሁለቱም ቤተሠብ የገዳይንም ሆነ የሟችን እህቶች ከሌላቸው ደግሞ አክስቶች በማምጣት ማርና ኮሶ ይቀርብና ከአንድ እጅ እንዲበሉና በአንድ ብርጭቆ እንዲጠጡ ይደረጋል(ገራድ ሙንዲኖ ጥር 28፣ 2006 ዓ.ም ስክርብ፣ 16)፡፡

ይህ የፍርድ ሂደት ካለቀ በኋላ ሽማግሌዎቹ ጥፋት ያጠፋውን ግለሠብ ፀጉሩን፣ ቅንድቡንና ሌሎች የሰውነት ክፍሎቹ ላይ ያሉትን ፀጉሮች በሙሉ እንዲላጭ ያደርጋሉ፡፡ ጥፍሩንም ሙልጭ አድርጎ ይቆርጣል፡፡ በመቀጠልም ገዳዩ ሟችን ሲገድል ለብሶት የነበረውን ልብስና ጫማ እንዲሁም የገደለበትንም መሣሪያ በማምጣት እነሱ ላይ በመቆም ይታጠባል፡፡ ፀጉሩን የሚላጨው፣ ጥፍሩን የሚቆርጠውም ሆነ ሰውነቱን የሚያጥበው በማህበረሰቡ ዘንድ 'ፉጋ' ተብለው ከሚታወቁት የሸክላ ሰሪዎች አንድ ሰው

ነው፡፡ እነሱ የሚመረጡበትም ምክንያት ለሁለቱም ወገን በዝምድና ስለማይቀርቡና በደም ስለማይገናኙ ነው፡፡ ከእጥበቱ በኂላ እነዚያ መሣሪያዎችም ሆኑ ልብስና ጫማ ላጠበው ሽክላ ሰሪ ይሰጠዋል፡፡ ገዳዩ መሣሪያው ለሌላ ሰው መሠጠቱ ካሳዘነው ወይም መሳሪያውን የሚፈልገው ከሆነ ውስጥ ለውስጥ ከሽክላ ሰሪው ጋር በመደራደር መልሶ ሊገዛው ይችላል፡፡

በሀላባ ብሔረሰብ የአንድ ለቅሶ ስርዓት የሚያልቀው በሰባተኛው ቀን ነው፡፡ በዚያ ቀን ቤት ይጠረጋል፡፡ በመሆኑም የሽምግልና ሆኑ ሌሎች ጉዳዮች የሚታዩት ከነዚህ የሀዘን ቀናት በኂላ ነው፡፡ ስለሆነም የገዳይ ሽማግሌዎች የዕርቁን ጉዳይ ለመጨረስ በስምንተኛው ቀን ወደ ሙዋች ወገኖች ይሄዳሉ፡፡ በለቅሶው ወቅት ያወጡትን /የሟች ወገኖች/ ወጪ ማለትም ለመስተንግዶ ለከፈን፣ በቀብር የመሣሠሉትን ደምረው እንዲነግራቸው ይጠይቃሉ፡፡ የሟች ቤተሠብም የወጣውን ወጪ ደምረው ይነግሯቸዋል፡፡ ከዚያም የገዳይ ቤተሠብ ወጣ ተብሎ የተናገራቸውን ወጪ በመያዝ በአዲስ መልኩ የሟችን ለቅሶ ይደርሳሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ወቅት ሽማግሌዎቹ ከፊት ሆነው ወደ ሟች ወገኖች ይሄዳሉ፡፡ የገዳይ ወገኖች እያለቀሱ ሲገቡ የሟች ወገኖች ጀርባቸውን ሰጥተዋቸው ይቆማሉ፡፡ እንደዞሩ ነው የሚያለቅሱት፡፡ የገዳይ ወገኖች ደግሞ ፊት ለፊት ነው እያለቀሱ የሚገቡት፡፡ ነገር ግን መሀላቸው ሽማግሌዎች አሉ፡፡ የገዳይና የሟች ቤተሠቦች በለቅሶው ወቅት አይቀላቀሉም፡፡ ለለቀሶ ደራሾቹ እንደ ሌላ ለቀስተኛ የሚታጠቡበት ውሃ አይሰጣቸውም፡፡ ምንም መስተንግዶም አይደረግላቸውም፡፡ ለቅሶአቸውን ከጨረሱ በኂላ ሳያርፉ ወደቤት ይሄዳሉ የገዳይ ቤተሠቦች ከሄዱ በኂላ የሙዋች ቤተሰቦች ለሽማግሌዎች ውሃ ሰጥተው ያሳርፏቸዋል፡፡ ከዚያም ሽማግሌዎቹ "ዛሬ የመጣነው ለቀሶ ለመድረስና ለለቅሶው ስርዓት፣ ለቀብርና ከፈን ያወጣችሁትን ወጪ ለመክፈል ስለሆነ የሚቀበል ሰው ስጡን" ይላሉ፡፡ ከዚያም ብሩ ይሰጣል፡፡ ወዲያውም የእርቁ ቀን ይወሰንና በተወሰነው ቀነ ቀጠሮው በገዳይ ቤተሠቦች ዘንድ ይሆናል፡፡ ዕርቁ በዚያው ይፈፀማል፡፡

- **የዕርቅ አከዋወን ስነስርዓት**

በዕለቱ የገዳይ ቤተሠብ ለካሣ የሚሆን ምርጃሞ /የኮርማ ቅጣት/ ማር፣ ቡልኮና ከገዳይም ከሟችም ቤት ለሚመረጡት ሁለት ሴቶች ነጠላ በማዘጋጀት እቤታቸው ሆነው የሟችን ቤተሠብ ይጠብቋቸዋል፡፡

ለእርድ የተዘጋጀውም ጥቁር የቀንድ ከብት፣ ማርና ኮሶ ይዘጋጃል፡፡ ለጉዳ የሚመጡት ሰዎች ወደቤት ከመግባታቸው በፊት ከሁለቱም ቤተሠቦች የመጡት ሁለት ሴቶች የተሰጣቸውን ነጠላ ለብሰው የሚች ወገን የሆነችው ሴት ማር ይዛ በመግቢያው በቀኝ በኩል፣ የገዳይ ወገን የሆነችው ሴት ደግሞ ኮሶ ይዛ በግራ በኩል ቆመው ይጠብቋቸዋል፡፡ ከዚያም ሰዎቹ በሚገቡ ሰዓት ኮሶ የያዘችው ሴት በእርጥብ የግራዋ ቅጠል ኮሶውን በጉዳው ሰዎች እግር ስር ትረጨዋለች፡፡ በመግቢያው ቀኝ በኩል ያለችው ከሚች ቤተሠብ የተወከለችው ሴት እንዲሁ በእርጥብ የግራዋ ቅጠል ማሩን እግራቸው ስር ትረጨዋለች፡፡ ይህም የሚደረገው ኮሶ የመረጨቱ ጉዳይ የደረሰው አደጋ ወይም ግድያ በጣም መራራና እንደ ኮሶ የጎመዘዘ እንደሆነ ለማመልከት ነው፡፡ የማር መርጨቱ ሥርዓት ደግሞ በሚች ቤተሰብ ተፈጥሮ የነበረው ሃዘን መራራ ቢሆንም በዕርቁ ምክንያት ሀዘናችን አልፎ ጣፋጭ ሰላምና ፍቅር ይግባ የሚል መልዕክት አሰቡ፡፡

ከዚህ በመቀጠል የጥቁር እንስሳ እርድ ይከናወናል፡፡ ለዕርድ የሚቀርበው እንስሳ መልኩ ጥቁር ሲሆን ከፍየል ውጪ ማንኛውም የቀንድ ከብት ሊሆን ይችላል፡፡ ጥቁር የሚመረጥበት ምክንያትም በሚች ቤተሠብም ሆነ በገዳይ በኩል የደረሰው ነገር በጣም የከፋና መራራ፣ ክፉ መከራና እንደ ጨለማ የከበደ ሀዘን መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡ ፍየል ጭራዋ አጭር፣ ወደላይ የተቀለበሰና ሃፍረቷን የማትሸፍን በመሆኗ በማናቸውም የዕርቅ ሥርዓቶች ላይ ለእርድ አትቀርብም፡፡ በደረሰው የግድያ ሁኔታ ምክንያት ሁለቱም ቤተሰቦች መካከል ተፈጥሮ የነበረው ችግር፣ መከራና ስቃይ ተገፍፎ ወደ ብርሃን የሚቀየረው ጥቁር መልክ ያለው እንስሳ የታረደ ሲሆን ብቻ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ግድያው ከተፈፀመበት እለት ጀምሮ ሁለቱም ቤተሰቦች ከማህበሪዊና ኢኮኖሚያዊ የጋራ መስተጋብሮች በእጅጉ ተለያይተው የቆዩ በመሆናቸው በመጨረሻዋ የዕርቅ ዕለት ከጥቁር እርድ ሥነ-ሥርዓት በኋላ ፊት ለፊት ይተያያሉ ፡፡ በእርቁ ዕለት የገዳይ ቤተሠቦችም ሆኑ የሚች ቤተሠቦች እርዱ በሚከናወንበት ቦታ የእንስሳው ደም እስኪፈስ ድረስ ፊት ለፊት እንዳይተያዩ ፊታቸውን አዙረውና ጀርባ ለጀርባ ተሰጣጥተው ማዶ ለማዶ ነው የሚቆሙት፡፡ እርዱ ተፈጽሞ ደም ከፈሰሰ በኋላ ፊታቸውን በማዞር እርስ በርስ ይተያያሉ፡፡ ከዚያም ወዲያው የታረደውን እንስሳ ሆድቃ በመክፈት አንጀቱን በማውጣት ታልቦ እነደሰንሰለት እየተጠላለፈ ይገመዳል፡፡በመቀጠል የሚችና የገዳይ ወገኖች የተገመደውን አንጀት ተቃራኒ ጫፎች ይዘው

ይማማላሉ፡፡እንዲሁም ቀሪዎቹ የገዳይ ቤተሰቦች የፈሠሠውን የእንስሳ ደም እየተሻገሩ ወደ ሟች ወገኖች ይቀለቀላሉ፡፡ ከዚያም ወደቤት ይገባሉ፡፡ አስከትሎም የገዳይ ቤተሠብ ገዝቶ ያስቀመጠውን ትልቅ ቡልኮ ያመጣል፡፡ የገዳይም ሆነ የሟች ቤተሠብ ክብ ሰርተው ይቀመጡና ያን ትልቅ ቡልኮ በዙሪያቸው ይለብሱታል፡፡ በመቀጠል ከታረደው እንስሳት ስጋ በጥሩ ሁኔታ የተሠራ ክትፎ ይመጣል፡፡ ክትፎውንም በገዳይ እጅ /እፍኝ/ ላይ ይቀመጣል፡፡ መጀመሪያ የሟች አባት ከገዳይ እጅ ላይ ክትፎውን በአፉ እንዲበላ ይደረጋል፡፡ በዚህ መልኩ ገዳይም ከሟች አባት እጅ ይበላል፡፡ ከአንድ እጅ መብላትና በአንድ በልኮ መጠቅለልና መቀመጥ ከምንም በላይ የገዳይንና የሟችን ወገኖች አንድ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ጉዳና ጉማ ሲደረግ ሁሉም ነገር ተመልሶ ተቆራኘ ማለት ነው፡፡የተጠቀለሉበትን ቡልኮ ለሟች ቤተሰብ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ለሟች ቤተሠብ ለጉማ ከተከፈለው ታክሎ ሁለት ከብት ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የእርቁ ስነ ስርዓት ይፈፀማል፡፡ ነገር ግን ይህንን ሁሉ ነገር በጉዳና በጉማ ጨርሰው ሠላም ከፈጠሩ በኋላ ለበቀል የሚያስብ፣ ህግ ቦታ ሄጄ እከሳለሁ የሚል እንዲሁም በስውር ገዳይን እበቀላለሁ ብሎ የሚያስብ ካለ ከሀላባ ሴራ ይወጣል፡፡ ይወገዛል፡፡ እዚህም አልፎ መሀላና ግዝትአፍርሷልና በራሱ ላይ ችግር ይፈጥራል (ገራድ ሙንዲኖ ጥር 28፣ 2006 ዓ.ም.፣ስክርብ፣17)፡፡

በአገቴው ስርዓት ላይ ጥፋቱን ያመነውና በስርዓቱም ቅጣት የተጣለበት ግለሰብ ዋስ እንዲጠራ ይደረጋል፡፡ ይህ ሂደት በሀላባ ባህል "ሩበቴ" ተብሎ ይጠራል፡፡ አቻ ፍቺው ዋስ ማለት ነው፡፡ ለአገቴው እለት ተከሳሽ ጥፋቱን ካመነ በኋላ በቆርቶዎቹ አማካይነት የጥፋቱ መጠንና ሂደት በክርክር ከተካሄደ በኋላ መሪው /ወማው ለተሰብሳቢዎቹ "ምን ይደረግ" ብሎ ይጠይቃል፡፡ አገቴውም በአንድ ድምጽ "ይቀጣ" ይላል፡፡ መሪው መልሶ "ምን ይቀጣ" ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደ አገቴው ህግ ጥፋተኛው በመጀመሪያ ዋስ እንዲጠራ ይደረጋል፡፡ ጥፋተኛውም ይዋሰኛል ብሎ ያሰበውን ሰው ይጠቁማል፡፡ ምክንያቱ ጥፋተኛውን በተመለከተ የተጣለበትን ቅጣት በተወሰነው የጊዜ ገደብ እንዲከፍል እንዲያስገድደውና ምናልባትም ጥፋተኛው ከአካባቢው ቢሠወር እነዚህን ጉዳዮች ለማስፈፀም ሀላፊነት የሚወስድ ሰው ለማስቀመጥ ነው፡፡ ጥፋተኛውም ይህንን ጉዳይ ባይፈጽምና ከአካባቢው ቢሠወር ዋሱ በሀላፊነቱ መሠረት ተጠያቂ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ይህ ሁኔታ ተከስቶ ዋሱ ከነ ቤተሠቡ ችግር

ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉ ጥፋተኞች አይስተዋሉም፡፡ በተቃራኒው ዋሱ ችግር ውስጥ እንዳይገባና እንዳይቸገር በማሠብ ጥፋተኛው ለሽንጎው ውሳኔዎች በመገዛት ሁሉን ይፈጽማል፡፡

በአገቴው ስርዓት ላይ የተላለፈውን ሁሉ በመሻር በቂም በቀልም ሆነ በማንኛውም ጠብ በሚያጭር መልኩ በሌላው ላይ የሚነሳ ወገን በሽማግሌዎች ዘንድ እርግማን ይደርስበታል፡ በማህበረሰቡም ዘንድ ደግሞ መገለል ያጋጥመዋል፡፡ ማህበረሰቡም፤ ቢታመም አይጠይቀውም፣ እቤቱ ላይ እሳት ቢነሳ አይደረስለትም፣ ቢሞት አይቀብረውም፡፡ ሌሎች ከዚህ ጋር የተገናኙ ጉዳቶች ሁሉ ያደርሱበታል (ገራድ ሙንዲኖ ጥር 28፣ 2006 ዓ.ም.፣ ስክርብ፣17) ፡፡

## 4. የግጭት መፍቻ ተቋማት በሀላባ ብሄረሰብ

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሰዎች በአንድነት ሲኖሩ የተለያዩ ግንኙነቶች ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እነዚህንም በጎ የሆኑና አሉታዊ ግንኙነቶች በማለትም ልንፈርጃቸው እንችላለን፡፡ ከነዚህ ውስጥ ግጭት አንዱ ገጽታ ነው፡፡ ግጭት ደግሞ ስር ሳይሰድና ሳይጠናከር ቶሎ እርምጃ ካልተወሰደበት ትልቅ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ይህንንም ግጭት የማስወገድ እርምጃ የሚተገብሩ ተቋማት ማቋቋም በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም በሀላባ ብሄረሰብ ግጭትን በመፍታት ላይ የሚገኙ ሁለት ዋና ዋና ተቋማት ይገኛሉ፡፡

### 4.1 ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም

በሀላባ ብሄረሰብ ከመንግስታዊ የፍትህ መስጫ ተቋም (መደበኛ ፍርድ ቤት) ጎን ለጎን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማስወገድና ከምንጫቸው ለማድረቅ በከፍተኛ ደረጃ በመስራት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ይህም ተቋም ከላይ ወደታች ወይንም ከታች ወደላይ በመዋቅር በመደራጀት የህብረተሰቡን ግጭቶች ለመፍታት የሚያገለግል ባህላዊ እሴት ነው፡፡ በአወቃቀሩም አራት ደረጃዎችን ሲይዝ እነሱም የቤተሰብ ሸንጎ (ሚኒ ኦገቴ) ፣የቤተዘመድ ሸንጎ (ቦኪ ኦገቴ)፣የጎሳ ሸንጎ (ደቦ ኦገቴ) ና የሀላባ ሸንጎ (ሃላቢ ኦገቴ/ጎጎታ) በመባል ተግባሩን በደረጃ ይከውናል፡፡የየደረጃው ኦገቴ አካላት ተግባርና ሃላፊነት ከዚህ ክፍል በፊት በተዘረዘሩ ክፍሎች ቀርቧል፡፡በተቋሙ ውስጥ ከፍተኛውን ስራ የሚሰሩት የሃገር ሽማግሌዎች ፣ የሃይማኖት አባቶችና የጎሳ መሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት ለባህላዊው የእርቅ ስርዓት የሚመረጡት በሁለት መንገድ ነው፡፡

የመጀመሪያው ከሳሽና ተከሳሽ ውይም በዳይና ተበዳይ ጉዳያቸውን እንዲያዩላቸው የየራሳቸውን ሽማግሌዎች እንዲመረጡ ይደረጋል፡፡ በዚህም ሂደት ከሳሽ ለሱ የሚሆኑትን ፤ተከሳሽም ለራሱ የሚበጁትን ሽማግሌዎች ይመርጣሉ፡፡ምረጫው በራሳቸው ፍላጎት የሆነበት ምክንያት የሚመረጡት ሽማግሌዎች ፍርድ እንዳያጓድሉባቸው በማሰብ ነው፡፡ ለምሳሌ በዳይ የመረጣቸው ሽማግሌዎች ውስጥ ተበዳይ ያልተስማማው ሽማግሌ ካለ ሊያስቀይር ይችላል፡፡ ተበዳይም እንዲሁ፡፡ እነዚህም ሽማግሌዎች የተመረጡት ይህንን ጉዳይ ብቻ ለመፍታት ስለሆነ ሌላ ጉዳይን

ለመሽምገል እንደገና መመረጥ ይኖርባቸዋል። ማለትም አንዴ ከተመረጡ አገልግሎታቸው ለአንዴ ብቻ ነው።(ሼህ ከድር፡ ጥር 28፣ 2006 ዓ፣ም. ስክርብ ፣21)። ይህንንም የሚያደርጉበት ዋናው ምክንያታቸው በዳይ ወይም ተበዳይ በማይፈልጉት ሽማግሌ ከተሽመገሉ በደል ለደርስብን ይችላል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድም የሚከተለውን ታሪክ ይነግሩናል።

> ተረክ 6. ሺፋ ሙራድና ዘመዴ ዳርሰቦ የተባሉ ሰዎች መጠጥ ቤት ገብተው ሲጠጡ በድንገት ተጣልተው በተቀሰቀሰ ጠብ ሺፋ በያዘው ዱላ ዘመዴን ጭንቅላቱን ፈንክቶት ነበር። ጥቃት የደረሰበት ዘመዴ ሽፋን በፍርድ ቤት ከስሶና ምስክር ቆጥሮ ሊያስፈርድበት ሲል ሺፋ ለጎሳው ሽማግሌ ጉዳዩን በባህላዊው መነንገድ እንዲፈቱለት ጠየቀ።ሽማግሌውም ጉዳዩን እኔ በቤተሰብ እፈታዋለሁ ብለው ለእርቅ ኣመጡት። ከዚያም ሺፋንና ዘመዴን የየራሳቸውን ሽማግሌ እንዲመርጡ አስደረጉ።በዚህ ወቅት ዘመዴ ሺፋ ከመረጣቸው ሽማግሌዎች አንዱን በደርግ ጊዜ አባቴ በፖለቲካ ምክንያት አሳስሮት ስለነበር አሁን በዚህ አጋጣሚ ሊበቀለኝ ይችላል ስለሆነም አልስማማም በማለት የመረጠውን ሽማገሌ ሽማግሌ እንዲሰርዝ አድርጎታል። ከዚያም ሺፋ ሌላ ሽማግሌ ጠቆመ። ዘመዴም በሁለተኛው ምርጫ ተስማማና ወደ እርቁ ስረአት ገቡ።በስርዓቱም ሺፋ ጥፋቱን ስላመነ ዘመዴ ለህክምና የወጣውነ ገንዘብ፣ ለሰውነቱ መጠገኛ የሚያስፈልጉትን ምግቦች የሚገዛበትን ሁለት መቶ ብር እንዲከፍል ተወሰኖበት ስርኣቱ አብቅቷል(እማም ዝዋር፡ ጥር 30 ፣2006 ፣ዓ.ም. ስክርብ ፣ 34)።

ሁለተኛው በብሄረሰቡ ባህልና እምነት መሰረት ዋናውን የሃላባ ሸንጎ /ሀላቢ አገቴ/ የሚመራው በብሄረሰቡ ሲዶ ተብሎ ከሚጠራው ጎሳ ታላቅ ልጅ (ሰው) ልጆች በተዋረድ የሚወረስና በቋሚነት የሚያገለግል ነው (አቶ ሃቢብ ሸኩራህ፡ የካቲት 16፣2006 ዓ. ም. ስክርብ፣ 42)።

## 4.2. ዘመናዊ የፍትህ መስጫ ተቋማት

እንደማንኛውም የሃገሪቱ ክልል፣ ዞንና ወረዳ የሀላባ ልዩ ወረዳም የአካባቢውን ሰላም ለመጠበቅ ፣ ህዝቡ በሰላም እንዲኖርና ጸጥታን ለማስጠበቅ ከባህላዊው የፍትህ መስጫ ተቋም ጎን ለጎን ዘመናዊውን የፍትህ መስጫ ተቋማት ይጠቀማል። እነዚህ ዘመናዊ የፍትህ ተቋማት በህበረተሰቡ ውስጥ ሰላምን ለመፍጠር በቀበሌ ደረጃ ከተቋቋመው የቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ጀምሮ ፖሊስና ፍርድ ቤትን በዋናነት በማቀፍ ለህብረተሰቡ ሰላም በትጋት እየተሰራበት የሚገኝ መንግስታዊ ተቋም ነው።

# 5. በመደበኛ ፍርድ ቤትና በአላባ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት /አገቴ/ መካከል ያለ ግንኙነት

በሀላባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት /አገቴ/ና መደበኛው ፍርድ ቤት በተጠናከረ መልኩ በጥምረት በመስራት ላይ ይገኛሉ። ለዚህም እንደምክንያት ሆኖ የሚያገለግለው ባህላዊው የዳኝነት ስርዓቱ የራስ የሆነ ተዋረዳዊ መዋቅር ያለው ስለሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩት የደረጃ ግጭቶች ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ሳይደርሱ እዚያው ስለሚያልቁ ነው። ይህም ሲባል ይህ በማህበረሰቡ ውስጥ የማፈጠር ብዙ ግጭት ባህላዊውን የፍትህ ስርዓት ተሻግሮ ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ቢሄድ ይህ ክፍል ካለበት የባለሙያ እጥረት፣ ጉዳይየማጣሪያ ጊዜና የማቆያ ቦታ ማነስ አንፃር ፍርድ ቤቱም ሲቸገር ከሳሽ ሆነ ተከሳሽም ሊጉላሉ ይችላሉ። በመሆኑም መደበኛው ፍርድ ቤት ወደ ባህላዊው ስርዓት /አገቴ/ ይልካቸዋል። በዚህ ምክንያት በወረዳው ውስጥ የሚፈጠሩ ማናቸውንም ዓይነት ግጭቶች በአንድ ላይ ይፈታሉ (አህመድ ናስር፡መጋቢት 4፣ 2006 ዓም ፣ ስክርብ ፣22)።

## 5.1. የአገቴው ሚና በሀላባ በሚፈጠሩ ግጭቶች ላይ

የሀላባ አገቴ በአሁኑ ወቅት በወረዳው ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ከመፍታት አንፃር ከፍተኛውን ድርሻ በመውሰድ እየሰራ ይገኛል። ፍትህን ለመስጠትና በዳይን ለመቅጣት የሚቀመጡት አካላት ደመወዝን መሰረት በማድረግ የተሰየሙ ሳይሆን ከወላጆቻቸው ሲተላለፍ የኖረውን ፍትሀዊ ስርዓት ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ የቆሙ በመሆናቸው፣ እንዲሁም ፈጣሪን በመፍራትና የማህበረሰቡ ዋና እሴት የሆኑትን ሰላምንና በሰላም አብሮ መኖርን ለመፈፀም የተሠየሙ ናቸው። ስለሆኑም ያለምንም ማዛባትና ማዳላት እውነቱን ስለሚፈርዱ ነው ማህበረሰቡ ይህንን ስርዓት የሚመርጠው(አምባዬ መጋቢት 2፣ ፣ 2006 ዓ፣ም. ስክርብ፣30)።

ለምሳሌ፡- በመደበኛው ፍርድ ቤት የሚከናወነውን የፍርድ ስርዓት ብንመለከት ለምስክርነት የሚቆጠሩት ሰዎች በገንዘብ በመደለልና ለዘመድ በማድላት እውነተኛ ያልሆነ የምስክርነት ቃል በመስጠት ፍርድ እንዲንሻፈፍ ሊያደርጉ ይችላሉ።ነገር ግን በአገቴው ስርዓት ላይ የሚሠጠው የምስክርነት ቃል ከዚህኛው ፈጽሞ የተለየና

በፍርሃትና እውነትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡በዚህ ሂደትም እውነተኛው ጥፋተኛ ይገኛል፡፡ ትክክለኛ ብይንም ይሰጣል(አህመድ ናስር ፡ መጋቢት 4፣ 2006 ኣ.ም፣ ስክርብ፣ 18)፡፡

## 5.2. በሀላባ ማህበረሰብ ዘንድ የአገቴው ስርዓት ተመራጭነት

የሀላባ ኦገቴ ስርአት በማህበረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ሆኖ ሲሠራበት ቆይቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የተለያዩ ግጭቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ጉዳዮቹን ለመፍታትና ግጭቶችንም ከስራቸው ለማጥፋት በሚደረገው ክዋኔ መሠረት ህብረተሰቡ ስለሚረካና የውስጡን በደልና ጥፋተኝነት በተለያዩ ሁኔታዎች እንዲቀረፍ ስለሚያደረግ ነው፡፡ ይህንንም በሚያደርግበት ወቅት የሚከተላቸው ስርዓቶች ማለትም መሀላዎች፣ እርግማኖች፣ ምርቃቶች፣ ጭዳዎችና ካሣዎች ሂደቱ ትክክለኛ እንደሆነና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሳይዛነፍ የተላለፈ እንደሆነ ስለሚያስረዳቸው ነው፡፡ በዚህ መሠረት በማህበረሰቡ ዘንድ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ተበዳይ ፍትህ ማግኘት ሲፈልግ በመጀመሪያ ደረጃ የሚመርጠው ባህላዊውን የፍትህ መስጫ ስርዓት /አገቴ/ን ነው (አህመድ ናስር ፡ መጋቢት 4፣ 2006 ኣ.ም ፣ስክርብ ፣18)፡፡

ማህበረሰቡ ኦገቴውን የሚመረጥበት ዋና ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው ፍትህ ሳይዛነፍ ብይን ስለሚሰጥና በዚህ ስር የሚደረገው የእርቅ ስነ ስርዓትም ከሆድ የሆነና በድጋሚ ለቂም በቀል የማያነሣሣ ስለሆነ ነው፡፡ ለአብነትም፡-

ተረክ .6 በሀላባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ቁፌ በሚባል ቀበሌ ውስጥ በምትገኝ አንዲት ኩሬ ውስጥ አንድ ሰው ሞቶ ተገኘ፡፡ ገደዩ አልታወቁም ነበር፡፡ የሟች ቤተሠብ ገድለዋል ብለው የጠረጠሯቸውን ሰዎች በመደበኛ ፍርድ ቤት ከሰሷቸው፡፡ የሀሰት ምስክር በማምጣትም ሰዎቹ 13 ዓመት እያንዳንዳቸው እንዲታሠሩ ፈረዱባቸው፡፡ ነገር ግን ተከሳሾቹ ይግባኝ ጠይቀው ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ ታይቶላቸው በነፃ ተለቀቁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች በነፃ ቢለቀቁም በማች ቤተሠብ ዘንድ በገዳይነት ተጠርጥረዋልና ተመልሰው ወደ ቀያቸው ሊሄዱ አልቻሉም፡፡ ስለሆነም ሽማግሌዎች ጉዳዩን ያዙት፡፡ ተጠርጣሪዎቹን ገድለው እንደሆነ ለማወቅ የሚችሉትን ሁሉ አደረጉ፡፡ ነገር ግን ምንም ፍንጭ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ ተጠርጣሪዎቹን ሟችን አልገደልንም ስትሉ ይህንን ጥቁር በግ እረዱ ተባሉ፡፡ ተጠርጣሪዎችም አልገደልንም ብለው ጥቁሩን በግ አረዱ፡፡ የሟች

ቤተሠብንም እንዲሁ ተጠርጣሪዎቹ ሚችን ገድለዋል ብላችሁ እረዱ አሏቸው፡፡ የሚች ቤተሠቦች ፈሩና ሳያርዱ ቀሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ ተጠርጠሪዎቹ እንዳልገደሉ በመረዳት ሁለቱን ቤተሠብ ጉዳያቸን በእርቅ እንዲያልቅ አደረጉት (አቶ እንዳለ ፡ጥር 29፣ 2006 ዓ.ም. ስክርብ፣ 14)፡፡

ከላይ የተገለጸውን ተረክ ስናነበው በባህላዊው የፍትህ ስርዓት የማያልቅና የማይፈታ ምንም ነገር እንደሌለ ነው የተረዳነው ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ጠንከር ያለ መንግስትን፣ ፖለቲካውንና ሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮችን የሚነኩ ግጭቶች ሲፈጠሩ ከባህላዊው የግጭት መፍቻ ሰርዓት ይልቅ መደበኛው ፍርድ ቤት ጣልቃ ይገባበታል፡፡ ለምሳሌ የሴት ልጅ መደፈርና መጠለፍ የመሣሠሉት መንግስታዊ ትኩረት ያገኙ ጉዳዮችን አገቴው ሊጨርስ ቢችልም መደበኛው ፍርድ ቤት ይይዘዋል፡፡ በተለይ የነፍስ ግድያ ጉዳይ ቀድሞ ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ከገባና ጉዳዩ ከሌሎች ነገሮች ጋር የተየያዘ ምሳሌ እንደ ፖለቲካ ቅስቀሳ፣ ብሔረሰብን ከብሔረሰብ የሚያጋጭ ዓይነት ከሆነ የእስር ፍርድ ይጠብቃዋል፡፡ የሀላባ ወረዳ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት ተወካይ አቶ አህመድ ናስር ገጠመኛቸውን እንዲህ የቀርባሉ፡፡

ተረክ 7 መቃላ በሚባል አካባቢ /ቀበሌ/ ሰዎች ሆነ ብለው ተነስተው የሰዎችን ቤት በእሳት አቃጥለው ነበረ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ውስጥ ከእሳቱ ሊያመልጡ የማወጡ ሠዎችንም ገድለው ነበር፡፡ በዚህም ጎሣ ከጎሣ ከፍተኛ ግጭት ፈጥረው ለቁጥጥር ሁሉ አስቸግረው ነበረ፡፡ ነገር ግን የአካባቢው ሽማግሌዎች ወደ ፍርድ ቤት በመምጣት ጉዳዩን እነርሱ ሊጨርሱት እንደሚችሉ በመግለጽ ለነሱ እንዲሰጣቸው ጠየቁ፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በዋናነት ከመሩትና ከጠነሰሱት እንዲሁም ነፍስ ካጠፉበት ሁለት ሰዎ ውጪ የቀሪዎቹን ጉዳይ አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ የነዚያም ሰዎች ጉዳይ በአገቴው አልቆ ጥፋተኞቹ እንደየጥፋታቸው መጠን ካሣ እንዲክሱ በማድረግ ወደ ማህበረሰቡ ቀላቅሏቸዋል (አህመድ ናስር፡ መጋቢት 4፣ 2006 ዓ.ም. ስክርብ፣ 23)፡፡

በዚህ ዓይነቱ የፍርድ ሂደት ውስጥ ኦገቴው ትልቁን ሚና ቢጫወትም አንዳንድ ጊዜ ተበዳዮች በዳያቸው እነሱ የደረሰባቸው ዓይነት ችግር እንዲደርስበት በማሰብ ከአገቴው ይልቅ መደበኛውን ፍርድ ቤት በመምረጥ እዚያ ይካሰሳሉ፡፡

በሀላባ ብሔረሰብ ውስጥ መደበኛው የፍርድ ስርዓትና ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት በመተባበርና በመደጋገፍ በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ውስጥ በአጋጣሚም ይሁን ሆነ ተብሎ በሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች ላይ ሁለቱ የፍትህ ተቋማት በትብበር

በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ አንድ ላይ የሚሠሩባቸው ሂደቶችም ግጭቶች ሁሌም በማህበረሰቡ ውስጥ አሉ፡፡ በየደረጃው የሚፈጠሩ እነዚህ ግጭቶች ሁሉም ወደ ፍርድ ቤት ሊመጡና ሊዳኙ አይችሉም፡፡ እንደየደረጃቸውና ዓይነታቸው በባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት ያልቃሉ፡፡ በዚህም መልኩ ባህላዊው  የፍትህ ስርዓት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ስራ በዚህ መልኩ ሲረዳ ይታያል፡፡ በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙት የማህበረሰቡን ሰላም ለማስፈን እና ህብረተሰቡም በተረጋጋ መልኩ እንዲኖር እንዲሁም ወንጀለኞችን ለመቅጣት በመሆኑ ከዚህ ዓላማው ጋር በመመሳሰል የማህበረሰቡን ሰላም ለመጠበቅና ህብረተሰቡ በባህላዊው መንገድ ትውፊቱን ጠብቆ እንዲኖርና ባህሉን እንዲንከባከብ የሚያደረገው ኦገቴም በትብብር ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ሰላም ተጠብቆ በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳይቆይ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ በቂም በቀል በመነሣሣት ለጥፋት መዘጋጀት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሰላም እንዲፈርስና ህዝቡ በተረጋጋ ሁኔታ እንዳይኖር ያደርገዋል፡፡ ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት ደግሞ ይህንን ሰላም የሚያደፈርስ ቂምና በቀል በመሃላ፣ በካሳና በሌሎች ባህላዊ ጉዳዮች ሲጨርስ ይስተዋላል፡፡ ይህ ነገር በመቅረቱ ደግሞ በዚህ ምክንያት እየተፈጠሩ ፍርድ ቤትን የሚያጨናንቁ ጉዳዮች ከምንጫቸው ይደርቃሉ፡፡ ስለሆነም መደበኛው ፍርድ ቤትና ባህላዊው የፍትህ ስርዓት በትብብር ይሰራሉ፡፡ ጠቅለል ሲል መደበኛው ፍርድ ቤትና ባህላዊው የፍትህ ስርዓት በመተባበር የተፈጠረ ግጭትን በማስወገድና ሌላ ግጭት እንዳይፈጠር በማድረግ በሀላባ ልዩ ወረዳ ውስጥ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

# 6. ትንተናና ቁዘማ

ሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ ያለውና ለረጅም ዘመናት በማህበረሰቡ ውስጥ ስለቆየ በተለያዩ ገጽታዎች የማህበረሰቡ እሴት ሊሆን ችሏል፡፡

## 6.1. የባህላዊ የፍትህ ስርዓት እሴቶች

- *ሀይማኖታዊ እሴቶች*

የሀላባ ብሔረሰብ ከ99% በላይ የእስልምና ተከታይ እንደመሆኑ መጠን (የደቡብ ብ/ብ/ፕሮፋይል 2004፣11)ሀይማኖታዊ ህጉንና ስነ ምግባሩን ጠብቆ ይኖራል፡፡ ከዚህም በተጓዳኝ ባህሉን በተሻለ መልኩ ጠብቆ መገለጫው በማድረግ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖታዊው አኗኗር ባለበትና ብሎም በተሻለ መልኩ ከባህሉ ጋር ተስማምቶ እዲቀጥል በማድረግ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ ላይ የፍትህ አሰጣጡ እንዳይጓደል፣ተበዳይ እንዳይጉላላና . መጥፋተኛው እንዲታረምና ለበደሉ ቅጣት እንዲቀበል በማድረጉ በኩል  የሀይማኖት መሪዎች አስተዋጽዖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም የአላባ ብሔረሰብ ከእምነቱ ጋር ባህላዊውን ስርዓት በማስማማት የህዝቡን ሰላም እየጠበቀና ግጭትን እየፈታ ይገኛል፡፡

- **ኢኮኖሚያዊ እሴቶች**

የሀላባ ብሔሰብ ዋና የኢኮኖሚ ምንጭ ጥምር  ግብርና  ነው፡፡ ይህም ሲባል ማህበረሰቡ የሚተዳደረው ከብት በማርባትና ሰብል በማምረት ነው፡፡ የብሄረሰቡ  አባላት እንደ ማንኛውም የሀገሪቱ ብሔረሰቦችም የእርሻው ውጤት ከእጅ ወደ አፍ ደረጃ ያልዘለለ በአመት የበልጉን ዝናብ ጠብቆ የሚያመርት ህብረተሰብ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ ኑሮው ከዕለት ወደ ዕለት ለውጥ የሌለውና ተመሳሳይ (አሰልቺ) ነው፡፡ በዚህም የግብርና ስራ እንዳይተዳደሩ ያለው የእርሻ መሬት ውስን ነው፡፡በመሆኑም አብዛኛው የገጠር ወጣት በእርሻው መጥበብ /ማነስ/ና በምርቱም ባለመርካት ወደ ከተማ በመሄድ የተለያዩ የጉልበት ስራዎችን በመስራት ኑሮውን ይገፋል፡፡ እንደዚህ በመሆኑ ምክንያት በሀላባ ውስጥ ዋና ዋና የግጭት መንስዔ ከሚባሉት ጉዳዮች አንዱ የኢኮኖሚ ችግር  ሆኖአል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ምርታቸውን ከፍ ለማድረግ የአጎራባች ህዝቦችን ድንበር

በመግፋት፣ ለከብቶቻቸው መኖ መግዣ ሲያጡ ሌሎች ሰዎች የግጦሽ ቦታ ላይ ከብቶቻቸውን በመልቀቅ በሚያስግጡበት ወቅት ከሰዎች ጋር ግጭት ውስጥ በመግባት እርስ በርስ ሲቆራቆዙ ቆይተዋል፡፡ በሌላ መልኩ በሃላባ ብሄረሰብ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና ዘርን ለመተካት እንዲሁም ኑሮን በመተጋገዝ ለመግፋት ትዳር መመስረት አንዱ ነው፡፡ ይህንን ማህበራዊ ተቋም ለመመስረት ደግሞ ባህላዊ ግዴታዎችን መፈጸም ወሳኝ ነገር ነው፡፡ እነዚህም ግዴታዎች ወንዱ ለሚያገባት ሚስቱ ቤተሰብ ጥሎሽ መክፈል አለበት፡፡ በመሆኑም ወንዶች ትዳር ሊመሰርቱ ሲፈልጉ በገንዘብ እጦት ምክንያት /ገበራ/ጥሎሽ ለመክፈል ሲያቅታቸው የሚወዷትን ልጅት ላለማጣት ህጋዊ ባልሆነና ግጭት ሊፈጥር በሚያስችል መልኩ በጠለፋ ትዳር ይመሰርታሉ፡፡ በጠለፋው ምክንያት የሴት ቤተሰብ ተደፈርኩ በማለት ለጠብ ይዘጋጃል፡፡ በአጠቃላይ ባህላዊው የፍትህ ተቋም በኢኮኖሚ ምክንያት የሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶች ለማስወገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

- **ማህበረ ባህላዊ እሴቶች**

በሀላባ ብሔሰብ ባህል ትልቅ ቦታ አለው፡፡ ይህንንም ማረጋገጥ የሚቻለው በማህበራዊ ህይወት መስተጋብራቸው ሁሉ ባህላቸውን ማንፀባረቅ መቻላቸው ነው፡፡ ለዚህም መገለጫው በበሔረሰቡ ዘንድ በየአመቱ  የሚከበረውን  የሀላባ ሴራ በዓል በብሔረሰቡ ውስጥ ባሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እድሜ፣ ፆታ፣ ሃይማኖትና  ማህበራዊ ደረጃ ሳይወስነው በየዓመቱ በታህሳስ ወር መጨረሻ በደመቀ ሁኔታ በሀላባ እግር ኳስ ስቴድየም መከበሩ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማህበረሰቡን ባህል በማክበር በብሔረሰቡ ውስጥ ትልቅ ግጭት ቢነሣና የሰው ህይወት እንኳን ቢጠፋ፣ በባህላዊው መንገድ በሚደረገው የእርቅ ስርዓት ላይ ቂምና በቀልን ከውስጥ በማውጣት ከአንጀት የሆነ እርቅ መፈፀም መቻላቸው ነው፡፡ በሌላም በኩል በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቁን ባህላዊ አስተዳደራዊ ተቋም “አገቴ”  በማክበርና በባህላዊ ህጉም በመገዛት ተከባብሮና ተሳስቦ እንዲኖር አስችሎታል፡፡

## 6.2 የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ ጠንካራና ደካማ ገጽታዎች

### 6.2.1 ባህላዊው የግጭት አፈታት ያሉት ጠንካራ ጎኖች

1. በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን በማግኘት የፍርድ ስርዓቱን በቀናና በተስተካከለ መንገድ ማካሄዱ፣ እንዲሁም ፈጣሪን በመፍራትና ባህሉን በጠበቀ መልኩ ዕርቅን መፈፀሙ፤
2. ባህላዊው የግጭት መፍቻ ተቋም እዚያው ማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝና ከራሱ ከማህበረሰቡ የተዋቀረ እንዲሁም ቅርባቸው ስለሆነ አንድ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ወዲያው ወደ ግጭቱ መድረስ መቻሉ፣ ከዚህም ባለፈ ግጭቱ እንዲቀዘቅዝና ግጭቱ እንዲፈታ በባህሉ መሠረት ትክክለኛና ዘላቂ እርቅ መፈፀም መቻሉ፡፡
3. በአካባቢው የተፈጠሩት ግጭቶች ተካርረው ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዳይደርሱና የሰው ህይወት እንዳይጠፋ፤ አካል አንዳይጎድልና ንብረት እንዳይከስር ከጅምሩ ግጭቶቹን ማድረቅ መቻሉ፡፡
4. በመደበኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ሂደት ሊገለጹና ሊታወቁ ያልቻሉና የተሸፈኑ /የተደበቁ/ ነገሮች በአገቴው ስርዓት ላይ በሚፈጠረው ባህላዊና የእውነተኛነት ድባብ ግልጽ እንዲወጡና ተገቢው ብይን እንዲሰጥ ማድረጉ፤
5. በባህላዊው የፍትህ ስርዓት ላይ የሚፈፀመው የፍትህ ስርዓትና የእርቅ ሂደት እውነተኛ ከመሆኑም በላይ ወደፊትም ከሳሽና ተከሳሽ ባላቸው ህይወት ተባብረውና ተፋቅረው በአንድነት እንዲኖሩ የሚያስችል መልሶ ላለመጋጨት የሚያግባባ ቃለ መሃላና ምርቃት እንዲሁም ካሣ መካፈል ስለሚፈፀምበት ከቂምና በቀል የፀዳ በመሆኑ፤
6. በዓውዱ ላይ የሚደረገው /የሚከወነው/ የፍትህ ስርዓት ሰላም የሚፈጥርና ዘላቂ ሰላምን የሚያሰረግጥ በመሆኑ፤ በማህበረሰቡ ዘንድ የመጀመሪያ የፍትህ መስጫ ስርዓት ሆኖ መመረጡና በዓውዱም ላይ ያሉ ወጣት ወንዶችን ለወደፊቱ ባህሉን ተረካቢ ናቸው በሚል በማሳተፍ ባህሉ ተጠብቆ እንዲኖር መደረጉ የባህላዊው ፍትህ መገለጫ ስርዓት ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡

### 6.2.2. የባህላዊው የፍትህ ስርዓት ደካማ ጎኖች

1. በባህላዊው የፍትህ ስርዓት የተፈጠሩ ግጭቶችን የማፈታው በባህላዊ መንገድ ትውፊቱን ጠብቆ በዳይ እንዲቀጣና እንዲክስ፤ ተበዳይ ደግሞ እንዲካስ በማድረግ ነው፡፡ ይህን ሂደት ማህበረሰቡ ተቀብሎትና ቅጣት እንዳይደርስበት በመፍራት በቻ ሳይሆን ባህሉን በማክበር እንዲኖር አድርጎታል፡፡ ነገር ግን አንዳንዴ ከጎሣው አባላት ውስጥ ጉማ /ካሣ/ መክፈል የሚችሉ ሰዎች የበደላቸው ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱበትና ሊቀጡ የማችሉትን ቅጣት ስለሚያውቁ የበደላቸው ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በነፍስ ማጥፋት ጉዳይ ላይ ጉማውን የሚከፍሉት አራት መዓዘን ተብለው የሚታወቁት የቤተዘመድ ክፍሎች በመሆናቸው ለድርጊቱ መፈፀም ብርታት ይሆናቸዋል፡፡
2. የሀላባ ማህበረሰብ 99% የሚሆኑት የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ በመሆናቸው የአገቴው ስርዓት ለሴቶች ተሳትፎ ያለው አሳታፊነት ዝቅተኛ ነው፡፡ በሆኑም የባህላዊው እርቅ ስርዓት ድክመት ሆኖ ይስተዋላል፡፡
3. በተለያዩ የግጭት መፍቻ ቦታዎች በመሄድ ሽማግሌዎቹ የማህበረሰቡን ችግር ሲያስወግዱና እርቅ ሲያስፈጽሙ የራሳቸውን የስራ ሰዓት በመተው አምራችነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠር፡፡

## 6.3. ግጭት የፈጠሩት አካላት ባህላዊውን የፍትህ መፍቻ ስርዓት የሚመርጡበት ምክንያት -

ከፖሊስ ጋር በመተባበር በሀላባ ብሔረሰብ ግጭት ሲፈጠር ቶሎ በመድረሰና ግጭቱን በማብረድ ትልቁን ሚና የሚወስደው ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተፈጠረው ግጭት ያደረሰውን ጉዳትም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለምሳሌ ለግጭቱ መንስኤ የሆነው የቤት ቃጠሎ የሆነና በወቅቱም ይህ አደጋ ተከስቶ ከሆነ ቀድሞ ወደ ህይወት ማዳኑና ንብረት ማትረፉ ላይ ነው የሚያተኩረው፡፡ በወቅቱ የተፈጠረው እሳት ቤቱን አቃጥሎትና ንብረት አውድሞ ከሆነ የተቃጠለባቸውን ቤተሠቦች መጠለያ ሰርቶ ወደቀድሞ ህይወታቸው መመለስ ትልቁ ጉዳይ ነው(ገራድ ሙንዲኖ፣ ጥር 2006 ዓ.ም.፣ ስክርብ )፡፡ ከዚህ በመቀጠል ነው ምርመራውን

የሚጀምረው፡፡ በምርመራውም ወቅት እውነተኛና ፍትህን መሰረት በማድረግ ትክክለኛ ፍርድ ይበይናል፡፡ የበደለ ይቀጣል፡፡ ካሣም ይከፍላል፡፡ ተበዳይም ይካሣል፡፡ በዚህ ሳያበቃ የእርቅ ስነስርዓቱን በወጉና በባህሉ መሠረት ያከናውናል እውነተኛና ከቂም በቀል የፀዳ እርቅ ይፈጽማል፡፡ በዚህ ሥርዓት ላይ ውሸትም ሆነ ማጭበርበር ፈጽሞ የለም፡፡ በመሆኑም ዘላቂ እርቅ ይፈፀምበታል፡፡ በዚህም ምክንያት ባህላዊው የፍትህ ስርዓት በብሄረሰቡ ነዋሪዎች ዘንድ ተመራጭ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም እውነትን ፍለጋ ማህበረሰቡ ወደ ባህላዊው የፍትህ መስጫ ስርዓት መምጣት ይመርጣል፡፡

## 6.4. የባህላዊ የፍትህ ስርዓቱ የብሔረሰቡን ሰላም የማምጣትና የማስጠበቅ ሚና

ባህላዊ ስርዓቱ እንደስያሜው ሁሉ በተለያየ ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት ሰላም በመፍጠርና ህብረተሰቡ በሰላም እንዲኖር በማድረግ የሚሠራ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ የማፈጠረውን ጥቃት ደርሶበት ድብደባን በድብደባ ለመመለስስና አልበለጥም ወይም ከማን አንሼ በሚል ስሜት ተነሳስተው የሚጭሩትን የአፀፋ ምላሽ ጥቃቶች ማስወገዱና ማስቀረቱ ላይ እዚህ ጋ ቀረህ የሚባል ክፍተት የለውም፡፡ ምክንያቱም በሰው ልጆች የህይወት ኡደት ውስጥ ትልቁ የግጭት ውጤት የሚባለው “ሞት” ነው፡፡ በዚህ የግጭት ውጤት በሆነው የነፍሰ ግድያ ጉዳይ ከፍተኛ ግጭት ውስጥ የገቡት የብሔረሰቡ አካላት ለመበቃቀልና ለደረሰባቸው ጥቃት አፀፋ ምላሽ ሊሰጡ በሚዘጋጁበት ጊዜ ይህ ባህላዊ ተቋም በመግባት በስርዓቱ መሠረት በዳይን በማቅረብ የሚፈፀሙ ስርዓቶችን ከፈፀመ በኋላ በባህሉ መሠረት እንደ ጥፋቱ መጠን ማለትም አውቆ ጥፋት የሰራ ባህሉ የሚያዘውን ቅጣት እንዲቀጣ በማድረግ ሳያውቅና በስህተት  ጥፋቱን የፈጸመውን ደግሞ እንደሁኔታው በመቅጣት የህብረተሰቡን ሰላም በመጠበቅ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡

ተረክ 8. በአካባቢያችን  የጎረቤት ላም አንድ የአራት አመት ህፃን ልጅ ወጋች፡፡ ህጻኑ ለጊዜው ቢወድቅም  ግን አልተጎዳም ነበር፡፡ነገር ግን የህጻኑ አባት በድንጋጤና በንዴት እንጨት ይቆርጥበት  በነበረ ቆንጮራ ላሚቷን አባሮ እግሯን ይቆርጣል፡፡ ላሚቷም ደሟን እየፈሰሰች ሄደች፡፡ የላሚቷ ባለቤትም ተናዶ በመምጣት ከልጁ አባት ጋር ሊጣላ ሲል ሰዎች መሃል በመግባት ገላገሏቸው፡፡ ከዚያም የላሚቷ ባለቤት በቤተሰብ ጉባዔ ላይ የህጻኑን አባት ከሰሰው፡፡ የሽንጎውም መሪ ጉዳዩን ከሰማ በኋላ የህጻኑን

አባት ለምን እንደዚያ እንዳደረገ ጠየቀው፡፡ የህጻኑም አባት በወቅቱ በድንጋጤ ጥፋቱን እንደፈጸመ ተናገረ፡፡ የጎሳው ሽማግሌም ምንም እንኳን ልጅህ ቢወጋ የላሚቷን ባለቤት ልጅህን እንዲያሳክም ትጠይቀዋለህ እንጂ ምንም የማታውቅ እንስሳ በቆንጮራ መቁረጥ አልነበረብህም በማለት የገንዘብ ቅጣት በማስተላለፍ በሁለቱ ሰዎች መሃል እርቅ እንዲፈጸም አድርገዋል(አህመድ መሶሮ፡ መጋቢት 3፣ 2006 ዓ.ም. ስክርብ ፣ 25)፡፡

## ❖ የትዕምርቶች ትንተና

አንድ ማህበረሰብ በጋራ በሚኖርበት ወቅት በአኗኗሩ፣ በአመጋገቡ፣ በአለባበሱና በተለያዩ እሴቶቹ ተስማምቶና ተግባብቶ በጋራ የሚያስማማው ሕግና ደንብ አውጥቶ መኖሩ ለማንኛውም ሰው ግልጽ ነው፡፡ እነዚህንም ህጎችና ደንቦች ከግብ ለማድረስ የተስማማባቸውን ስርዓቶችና ትዕምርቶች ይጠቀማል፡፡ በሃላባ ብሄረሰብም ግጭቶችን ለመፍታት የተለያዩ ስርዓቶችና ድርጊቶች ይከወናሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ጥቁር ማረድ ፣ የሟች ቤተሰብ ከገዳይና ገዳይ ከሟች ቤተሰብ እጅ መጉረስ(መብላት)፣ ወተትና ማር ከአግር ስር መድፋት፣ አንጀት መግመድና ጎትቶ መበጠስና የመሳሰሉት በሃላባ ብሄረሰብ ውስጥ ግጭት ሲፈጠር ለመፍታት የሚከወኑ ድርጊቶችና የሚፈጸሙ ስርዓቶች ናቸው፡፡

**ጥቁር ማረድ** በብሄረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ የግድያ ወንጀሎችን ለመፍታት ከሚከወኑ ስርዓቶች አንዱ ጥቁር ማረድ ነው፡፡ ይህም ተምሳሌትነቱ በሟች ቤተሰብና በገዳይ መካከል የተፈጠረው ግጭት ሁለቱ ወገኖች መካከል ጥሩ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖርና በነፍስ እንዲፈላለጉ ያደረገ ስለሆነ ጨለማ ነው ፣ ሰላም አያመጣም ተጨማሪ ደም ሊያፋስስ ይችላልና ይህ ጥል(ግጭት ) ሲፈታ ጥቁር መታረድ አለበት ተብሎ በብሄረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡ ጥቁር መታረዱም በሁለቱ ቤተሰብ መሃል ተፈጥሮ የነበረው እንደጨለማ የተደፈነ ጥል ይፈታል ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ጥቁሩ እንስሳ ሲታረድ ጥቁሩ ጨለማ ከመሃላችን ተነስቷል(ተገፏል)ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

ከጥቁር እንስሳ ማረዱ ጋር ተያይዞ ከታረደው እንስሳ ስጋ ወይም ሌላ የተዘጋጀ ባህላዊ ምግብ የሟችና የገዳይ ቤተሰቦች አብረው እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ የአበላል ስርዓታቸውም ገዳይ ከሟች አባት ወይም ወንድም እጅ እንዲሁም፤ የሟች አባት ደግሞ ከገዳይ እጅ

እንዲበሉ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚደረገው ከእርቅ በኋላ የሟች ቤተሰብ ሌላ የበቀል ስሜት እንዳይፈጠርበትና ከልብ የሆነ ሰላም እንዲፈጠር ለማደረግ ነው፡፡ ይህም ሲባል በብሄረሰቡ ከአንድ እጅ አንድ ላይ መብላት ታላቅ ወዳጅነት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለሆነም ከአንድ እጅ በልተናልና መሃላችን ምንም ነገር ላይፈጠር ተዋደናል ፣ እንደ አንድ ቤተሰብም ሆነናል ብለው ስለሚቀበሉት ነው፡፡

በተጨማሪም የእንስሳውን አንጀት በማውጣት እንደሰንሰለት በማጠላለፍ ይገምዱትና ከዳርና ዳር በመጎተት ይበጥሱታል፡፡  አንጀቱ የተመረጠበት ምክንያት እንደባህሉ አንጀት የመቀራረብና ከልብ የሆነ መዋደድ ምልክት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን አንጀት አውጥተው በሚበጥሱት ጊዜ በውሰጣቸው ያለው ጥላቻ ተቀርፎ  ውስጣዊ መዋደድ ይተካል  ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

**ማርና ኮሶ መርጨት**፡- ስርዓቱ የሚካሄደው የሟችና  የገዳይ ቤተሰቦች በእርቁ ቀጠሮ ቀን ወደ ቤት ሲገቡ  የሟች እህት ወይም አክስት የተበጠበጠ ኮሶ ታዘጋጅና በመግቢያው አንድ ዳር ትቆማለች፤ እንዲሁም የገዳይ አክስት ወይም እህት የተበጠበጠ ማር  ትይዝና በሌላኛው የበሩ ዳር ትቆማለች፡፡ ሰዎቹ ሲገቡ የሟች እህት ኮሶውን ከሰዎቹ እግር ስር ትደፋዋለች፡፡ ይህም ተምሳሌትነቱ በልጃችን ሞት ምክንያት ሰላማችን ተበጥብጧል ፣መራራም  ሆኖብናል ሃዘኑም ጎድቶናል የሚል አንድምታ ይሰጠናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የገዳይ እህት ወይም አክስት በጠብጣ  ያዘጋጀችውን ማር በብሳና ቅጠል ሰዎቹ እግር ስር ትረጨዋለች፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥ መራራ ነገር ቢፈጠርም ዛሬ በተፈጠረው እርቅ ምክንያት ሃዘኑም፣ምሬቱም መራራቁም  ወደ ሰላም ተቀይሯል በሚል እሳቤ ድርጊቱን ትፈጽመዋለች፡፡

በአጠቃላይ በብሄረሰቡ ውስጥ  ባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት  ያለው ሃይማኖታዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረ ባህላዊ  ጠቀሜታ ምን ያህል እንደሆነ ፤ እንዲሁም  ካለው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት አንጻር በማህበረሰቡ ዘንድ ዋናና ተመራጭ ሆኖ እንዲዘልቅ በማድረግና የህዝቡን ሰላም ከማስጠበቅም አኳያ፣ ትልቅ ሚና እንዳለው ማየት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በብሄረሰቡ ውስጥ ሰላምን ለመፍጠርና ግጭትን ለማስወገድ የሚከወኑት ስርዓቶችና ደንቦች ማህበረሰቡን በማስተሳሰርና ባህሉንም  እንደ ትልቅ እሴት በመቁጠር እንዲያከብሩትና እንዲተገብሩት ብሎም  በመስማማት እንዲኖሩ በማድረጉ በኩል ከፍተኛ  ሚና እንደሚጫወትም ታይቶበታል፡፡

## 6.5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት በሃላባ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ የሃላባ ብሄረሰብ በተለያዩ ምክንያቶች በህዝቡ ውስጥ ግጭቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ የተፈጠሩትን ግጭቶች ለማስወገድ የሚጠቀመውን ባህላዊ የፍትህ መስጫ ተቋም (ኦገቴ) ምንነት ፣ስርዓት ፣መዋቅርና የስርኣት አከዋወን እንዲያሳይ ተደርጎ የቀረበ ነው፡፡

ጥናቱ ሲጀምር ዓላማው ያደረገው በሃላባ ብሄረሰብ የውስጥም ሆነ የውጭ ግጭቶች ሲፈጠሩ የተፈጠረውን ግጭት ለማስወገድና ሰላም ለመፍጠር የሚካሄደውን የሰርኣት ሂደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ በመተንተን ለማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም በሃላባ ብሄረሰብ አንድ ግጭት ቢፈጠር ቀድሞ የት እንደሚኬድ ፣ ተኪዶ ምን እንደሚደረግ ፣የእርቁን ስርዓት ለማስፈጸም ምንምን እንደሚመቻች ፣ስርዓተ ዕርቁ እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈጸም በጥናቱ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

በተጨማሪም የብሄረሰቡ ባህላዊ የፍትህ ተቋም በደረጃ ማለትም ሚኒ ኦገቴ፣ ቦኪ ኦገቴ፣ ደቦ ኦገቴ ና ሃላቢ ኦገቴ በመዋቀር ከመደበኛው ፍርድ ቤት ጋር በመተባበር በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩትን ግጭቶች እየፈታና ሰላም እየፈጠረ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡ ከዚህም ባለፈ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ አቅመ ደካማዎችን ፣ የተለያየ ችግር ያጋጠማቸውን ሰዎችና ሌሎችንም በገንዘብና በጉልበት እንዲታገዙ እንደሚያደርግም ጥናቱ አሳይቷል፡፧

ባህላዊ የፍትህ ተቋሙ ተበድለው በደላቸውን ለመግለጽ የሚመጡ ሰዎችን ለማስተናገድ በብሄረሰቡ ውስጥ በንግግርና ባህል አዋቂነታቸው የተመሰከረላቸውን 'ቆርቶ' ተብለው የሚታወቁትን ሰዎች መጠቀሙና ክርክሩንም ሆነ ፍትሁን በግልጽ ማካሄዱ ከሌሎች በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከተሰሩት ጥናቶች እንደሚለየውና የሚወሰነው ውሳኔም ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረጉ በግልጽ ታይቶበታል፡፡

በብሄረሰቡ በተደጋጋሚ የሚነሱትን ግጭቶች እንደየደረጃቸው የሚፈቱበትን ሂደትም አሳይቷል፡፡ በኣካባቢው በብዛት የሚከሰቱት ግጭቶችንም የቤተሰብ አለመግባባቶች ፣ የጎሳዎች የእርስ በርስ ግጭት፣ ከአጎራባች ህዝቦች ጋር የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ፣

በንብረት ስርቆት ምክንያት የሚፈጠር ጠብና የመሳሰሉት መሆናቸውን አሳይቶ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት እንደየጥፋቶቹ ታይተው አጥፊዎች ተቀጥተው ተበዳዮች ደግሞ ተክሰው ወደ ሰላማዊ ህይወት እንደሚመለሱበት ተመልክቷል፡፡

ባህላዊ የግጭት ተቋሙ በማህበረሰቡ ዘንድ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይልቅ ተመራጭ እንደሆነ ፤ይህም የሆነው በባህላዊው የፍትህ አውድ የሚከወነው የፍርድ ሂደት ቀናና ባህሉንና ሃይማኖታዊ የአኗኗር ገጽታውን የሚያንጸባርቅና፣ እውነተኛ ብይን የሚሰጥበትና የሚታመን በመሆኑ ነው፡፡በተቃራኒው ግን በመደበኛው የፍትህ አውድ የሃሰት ምስክር የነገሰበት ፤በዘር በሃብትና በመሳሰሉት አድልዎ የተንሰራፋበት ነው በማለት ወደ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት እውነተኛ ፍርድን ፍለጋ እንደሚመጡ በጥናቱ ተዘርዝሯል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ሁለቱም የፍትህ ተቋማት በአካባቢው በመተባበር በጥምረት እንደሚሰሩ ተዳሶበታል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ በዓላማው ላይ የተነሱትን ሃሳቦች በመደገፍ ባህላዊ የፍትህ ተቋሙ ባህሉ በሚፈቅደውና በብሄረሰቡ በተለመደው የእርቅ ስርዓት ፤ የእርቅ ሂደትና አከዋወን ስርዓት ውስጥ በመግባት ዓይነተኛ ስራ እንደሚሰራም ያሳየ ነው፡፡

## 6.6. ይሁንታ

የሃላባ ብሄረሰብ አባላት በዘውትራዊ ህይወታቸው ላይ የሚያጋጥሟቸውን ግጭቶችና አለመግባባቶች ለመፍታትና ሰላማዊ ህይወታቸውን በተረጋጋ ሁኔታ እንዲገፉ ከሚያደርጓቸው ባህላዊ ተቋማት አንዱ የሀላባ ኦገቴ (ሃላቢ ኦገቴ/ጎጎታ) እንደሆነ ጥናቱ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም ይህ ባህላዊ ተቋም አዎንታዊነቱ ጎልቶና ለበሄረሰቡ የሚኖረው ጠቀሜታ ከኢኮኖሚያዊ እሴትነቱ፣ ከማህበራዊ ፋይዳው ፤ከስነ ልቡናዊና አስተዳደራዊ አጋዥነቱ አንጻር እንዲጎለብት፤ ቢሻሻልና ቢጠናከር መልካም ውጤት ሊያመጣና ተቀባይነቱና ዘላቂነቱ ይበልጥ ይሆናል ብዬ የማስባቸውን የይሁንታ ሀሳቦች እንደሚከተለው አቀርባለው፡፡

- ባህላዊው ተቋም በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነቱን እንደያዘ እንዲቀጥል መንግስት ባህሉን በጠበቀ መልኩ በህግ ማዕቀፍ ቢያደራጃቸውና ማህበረሰቡም

የብሄረሰቡ መገለጫ አሴት እንደመሆናቸው መጠን እንደግል ሃብታቸው ቢንከባከቡት የላቀ ስራ ይሰራል፡፡

- የባህላዊ ተቋሙን ሽማግሌዎች (እርቅ አስተባባሪዎች) ባህላዊ ትውፊቱን በጠበቀና ከነበረው ደረጃ በተሻለ እንዲሰሩ የሞራልና የሙያ ድጋፍ ቢሰጣቸው ፣ እንዲሁም በስልጠና ቢታገዙ ይበልጥ ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡
- መንግስት ህግ ሲያወጣና ፖሊሲ ሲቀርጽ ባህላዊውን የፍትህ መስጫና ሌሎች አዎንታዊ ገጽታ ያላቸውን ባህሎች ቢያካትታቸው ፤ በተጨማሪም በትምህርት ፖሊሲም ላይ በተወሰነ መልኩ ቢጨመር ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ባህላቸውን ወደ ውስጣቸው እንዲያሰርጹት ይረዳቸዋል፡፡
- ባህላዊው የፍትህ ስርዓት የሚከወነው ጥላ ስር እንደመሆኑ መጠን ክረምት ሲሆን በዝናብ ፣ በጋ ሲሆን ደግሞ በአቧራው ምክንያት በወጥነት ለክዋኔው በተመቻቸ ሁኔታ አገልግሎት ሊሰጥ ስለማይችል ፣ ቢቻል የመሰብሰቢያ ቦታቸው ላይ በቋሚነት መቀመጫ ቢሰራላቸው ስራቸው እንዳይስተጓጎል ይረዳቸዋል፡፡
- በብሄረሰቡ አንድ ጥፋት የሰራ ግለሰብ በመደበኛው ፍርድ ቤት ቅጣት ተጥሎበት እስሩን ጨርሶ ሲወጣ “ሄደህ ጉዳይህን በባህል ጨርሰህ ወደ ማህበረሰቡ ግባ“ ተብሎ ብቻ ከመደበኛው ፍርድ ቤት ከሚነገረው ይልቅ መደበኛ ተቋሙ ከባህላዊው የዳኝነት ሽማግሌዎች ጋር ቅድመ ሁኔታዎችን በማዘጋጀት ሰላም እንዲፈጠር ቢያደርግ የተሸለ ይሆናል፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች

ብርሃኑ ቦጋለ፣ *"መሳል ባላዊ የግጭት እታት ስርዓት በአንጾኪያ ገምዛ ወረዳ"፤* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ፡፡ 1998 ዓ.ም.

ተመስገን ምንዋጋው፣ *"ሀገረሰባዊ የግጭትአፈታት ስርዓት በዶኮ ጋሞ፤"* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ፡፡ 1998 ዓ.ም.

አብርሃም ታደሰ፣ *"ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በሲዳማ ብሄረሰብ"* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ፡፡1999 ዓ.ም፡፡.

አምሩላህ ጠለሃ *የሃላባ ህዝብ ታሪክ* አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤አዲስ አበባ 2003፡፡

አንዱአለም አባተ፣ *"ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በመኤኒት ብሄረሰብ"* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ 2004 ዓ.ም.

የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ፣ *"የሃላባ ብሄረሰብ ባህልና ታሪክ"* 1998 ዓ.ም. ያልታተመ፡፡

የወንድወሰን አውላቸው *"የሰባት ቤት ጉራጌ ባህላዊ አስተዳደርና የግጭት አፈታት ስርዓት"* በኢትዮጵ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ 1998 ዓ.ም.

የደቡብ ብ/ብ/ህ/ *ፕሮፋይል*፤ 2004 ዓ.ም.

ይልማ ተፈሪ፣ *“የሽምግልናና ዕርቅ ስርዓት በወላይታ”* በኢትዮጵ ቋዋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ 1998 ዓ.ም.

ፈቃደ አዘዘ *የስነ ቃል መምሪያ* አዲስ አበባ ፤ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረጃ ተቋዋም፤1991

---------------- ቴምፕሌት በአማርኛ፣ የካቲት ፤2003 ።

ፍሬህይወት አድነው ” ከምባቶመት“ በኢትዮጵ ቋዋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሙዋያነት የቀረበ 1997 ዓ.ም.

Anstey, M. *Negotiating conflicts insight and skill for negotiators and peacemakers*; Cape town, juta and co.1991.

Assefa Abebe “conflict in pastoralist community pastoralists in south omo.” prteceding of the workshop held in jinka (south omo) Epa RDA 2001 pp31_41

Boulding . K. G. *conflict and defense* ; A general theory, New York, harper raw publishers. 1962.

Coser Lewis A *The function of social conflict* ; the free press; New York,1970.

Fisher, Stanley Z. «Traditional criminal procedure in Ethiopia»; the American journal of competitive law. New York; Andronicus publishing company publishers,1976.

Kriedier, W. *Creative conflict resolution*; more 200 activities forekeeping in the  lassroom, Glenview.IL‘s scot, forces man and company, 1984.

Rugugnamu, severioner M. “Conflict management in Africa diagnosis of current practice and prospects” .(paper presented at the DPMF/OSSREA conference on African conflict reconstruction). Addis Ababa , Ethiopia. Dec 13–14 2000.

Siyoum Mengistu “natural resources competition and inter ethnic relation a case study of Arsi oromo and Alaba ethnic group in Alage” south central Ethiopia. MA thesis , Addis Ababa university, 2001›

Tesfaye Habisso “*Some Historical records of kembata” (part two),* Hambaricho, the mountain and the people. Web, July 14 2012

World Bank *Global economic prospect and the developing Countries;* making trade workfor the World poor, Washington DC. World bank. 2002

Yohannes G.Michael, Kassaye Hadgu and Zerihun Ambaye; *Addressing Pastoralists conlict in Ethiopia* ፡ the case of kuraz and Hamer sub districts of south omo zone.

Zertman, wiliam and Francis M. Deng (ed.) *Conflict resolution in Africa;* Washington DC, the brooking institution፤ 1991

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ ፡ የመረጃ ሰጪዎች ፎቶ

### የመረጃ ሰጪዎች ፎቶ በከፊል



ገራድ ሙንዲኖ ሁሴን የሴራ ሽማግሌ



እማም መሃመድ አብደላ የሴራ ሽማግሌ



እማም ሂርጶ ዎጩሶ የሴራ ሽማግሌ



ሼህ ክድር ኢብራሂም  የሴራ ሽማግሌ





ሻህ ሻፊ ሎኬ የሴራ ሽማግሌ

እማም ሁልጫፎ አብዶ የሴራ ሽማግሌ



በሀላባ ኦገቴ ባህል ለጉዳ እርቅ ስርዓት የተዘጋጁ የታራቂዎቹ አካላት



በእርቁ ስርዓት ላይ የሚች አባት ከገዳይ እጅ ሲበሉ



በእርቁ ስርዓት ላይ የገዳይ አባት ከሚች አባት እጅ ሲበሉ

## አባሪ ሁለት፡ የመረጃ ሰጪዎች ስምና ፕሮፋይል

## 1.የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

### *1.1. ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ዕድሜ ስራ*

| | | |
|---|---|---|
| 1. አቶ አክሊሉ ወንድሙ | 31 | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያ |
| 2. አቶ እንዳለ በቀለ | 52 | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያ |
| 3. ገራድ ሙንዲኖ ሁሴን | 55 | የሴራ ሽማግሌ |

**1. አቶ አክሊሉ ወንድሙ**

አቶ ክሊሉ ከሃዋሳ ዩኒቨርስቲ በ'general anthropology' በ2003 ዓ.ም. የተመረቀ ሲሆን በዚያው ዓመት መጨረሻ በሃላባ ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት በባህል ዘርፍ ተቀጥሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመስሪያ ቤቱም ለሶስት ተከታታይ ዓመታት አገልግሏል፡፡ በዚህ የአገልግሎት ዘመኑ በሃላባ ውስጥ ባህላዊ ትውፊቶችን በማስጠበቅ፣ የእደ ጥበባት ስራዎችን በማስፋፋትና ማህበረሰቡ በራሱ ምርት እንዲጠቀም በማበረታታት፣ የሃላባ ሴራ አዘጋጅ ኮሚቴ ውስጥ በመካተት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ስለ ሃላባ ባህልና ቋንቋ ሊያጠኑ የሚመጡ አጥኚዎችን በመቀበል መረጃ በመስጠትና መረጃ አቀባዮችን በማዘጋጀት እያገለገለ ነው፡፡ የሃላባ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት (ኦገቴ) ከበደበኛው ፍርድ ቤት ጋር እነዲሰሩ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ እበረከተ ይገኛል፡፡

**2. አቶ እንዳለ በቀለ**

አቶ እንዳለ በቀለ ነዋሪነታቸው በሃላባ ከተማ ሲሆን በልዩ ወረዳው ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ውስጥ በመረጃ ዴስክ ዘርፍ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ሙያዊ ስራቸው በተጨማሪ በባህላዊ የፍትህ መስጫ ስርዓቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና በመውሰድ ስላም በመፍጠሩ ረገድ ላቅ ያለ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም ኦገቴው ላይ የአስተርጓሚነት ስራ ይሰራሉ፡፡ እንደአጋጣሚ የመኪና አደጋ ተፈጥሮ ሰው ቢሞት ብዙውን ጊዜ ጉዳዩን ቀድመው የሚሰሙት አቶ እንዳለ ናቸው፡፡ የሰሙትንም ጉዳይ ክሽማግሌዎች ጋር በመሆን እስከፍጻሜው ድረስ ይከታተሉታል፡፡ ሌላው በተለያዩ የኦገቴ አውዶች ላይ በመገኘት ብዙ አጋጣሚዎችን

ስለተመለከቱ ልምድ ስላዳበሩ ለአጥኚዎች በአባዛኛው ቁልፍ አቀባይ ሆነው መረጃ በመስጠት ይረዷቸዋል፡፡

3.ገራድ ሙንዲኖ ሁሴን

የሃንሾ ቀበሌ ነዋሪና የጦሮንቦራ ጎሳ አባልና የጎሳው መሪ ናቸው፡፡ ገራድ ሙንዲኖ በሃላባ ብሄረሰብ ባህላዊ ክዋኔዎች ላይ ትልቅ ሚና ካላቸው ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡ በተለይም የሃላባ ሴራ ክብረ በዓል ላይ በመመረቅና ንግግር በማድረግ ፣ በባህላዊው የግጭት መፍቻ ስርዓት ላይ ድገሞ ጎሳቸውን በመምራት ወደ ሰላም በመመለስ ትልቅ ልምድ አላቸው፡፡ በተለይም በሃላቢ ኦገቴ(የሃላባ ሸንጎ) ላይ በመገኘት ትክክለኛ ፍትህ እንዲካሄድ ማለትም በደል የፈጸመው እንዲቀጣ ፣ ተበዳይ ደግሞ እንዲካስ በመዳኘት ይታወቃሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የእርቅ ስርዓቶች በሚፈጸሙበት ወቅት በዋና ሽምጋይነት በመሰየም ባህሉ ተጠብቆ እርቁ እንዲካሄድ በመምራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድም ተቀባይነትን አግኝተዋል፡፡ እንዲሁም በሃላባና በአጎራባች ብሄረሰቦች መካከል በሚከሰቱ ግጭቶች መሃል ሰላም ለመፍጠር በሚዋቀሩ ሽማግሌዎች ውስጥ በመካተት በተለያዩ ጊዜያት አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡


## 1.2 ንኡሳን መረጃ ሰጪዎች

| ስም | ዕድሜ | ስራ |
|---|---|---|
| 1. እማም ዝዋር ሄራሞ | 80 | የሴራ ሽማግሌ |
| 2. እማም መሀመድ አብደላ | 75 | የሴራ ሽማግሌ |
| 3. እማም ህርጶ ወጬሶ | 62 | የሴራ ሽማግሌ |
| 4. እማም ሁልጫፎ አብዶ | 65 | የሴራ ሽማግሌ |
| 5. ሼህ ከድር ኢብራሂም | 58 | የሴራ ሽማግሌ |
| 6. ሼህ ሻፊ ሎኬ | 52 | የሴራ ሽማግሌ |
| 7. አቶ አህመድ መሶሮ | 35 | የባህላዊ ኪነት አቀንቃኝ |
| 8. አቶ አህመድ ናስር | 45 | የህግ ባለሙያ |
| 9. አቶ አምባዬ ምንዳ | 45 | መምህር |
| 10. አቶ ሃቢብ ሽኩራህ | 40 | የ2ኛ በደኔ ቀበሌሊቀመንበር |

| ተ.ቁ | የመረጃ ሰጪው ስም | ዕድሜ | አድራሻ | ጥያቄው ያተኮረበት ነጥብ | ሀላፊነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አክሊሉ ወንድሙ | 31 | ሃላባ ከተማ | ስለ ግጭት፣ የግጭት መንስዔና ስለ አጠቃላይ ሚናዎች | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያ |
| 2 | እንዳለ በቀለ | 55 | ሃላባ ከተማ | ስለ ግጭት፣የእርቅ አፈጻጸም፣ አጋጣሚዎች | የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያ |
| 3 | ገራድ ሙንዲኖ ሁሴን | 55 | ሃንሾ ቀበሌ | ስለ ኦገቴው ዳኞችና መዋቅር | የሴራ ሽማግሌ |
| 4 | እማም ዝዋር ሄራሞ | 80 | ጮሮቆ ቀበሌ | ስለኦገቴ ሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመንና ሌሎች ባህሎች | የሴራ ሽማግሌ |
| 5 | እማም መሀመድ አብደላ | 75 | አንሾቀበሌ | የኦገቴውን መዋቅርና የእርቁን ባህላዊ ስርዓቶች በተመለከተ | የሴራ ሽማግሌ |
| 6 | እማም ሀርጾ ወጩሶ | 62 | ዋንጃ ቀበሌ | የእርቅ አፈጻጸም ስርዓትን በተመለከተ | የሴራ ሽማግሌ |
| 7 | እማም ሁልጫፎ አብዶ | 65 | መቃላ ቀበሌ | የግጭት አፈታት ሂደትን በተመለከተ | የሴራ ሽማግሌ |
| 8 | ሼህ ከድር ኢብራሂም | 53 | ሽቃቂ ገበሌ | የኦገቴውን አካሄድ፣ ስለ ቆርቶዎችና የመደበኛውንና ባህላዊውን የፍትህ ብሮነት በተመለከተ | የሴራ ሽማግሌ |
| 9 | ሼህ ሻፊ ሎኬ | 52 | ቁራንሶ | ከኦገቴው ውጪ ስላሉት ባህሎች | የሴራ ሽማግሌ |
| 10 | አቶ አህመድ መሶሮ | 35 | ሃላባ ከተማ | ስለ ግጭት ምንነትና ስለ ኦገቴው ሚና | |
| 11 | አቶ አህመድ ናስር | 29 | ሃላባ ከተማ | ባህላዊውና የመደበኛው ስርዓት በህዘቡ ዓይን ምን እንደሚመስል | |
| 12 | አቶ አምባዬ ምንዳ | 45 | ሃላባ ከተማ | ስለ ግጭት፣ ስለ ኦገቴ አመራርና ኦገቴው በማህበረሰቡ ቀጣይ ሰላም ላይ ስላለው ሚና | |
| 13 | አቶ ሃቢብ ሽኩራህ | 40 | 2ኛበደኔቀበሌ | ስለኦገቴአመራርና የስብሰባው የጊዜ ገደብ | |

## አባሪ ሶስት፡

## *ጥናቱ የተሰራበት የአማርኛ ቴምፕሌት*



ቴምፕሌት በአማርኛ

1. መግቢያ

ይህ ክፍል ስለምታጠኑት ብሔረሰብ መሰረታዊ መረጃዎችን የምታቀርቡበት ነው።

1.1 የሕዝቡና የአካባቢው ማስተዋወቂያ

1.1.1 አካባቢው የት ነው? ክልሉ፣ ዞኑ፣ ወረዳው፣

1.1.2 ጂኦግራፊው (ተራራ፣ ወንዝ፣ ሜዳ ወዘተ.) i.e. the physical environment

1.1.3 የብሔረሰቡ ታሪክ (አፈታሪክ እና ጡፍታሪክ)፣ ከጎረቤት ብሔረሰብ /ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት (የመተሳሰብ፣ የመተባበር፣ ያለመግባባት፣ የመጋጨት ወዘተ.)

1.1.4 የህዝቡ አይነትና ብዛት፣ የሚነገረው/የሚነገሩት ቋንቋ/ቋንቋዎች እና የቋንቋው/የየቋንቋዎቹ ቤተሰብ/ቤተሰቦች (language family/families)

1.1.5 መተዳደሪያው (economy)

1.1.6 ማህበራዊ አደረጃጀቱ (social organization)

1.1.7 ሃይማኖት እና ሌሎች እነዚህን የመሰሉ አስፈላጊ ጉዳዮች ባጭሩ ይቀርባሉ

1.2. የጥናቱ ምንነት

1.2.1 አጥኚው በቱለየ በዚህ ርእስ ለማስራት ለምን ተነሳ?

1.2.2 ዓላማው ምንድነው?

1.2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ምንድነው?

1.2.4 መረጃውን ከማን ነው የሚሰበስበው?


1.2.5 የሰበሰበውን መረጃ የሚያቀርብበት መንገድ ምንድነው?

1.2.6 የሰበሰበውን መረጃ የሚተነትንበት መንገድ ምንድነው?

1.2.7 ከእርሱ ጥናት ጋር **በቀጥታ የሚገናኙ** ቀደምት ጥናቶች አሉ? ካሉ እነርሱ የሰሩትን ከገለጸና ከገመገመ በኋላ የርሱ ስራ በዚያ ላይ የሚያክለውን ወይም ደግሞ በተሰሩት ስራዎች ውስጥ የተፈጸመ ስህተት ካለ ያንን በማስረጃ እየደገፈ ይገልጻል።

2. የሚጠናው ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታበት/የሚፈታባቸው ሥርዓት/ሥርዓቶች ምንነት እና መዋቅር/መዋቅሮች (structures)

|||የሚጠናው ብሔረሰብ ግጭት የሚፈታበት/የሚፈታባቸው ሥርዓት/ሥርዓቶች ምን ይባላል/ይባላሉ? ስያሜው በአካባቢው ቋንቋ ይሰጥና አስፈላጊው ማብራሪያም አብሮ ይቅረብ። ለተለያዩ የግጭት ዓይነቶች የተለያዩ ሥርዓቶችና ስያሜዎች ካሉ እነዚህንም ማስተዋወቅና በኋላ በተገቢ ስፍራቸው ማብራራት ያስፈልጋል። ከዚህ በኋላ ወደ መዋቅሩ ይገባል። (የኩተት 28 የታከለ ማብራሪያ-በፈቃደ አዘዘ) |||



በመዋቅር (ያካባሁት ቀልም በዚሁ አለት ታድጊል።) ስር የሚከተቱት ዓበይት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው። በእያንዳንዳቸው ስር ግን ልዩ ልዩ ንዑስ ርእሶች እንደየሁኔታው ሊኖሩ ይችላሉ።

2.1 አንድ ጠብ (ግጭት) ሲፈጠር የት ይሔዳል? ቀጥሎስ? እንዲህ እያለ ከመነሻ ጀምሮ ብያኔ እስኪያገኝ ድረስ የሚያልፍባቸውን ልዩ ልዩ ደረጃዎች፣ ቅደም-ተከተሉን አስተካክሉ መግለጽ ነው መዋቅሩን ማቅረብ ማለት። መዋቅሩ ከዘመን ዘመን በተለያዩ ምክንያቶች ተለዋውጦ ከሆነ ያንንም ከነምክንያቱ መግለጽ ያስፈልጋል። መረጃ ከተገኘም ዘመኑን መግለጽና እቅጩ ዘመን ማግኘት ካልተቻለም በአካባቢው የዘመን አጠቃቀስ ይትባሃል የሚነገረውን ማስፈር አስፈላጊ ነው። በገለጻው መጨረሻ ላይ ግን በልዩ ትኩረት የሚጻፈው ምርምሩ በተካያሄደበት ወቅት በተግባር ላይ ያለው መዋቅር ነው።

2.2 በሽምግልናው ስርዓት ውስጥ ነገር ለማየት የሚቀመጡት እነማን እነማን ናቸው? በምን መንገድና መስፈርት ነው የሚመረጡት? በዚህ አገልግሎት ላይ የሚቆዩበት ዘመን ገደብ አለው? በተለያዩ ምክንያቶች ለዳኝነት አይበቁም ተብለው የማይመረጡ የአካባቢው ማኅበረሰብ ክፍሎች አሉ? እነማን ናቸው? ለምንድነው ማእቀብ የሚደረግባቸው?

2.3 መዋቅሩ ባሁኑ ሰዓት በተግባር ላይ ነው? ምን ያህል? የሚያሻሙ፣ የሚያሰጋ፣ ተስፋ የሚሰጥ ወዘተ. ነገር አለ? ባጭሩ፣ ይህ ክፍል፣ ስለመዋቅሩ የሚሰጠው አጠቃላይ መግለጫ ከማብቃቱ በፊት መነገር አለባቸው፣ እንባብያንና ተመራማሪዎች ሊያውቋቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ ተብሎ ከታሰበ እነርሱ ተብራርተው የሚገለጹበት ክፍል ነው።

ከ2.1 እስከ 2.3 የሚጻፈው በሙሉ ከእውራ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡ መረጃዎች ጭምቅ ነው። በመሰረቱ፣ አቀራረቡም ገላጭ ነው። ተመራማሪው፣ ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች የሰበሰበውን፣ መልክ ሰጥቶና አደራጅቶ፣ የግል አስተያየቱን ሳይጨምር፣ ለአንባብያንና በእውቀቱ ለሚገለገሉ ክፍሎች ቁልጭ ባለ እና የአካዳሚያዊ ምርምርን ኢቲክስ በጠበቀ መንገድ የሚያቀርበው ነው።

3. የሚጠናው ብሔረሰብ ግጭት ሲፈታ የሚከተላቸው ሂደቶች (procedures)

‹ሂደት› ማለት አንድ ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ፍጻሜ እስኪያገኝ ድረስ በየእርከኑ / በየደረጃው የሚከናወኑ ተግባራት ማለት ነው። በዚህ ርእስ ስር የሚካተቱት ዓበይት ነጥቦች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። በእያንዳንዳቸው ስር ግን ልዩ ልዩ ንዑስ ርእሶች እንደየሁኔታው ሊኖሩ መቻላቸውን ከወዲሁ መገንዘብ ያስፈልጋል።

3.1 አንድ ግጭት ተከሰተ / ደረሰ እንበል። መጀመሪያ ለማን ነው የሚነገረው? ነጋሪው ማነው? እንዴት ነው የሚናገረው? ከዚያ በኋላ ማን ምን ያደርጋል?

3.2 ግጭቱን መመርመር የት፣ እንዴት ይጀመራል? በማን? ሽማግሌዎቹ ወይም ዳኞቹ በጉዳዩ ሳይቀርብ በፊት የሚከናወን ተግባር አለ? እነርሱ በጉዳዩ ከተረቡ በኋላስ ምን ይሆናል? ምስክሮች ጠርተው ቃላቸውን ይቀበላሉ? ሽማግሌዎች በምስክሮች ቃል ላይ ብቻ ተመርኩዘው ነው ብያኔ የሚሰጡት ወይስ በሌላ መንገድ ተጨማሪ መረጃ ይሰበስባሉ? የሚሰበስቡ ከሆነ ምን ዓይነት መረጃ ነው የሚሰበስቡት? ከማን? እንዴት? ከበደኞቹ አንዱ ጥፋቱን ገና ከመነሻው ከተቀበለ ምን ይሆናል?

3.3 እሳይ በተጠቀሱት ልዩ ልዩ መንገዶች መረጃ ከሰበሰቡ በኋላ ሽማግሌዎቹ ወደ ውሳኔ የሚያመሩበት መንገድ ምንድነው? ለምሳሌ፣ ሽማግሌዎቹ እርስ በርሳቸው ከተወያዩ በኋላ በስምምነት አንድ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ ወይስ ድምጽ በመስጠት የብላጫውን ድምጽ በውሳኔ መልክ ያጸድቃሉ? ወይስ ከሽማግሌዎቹ መሀከል ውሳኔውን የማስተላለፍ ስልጣን ያለው ሽማግሌ አለ?

3.4 ሽማግሌዎች ውሳኔያቸውን ለባለጉዳዮቹ የሚያሰሙት እንዴት ነው? የእርቁ ውሳኔ የሚነገርበት ሥርዓት አለ? ይህ ሥርዓት የሚካሄድበት የተለየ ስፍራ አለ? በሥርዓቱ ላይ ማን ማን ይገኛል? ማን ማን አይገኝም? ለምን? በሥርዓቱ ላይ እርድ ይካሄዳል? ጸሎት፣ ምርቃት፣ እርግማን ወዘተ. ይካሄዳል? ዘፈንና ጭፈራ አለ? እነዚህ በሙሉ ወይም በከፊል ካሉ የሚካሄዱበት ምክንያት ለሽማግሌዎቹ፣ ባለጉዳዮቹ፣ እና በማኅበረሰቡ አመለካከት ምንድነው?

3.5 ሽማግሌዎቹ የወሰኑትን ተግዳሮቹ እንዲቀበሉና በተግባር እንዲተረጉሙ የሚያደርጉበት መንገድ አለ? ካለ ምንድነው? ለምሳሌ ያስገድዷቸዋል? ልዩ ልዩ ተጽእኖ ያደርጉባቸዋል? ያግባቧቸዋል? ውሳኔው መተግበር አለመተግበሩን የሚከታተል ሰው ወይም አካል (ወገን body) አለ? ከበደኞቹ አንዱ ወይም ሁለቱም ውሳኔውን ቢያፈርሱ ሽማግሌዎቹ ምን ያደርጋሉ? በዚህ ጉዳይ ማኅበረሰቡ የሚጫወተው ሚና አለ? ካለ ምንድነው?

## 4. ወደሚጠናው ብሔረሰብ የግጭት መፍቻ ሥርዓት ብዙ ጊዜ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችና የተሰጡ ዓይነተኛ ውሳኔዎች

በዚህ ርእስ ውስጥ በሚጠናው ማኅበረሰብ ተደጋግመው የሚከሰቱ ዓበይት የግጭት ዓይነቶች ይዘረዘራሉ። ከዚያ በኋላ እያንዳንዳቸው ከየመነሻ ምክንያታቸው ጋር ባጭሩ ይገለጻሉ። ተመራማሪው እያንዳንዳቸውን ሲገልጽ ተገቢውን ቦታ እየመረጠ ለባህላዊው የግጭት መፍቻ ሥርዓት ቀርበው ከተሰጡ ውሳኔዎች አብነቶች (actual case histories) እያቀረበ ገለጻውን ያዳብራል። የግጭት ዓይነቶች ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ተመራማሪው ግንዛቤ እንዲያገኝና በእያንዳንዱ ስር ምን-ምን ጉዳዮችን መመርመር እንደሚገባው ለማመልከት በዚህ ቦታ አንዳንዶቹ ቀርበዋል። ሁሉም በርሱ ጥናት ውስጥ ዘርድ ያሉ ተራ ማለት እንዳልሆነ ግን ከወዲሁ መታወቅ አለበት። እርሱ ማተኮር ያለበት በሚያጠናው ማኅበረሰብ ውስጥ ጎልተው በሚከሰቱ ግጭቶች ላይ ነው።

4.1 ከሁከትና ከንብረት ጋር ተያያዥው የሚነሱ ግጭቶች። እነዚህ መሬትን፣ ድንበርን፣ የግጦሽ ቦታን፣ የውሃን፣ የከብት ዝርፊያን፣ ብድርንና የመሳሰሉትን ምክንያት አድርገው የሚነሱ ጠቦችን ይመለከታሉ።

4.2 የቤተሰብ ጠብ። እነዚህ ከጋብቻ፣ ከልጆች፣ ከውርስ ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው።

4.3 ወንጀል። ድብድብና ግድያን የመሳሰሉትን ያካትታል።

4.4 ተራ ወንጀሎች። ስርቆትንና የመሳሰሉትን ያካትታል።

4.5 የቡድን ጠብ። ይህ ደግሞ በጎሳና ጎሳ፣ በብሔረሰብና በብሔረሰብ፣ በሃይማኖትና በሃይማኖት መካከል የሚነሱትን ግጭቶች ይመለከታል። በዘመናችን ከቋንቋ፣ ከማንነት/ከምንነት (identity) እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች እንዳሉ ይታወቃል። ባህላዊዎቹ የፍትህ ሥርዓቶች እነዚህን የሚመለከቱ ከሆነም ጥናቱ ሊያካትታቸው ይገባል ማለት ነው።

## 5. በመደበኛ ፍርድ ቤትና በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት አሰራር መሀከል ያለ ግንኙነት

በዚህ ክፍል ውስጥ ተመራማሪው በሁለቱ መሀከል ያለውን ግንኙነት ያጠናል። አንዳንዴ ምንም ዓይነት ግንኙነት ላይኖር ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ ሁለቱ ሥርዓቶች በተጣጣመ መንገድ የሚሰሩበት ሁኔታ ይኖራል። በሌላ ጊዜ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ አንዳንድ አለመግባባት ሲኖር ይችላል። ስለዚህ፣ በዚህ ክፍል ይህንን ጉዳይ በጥልቀትና በጥንቃቄ መርምሮ፣ አብነቶችን (real case histories) በቃል ከሚነገሩ የእበው ተረኮችና ከመደበኛ ፍርድ ቤት ፋይሎች በሚሰበሰቡ የጽሁፍ ማስረጃዎች ደግፎ ማቅረብ ወደፊት በኢትዮጵያ ሲዘጋጁ ለሚችሉት ህጎችና ደንቦች መልካም ግብአት ይሆናል።

ተማራማሪው ይህንን ግንኙነት ለማጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጠየቀ እንዲጎዝ ለመነሻ ያህል ቀርበዋል። የመስክ ምርምሩ እየዳበረ ሲሄድ የሚነሱ ጥያቄዎችን እያከለ እነዚህን ማዳበር እንደሚጠበቅበት ግልጽ ነው።

5.1 ምርምሩ በሚካሄድበት ወረዳ / ዞን / ክልል ባህላዊው የሽምግልና ስርዓት ባሁኑ ጊዜ ዋናው የፍትሕ ሥርዓት ነው? ከመቼ ጀምሮ? ለምን?

5.2 በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ፣ አንዳንድ ግጭቶችን በመፍታት ከመደበኛው ፍርድ ቤት ይልቅ የባህል ሽምግልናው ጠቃሚና ፍትሓዊ ነው ተብሎ ይታመናል? በምን ምክንያት? ለነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች አንዳንድ አብነቶችን (real case histories) እየጣቀሱ መደገፍ አስፈላጊ ነው።

5.3 በማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ፥ አንዳንድ ግጭቶችን በመፍታት ደግሞ መደበኛው ፍርድ ቤት ከባህላዊው ይበልጥ ጠቃሚና ፍትሓዊ ነው ተብሎ ይታመናል? በምን ምክንያት? ለነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትንም መልሶች አንዳንድ አብነቶችን (real case histories) እየጠቀሱ መደገፍ አስፈላጊ ነው።

5.4 ጥናቱ በሚከናወንበት አካባቢ ሁለቱ የፍትሕ ሥርዓቶች በትብብርና በመደጋገፍ የሚሰሩባቸው ጊዜያት አሉ? መቼ ወይም ጉዳዩ ምን ሲሆን ነው የሚተባበሩና የሚደጋገፉት? ምን-ምን በማድረግ ነው የሚተባበሩ-የሚደጋገፉት? ለምን?

5.5 ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት የመደበኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሽርበት ወቅት/አጋጣሚ ምርምሩ በሚከናወንበት አካባቢ ተከስቶ ያውቃል? መቼ? ለምንድነው ውሳኔውን የገለበጠው? በአብነቶች (real case histories) የተደገፈ ዝርዝር ገለጻ በማቅረብ ሃሳብን ማጠናከር ያስፈልጋል።

5.6 መደበኛው ፍርድ ቤት የባህላዊውን የፍትሕ ሥርዓት ውሳኔ የሚሽርበት ወቅት/አጋጣሚ ምርምሩ በሚካሄድበት አካባቢ ተከስቶ ያውቃል? መቼ? ለምንድነው ውሳኔውን የገለበጠው? በአብነቶች (real case histories) የተደገፈ ዝርዝር ገለጻ በማቅረብ ሃሳብን ማብልጸግ ያስፈልጋል።

## 6. ትንተና እና ቁዘማ (analysis and reflection)

ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ተማራማሪው የሚያቀርበው ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቹና ከሌሎች አቀባዮቹ የሰበሰባቸውን መረጃዎች አስናድቶ ነው። የሚያቀርብበት መንገድም በተቻለ መጠን ዝርዝርና በገለጻ (description) መልክ ነው። የግል አስተያየትም ሆነ አስተውሎት (observation) ከመስጠት በተቻለ መጠን መቆጠብ አለበት።

ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ባሉት ክፍሎች ውስጥ ባቀረባቸው መረጃዎች፥ ማለትም በመዋቅሩ፥ በሂደቶች፥ በአፈጻጸም ሥነሥርዓት (rituals) ውስጥ ቀርበው ተጨማሪ ፍች ወይም ትርጓሜ (interpretation) የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ ትእምርታዊ (symbolic) ጉዳዮችን የሚተነትነው በዚህ ክፍል፥ ማለትም «በትንተና እና ቁዘማ» ውስጥ ነው። ትርጓሜዎቹም ከሁለት ምንጭ ተቀድተው፥ በትንተናው ውስጥ እየተስተያዩ የሚዋሃዱት እየተዋሃዱ፥ የሚለያዩት እየተለያዩ በመጨረሻ ወደ ማጠቃለያ ይሄዳል። የትእምርቶቹ ፍች የሚሰበሰበው አንድም ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች እና ከሚጠናው ማኅበረሰብ አባላት ነው። ተመራማሪው እነሱ የሚሰጡትን ፍች (interpretation) የእነሱ መሆኑን እየገለጸ ያቀርባል። የሰበሰባቸውን መረጃዎች በሙሉ፥ ሙያዊ እውቀቱን እና ለዚህ ምርምር ሲል ካነበባቸው ምንጮች የቀሰመውን እያጣቀሰ ደግሞ የእርሱን ትርጓሜ (interpretation) የትንተና መልክ ያቀርባል።

በዚህ የትንተና ክፍል ከሚያነሳቸው ነጥቦች መሀከል በሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ የተጠቆሙት ተጨማሪ ሆነው ቀርበዋል። ታድያ፥ ተመራማሪው፥ መረጃዎቹንና እውቀቱን አዋህዶ ከዚህ በታች በሰፈሩት መምሪያዎች ላይ የሚጨምረውን መጨመር፥ የሚቀንሰውን መቀነስ ይጠበቅበታል።

6.1 ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት በምን ዓይነት ማኅበራዊ እሴቶች ላይ የተመሰረተ ነው? የሚመሩት ማኅበራዊ እምነቶችና መርሖች ምንድናቸው?

6.2 የሚጠናው ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓት ብርታቶች እና ድክመቶች ምንድናቸው? ይህ ሥርዓት ይቀጥላል ተብሎ ይታመናል? የሽማግሌዎችና የሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት አስተያየት ምንድንነው?

6.3 ጠበኞች ባህላዊውን የፍትሕ ሥርዓት ተቀብለው ጉዳያቸውን ወደዚያ እንዲወስዱ የሚያደርጋቸው መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው?

6.4 ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት በየጊዜው የሚመጡትን የጠበኞች ግጭት ከመፍታት አልፎ ማኅበራዊውን ሰላም የማስጠበቅና የማረጋጋት ፋይዳው ምን ያህል ነው?

6.5 ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት ለባለጉዳዮች መኖሪያ ቅርብ በመሆኑ፥ የሚያስወጣው ወጪም ወደ መደበኛው ፍርድ ቤት ሲኬድ ከሚወጣው እጅግ በማነሱ፥ ቢሮክራሲያዊ ውጣ-ውረዱ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ተገልጋዮች ይመርጡታል የሚል ሃሳብ በተለያዩ ተመራማሪዎች ይነሳል። በዚህ ስራ በሚጠናው ማኅበረሰብ አባላት ዘንድ ተመሳሳይ አስተያየት ካለ በአባላቱ አነጋገርና በአብነቶች ተደግፎ ይቅረብ።

6.6 በባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት ሂደት ውስጥ የሚጠናው ማኅበረሰብ አባላት ያላቸው ወይም የሌላቸው ሚናም ምክንያት እየቀረበለት ይተንተን።

6.7 ባህላዊው የፍትሕ ሥርዓት የአረጋውያንን፥ የሴቶችን፥ የህጻናትን እና የሌሎች ተመሳሳይ የማኅበረሰብ ክፍሎች መብት የሚያስተናግድበት ሁኔታ እስ? ይተንተን።

6.8 በቁልፍ መረጃ አቀባዮች፥ በስልት በተመረጡ የማኅበረሰቡ አባሎች እና በተመራማሪው አስተያየት ትተነትነው የባህላዊ የፍትሕ ሥርዓት መልክዎም ባህርያት የትኞቹ በመደበኛው የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ቢካተቱ ይጠቅማል? የፖሊሲ አውጪዎች አጥንተዋቸው ወይም አስጠንተዋቸው አግባብ ያለው እርምጃ ቢወስዱ ይጠቅማል የሚባሉ ገጽታዎች የትኞች ናቸው?

## 7. ማጠቃለያ (a kind of concluding remark)

## 8. ይሁንታ (Recommendations)- እዚህ በምርምሩ ውጤቶች ላይ ተመስርተው የሚሰነዘሩ፥ በተቻለ መጠን ሕግ ማውጣትና ፖሊሲ ለመንደፍ አቅጣጫ የሚጠቁሙ መሆን ይገባቸዋል። ምርምር ያላደረገ ማንኛውም ሰው ሊሰነዝራቸው የሚችላቸው፥ «ባህላዊ የፍትሕ ስርዓቱ ተጠናክሮ ሕግ ግብአት የሚሆንበት መንገድ ይፈለግ» የሚሉ ዓይነት መሆን የለባቸውም ማለቱ ነው።

**ጥቅስማ (References)** በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሱት ብቻ የሚገቡበት ስለሆነ ነው «ጥቅስማ» የተባለው። አጠቃላይ መዘርዝር (Bibliography) አይደለም።

ፈቃደ አዘዘ
የካቲት 18 2003